

District of Columbia
Office of the State Superintendent of Education

# ለቅድመ-ትምህርት ዕድገት
# የገንዘብ አበርክቶ
# ከልደት እስከ አምስት ዓመት ዕድሜ

## የአስፈላጊ ነገሮች ግምገማ

2019

# ምስጋና

ይህ ጽሑፍ ለህትመት የበቃው፣ በ ቅድመ-ትምህርት የዕድገት የገንዘብ አበርክቶ፣ ከልደት እስከ አምስት ዓመት ዕድሜ (Preschool Development Grant, Birth through Five (PDG B-5) አነሳሽነት፣ ከህጻናት እንክብካቤ ጽህፈት ቤት፣ ከህጻናት ልጆችና ቤተሰቦች አስተዳደር፣ ከአሜሪካን መንግስት የጤና ጥበቃና ማህበራዊ አገልግሎት ክፍል በ ተደረገ የገንዘብ አበርክቶ፣ ቁጥር 90TP0045 አማካኝነት ነው።

ይዘቱም፣ ሙሉ በሙሉ የጸሓፊዎቹ ሃላፊነት እንጂ ከህጻናት ልጆች እንክብካቤ ጽህፈት ቤት ፣ ከልጆችና የቤተሰቦች አስተዳደር ወይም ከአሜሪካ የጤና ጥበቃና ማህበራዊ አገልግሎት ሚኒስቴር ጋር ላይመሳሰል ይችላል።

በተጨማሪም፣ የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ አስተዳደር ተሞክሮዎቻቸውን፡ እውቀታቸውንና አስተያየታቸውን ላካፈሉና ላበረከቱ ቤተሰቦች፣ የዲስትሪክቱ ተቋሞች ሽሪኮቹ፣ በማህበረሰቡ የሚገኙት ህዝባዊ ድርጅቶች፣ ጠበቃዎች፣ የህጻናት መማህራንን እንዲሁም አስተዳዳሪዎች እውቅና ለመስጠትና ምስጋናውንም ለማቅረብ ይወዳል።

# የይዘት ማውጫ


**ምስጋና** 2

**መግቢያ** 4

**ድሕረ-ታሪክ** 4

**የአሰራር አገባብ** 5

**ክፍሎች** 6

ክፍል 1 ግኝቶች 7

ክፍል 2 ግኝቶች 8

ክፍል 3 ግኝቶች 13

ክፍል 4 ግኝቶች 15

ክፍል 5 ግኝቶች 20

ክፍል 6 ግኝቶች 22

ክፍል 7 ግኝቶች 23

ክፍል 8 ግኝቶች 25

ክፍል 9 ግኝቶች 27

ክፍል 10 ግኝቶች 29

ክፍል 11 ግኝቶች 32

**ማጠቃለያ** 33

**ተጨማሪ** 34

**ተጨማሪ ሀ፤ በፍላጎት ግምገማ ላይ መረጃ የሰጡ ምንጮች** 34

**ተጨማሪ ለ ፤ ለጉዳት ለተጋለጡና ማግኘት ከሚገባቸው አገልግሎት በታች ለሚያገኙ ልጆች ጥራት ያለው እንክብካቤ ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ፤ ዲስትሪክቱ የሚወስዳቸው እርምጃዎች** 37

# መግቢያ

## ድሕረ-ታሪክ

በታህሳስ ወር 2018፡ የክፍለሃገሩ የትምህርት ጽሕፈት ቤት (ኦ-ኤስ-ኤስ-ኢ)( Office of the State Superintendent of Education (OSSE)፣ በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምብያ አማካኝነት፣ የመንግስታዊ የቅድመ- ትምህርት ዕድገት፣ ከልደት እስከ አምስት ዓመት ዕድሜ (Preschool Development Grant, Birth through Five (ፒ-ዲ-ጂ ቢ-5 PDG B-5) ላላቸው ልጆች የሚሆን $10.6 ሚልዮን የገንዘብ አበርክቶ አግኝቷል። በዚህ በፒ-ዲ-ጂ ቢ-5( PDG B-5) የገንዘብ አበርክቶ፣ ዲስትሪክቱ፤ ህጻናት ልጆችን በሚመለከት፣ በማንኛውም የህጻናት ልጆች የትምህርት ዘርፍ፣ ልጆችንና ከልደት እስከ አምስት ዓመት ዕድሜ ህጻናት ልጆች ያሏቸውን ቤተሰቦች የሚያግዝ፡ ግንኙነትና ትብብር፣ ቀደም ብሎ የሚጀመር እንክብካቤና ትምህርት ኢ-ስ-ኢ (ECE)፣ የልጆች ጤንነት፣ የአእምሮ ደህንነት፣ ማህበራዊ አገልግሎት፣ ቀደም ብሎ የሚደረግ የጣልቃገብነት ፕሮግራምና አገልግሎት የሚያጎለብት፤ አነሳሽነትን በሚመለከት እየሰራ ነው። እንዲሁም ኦ-ኤስ-ኤስ-ኢ (OSSE) ከአያሌ ባለሃብቶች፡ ቤተሰቦች፡ ሌሎች የዲስትሪክቱ ተቋሞች፡ የግልና ለበጎ አድራጎት ከተነሳሱ ድርጅቶች ጋር በመተባበርና ይህንን ለማሻሻል በሚያስፈልጉ ነገሮች ላይ ግምገማና ጥናት በማካሄድና ጥንቃቄ የተመላበት ስልታዊ ዕቅድና ሂደት በማውጣት፤ የዲስትሪክቱን የህጻናት የትምህርት ዘርፍ ለማሻሻል በከፍተኛ ደረጃ እየሰራ ነው።

ይህ ከፍተኛ ጥራት ያለው የ ኢ-ስ-ኢ ( ECE) ተመክሮ፡ ልጆች ከፍተኛ እውቀት እንዲያገኙ፤የተሻለ የጤንነት ደረጃ ላይ እንዲደርሱና ወደኋላም ጥሩ የደሞዝ ክፍያ ወደሚያገኙበት ደረጃ ያመራቸዋል።[1,2,3] ህጻናት ልጆች፤ በተለይም ለጉዳት የተጋለጡ ናቸው የሚባሉትና ማግኘት ከሚገባቸው አገልግሎት በታች የሚያገኙ ህጻናት ልጆች፤ ገና ከህጻንነታቸው ጀምሮ፤ ጥራት ያለው ትምህርት በማግኘት፤ ለጤንነታቸው ከፍተኛ እንክብካቤ በማድረግ በትምህርታቸውና በ እድገታቸው በማሻሻል በኩል ከፍተኛ ጫና አለው።[4,5] ዲስትሪክቱ ገና ለተወለዱና እስከ አምስት ዓመት ዕድሜ ላላቸው ህጻናት፣ በርካታ የትምህርት ዘርፍ ያላቸውን ፕሮግራሞች በመመስረትና በማካሄድ ይሰራል።[6] በ 2017-18 የትምህርት ዓመት ለምሳሌ ዲስትሪክቱ፣ የሶስት ዓመት (3) ዕድሜ ካላቸው ህጻናት ልጆች ውስጥ 72 ከመቶው፡ ዕድሜአቸው አራት ዓመት(4) ከሆነ ልጆች ደግሞ 86 ከመቶው በመንግስት ገንዘብ በሚተዳደሩ ትምህርት ቤቶች ውስጥ እንዲገቡ በማድረግ፤ ከመላው አገር የመጀመርያውን ደረጃ ይዞ ይገኛል። [7] በተጨማሪም ዲስትሪክቱ፣ የህጻናት ትምህርት አስተዳዳሪ፡ መማህራን፣ ምክትል መማህራን፣ በመኖርያ ቤት ውስጥ የልጆች እንክብካቤ ሰጪ ለመሆን የሚያስፈልገውን የትምህርት ደረጃን በመላው አገሪቱ ከፍ ካደረጉት የመጀመርያዎቹ ውስጥ አንዱ ነው።

በተጨማሪም፤ ቀደም ሲል በተደረሰው የመረጃ መለዋወጥ ስምምነት መሰረት እንዲሁም በስምምነት ውል (MOA)፣ እንደ የክፍለሃገሩ የህጻናት ዕድገት የትብብር ምክርቤት (State Early Childhood Development Coordinating Council (SECDCC) እና ኮሚቴዎቹ፣ ትሪይቭ ባይ ፋይቭ ዲሲ( Thrive by Five DC) እና በ የካቲት ወር በ2019 በተመሰረተው ትራይቭ ባይ ፋይቭ አስተባባሪ ምክርቤት ( Thrive by Five Coordinating Council በመሳሰሉትና በተለያዩ ሌሎች ተቋሞች መካከል፤ የመረጃ መለዋወጥንና ትብብርን ለማጠናከር ብዙ ተሰርቷል። በቀላሉ ግንኙነት የመፍጠር ሰኬታማነት ግልጽ ቢሆንም፣ በሁሉም ከልደት እስከ 5 ዓመት ዕድሜ ልጆች ባላቸው ቤተሰቦች መካከል ግንኙነትና የመረጃ መለዋወጥ እንዲኖር ዲስትሪክቱ በበለጠ መስራት እንዳለበት ያምናል። ዲስትሪክቱ፣ ይህንን መኖር የሚገባውን የመረጃ መለዋወጥንና ትብብርን በበለጠ ለማጥናከርና ወጣት ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦች እውቀት እንዲጎለብትና በሚያስፈልጉ ስራዎች ትብብራቸውን ለማግኘት፣ ይህንን የፍላጎቶች ግምገማ ይጠቀማል።

ይሄው የአስፈለጊ ነገሮች ጥናትና ግምገማ፣ እንደ አንድ የ PDG B-5 አካል ሁኖ የተካሄደ ሲሆን በ 2019 የተገባደደ ነው። በመሆኑም ጥናቱ ኮሮናቫይረስ ወይም ኮቪድ- 19 (COVID-19)ን በሚመለከት ሊነሱ ለሚችሉ ጥያቄዎች ወይም አስተያየቶች መልስ አይሰጥም።

---

[1] Bainum Family Foundation, *Early Learning Supply and Demand in the District of Columbia: Using Data to Identify Critical Gaps*, 2018.
[2] Andres S. Bustamante, Kathy Hirsh-Pasek, Deborah Lowe Vandell, and Roberta Michnick Golinkoff. *Realizing the promise of high-quality early childhood education* Brookings Institution, 2017.
[3] ZERO TO THREE, *America's Future Depends on Quality Childcare*, 2019.
[4] Bainum Family Foundation, *Early Learning Supply and Demand in the District of Columbia. Using Data to Identify Critical Gaps*, 2018.
[5] ZERO TO THREE, *Infant-Toddler Child Care Fact Sheet*, 2017.
[6] According to the Every Student Succeeds Act passed by the 114th Congress, "the term 'mixed-delivery system,' as defined by the Every Student Succeeds Act (ESSA), Pub. L. 114-95, Section 9212(b)(5), means a system of early childhood care and education services that are delivered through a combination of programs, providers, and settings, such as Head Start, licensed family and center-based child care programs, public schools, and other community-based organizations, that is supported by a combination of public and private funds." See 114th Congress Public Law 95, U.S. Government Publishing Office, https://www.congress.gov/114/plaws/publ95/PLAW-114publ95.htm.
[7] Office of the State Superintendent of Education, *Fiscal Year 2018 Pre-K Report*, 2018.

## የአሰራር አገባብ

ይህ የፍላጎቶች ግምገማ ወይም ጥናት፤ መረጃዎቹን፣ ከልደት እስከ አምስት ዓመት ዕድሜ ህጻናት ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦች፣ ልጆችና ማህበረሰቦች የሚያስፈልጓቸው ነገሮች ምን እንደሆኑ ግልጽ ለማድረግ፤ ከተለያዩ ተቋሞች የመረጃ ምንጮች ይሰባበስል።

ይህ የአስፈላጊ ነገሮች ግምገማ በስምንት የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምብያ ምንጮች ላይ የተመሰረተ ነው፡

1. እስከአሁን የቀረቡትን 20 የሚሆኑ ፍላጎቶችን እንደገና መገምገም
2. ከአገሪቱና ከዲስትሪክቱ መረጃዎች በመነሳት የአስተዳደር ና የህዝብ ብዛት መረጃዎችን መገምገም
3. በ32 ስብሰባዎች ቤተሰቦች የሰጡትን አስተያየት መስማት
4. 23 የባለሙያዎች የትኩረት ቡድኖች
5. ከ21 ቁልፍ የሆኑ መረጃ ሰጪዎች ጋር በተደረጉ ቃለመጠይቆች የተሰበሰቡ አስተያየቶች
6. በጥናቱ የተሳተፉ 2,099 ቤተሰቦች የሰጧቸው አስተያየቶች
7. የመጀመርያ የማሳያ ፕሮጀክት ሪፖርት
8. ኢ-ሲ-ኢ ን (ECE )በሚመለከት የቅርብ የክፍለሃገርና የአገር ሪፖርቶች

የእንዳንዱ ምንጭ ዝርዝር መረጃ በተጨማሪው መረጃ አፔንዲክስ(Appendix) ሀ ላይ ይገኛል። እነኚህ መረጃዎች ሁሉ አንድ ላይ ሲጠቃለሉ፤ ከልደት እስከ አምስት ዓመት ዕድሜ ላላቸው ህጻናት ልጆች የሚሰጠውን የትምህርት ይዘት በሚመለከት የዲስትሪክቱን ሃያል ጎኖችንና ሊያድግበት የሚያስችሉትን የተጣራና የተሻሻለ ጥናቶችን ያቀርባሉ።

# ክፍሎች



ከዚህ ቀጥሎ የሚገኘው ይዘት፤ በፒ-ዲ-ጂ( PDG) እንደ ክፍሎች በተመላከቱት በ አስራ አንዱ ክፍሎች ስር በ ህጻናት እንክብካቤ ጽህፈት ቤት፣ በህጻናት ልጆችና በቤተሰቦች አስተዳደር ክፍል፣ በአሜሪካ የጤናና የማህበራዊ አገልግሎት ሚኒስቴር ስር ይገኛል።[8] የሚያስፈልጉ ነገሮች ምን እንደሆኑ ለማወቅ ከአጠቃላይ ክፍሎቹ በተመረጡ መሪ ጥያቄዎች ነው የተገመገሙት።

የመጀመርያዎቹ ሶስት ክፍሎች የድህረ ታሪክ መረጃ፤ እንዲሁም የአንዳንድ ቃላትና አገላለጾች ማስረጃ የሚገኝባቸውና  ትኩረት የተሰጠበት የማህበረሰቡ ክፍል የትኛው መሆኑን የሚያስረዱ ናቸው። እያንዳንዱ የተቀረው ክፍል፤ ዲስትሪክቱ ገና የተወለዱ ህጻናትና እስከ 5 ዓመት ዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ህጻናት ጥራት ያለው አገልግሎት የሚያገኙባቸውን ፕሮግራሞችና አገልግሎቶችን እንዴት እንደሚገነባና እንደሚያሻሽል የሚያስረዱ ናቸው።

[8] Early Childhood Training and Technical Assistance Program, *PDG B-5 Needs Assessment Guidance*, 2018.

## ክፍል 1 ግኝቶች

# የስያሜዎች መግለጫ

**መሪ ጥያቄ: ዲስትሪክቱ፤ በዚህ የገንዘብ አበርክቶ የተጣራ ወይም ጥራት ያለው ሲል ምን ማለት ነው?**

**ግኝት 1 ሀ.** ዲስትሪክቱ ጥራት ያለው የኢ-ሲ-ኢ (ECE) ፕሮግራም ሲል ዕድሜአቸው ከልደት እስከ አምስት ዓመት የሆኑ ልጆችን የሚያስተናግዱና የህጻናቱን መሰረታዊ ጤንነትና ደህንነት ለመጠበቅ የህጻነት መዋያ ቦታዎቸ ማሟላት ያለባቸውን የጤናና የደህንነት ጥበቃ የሚያሟሉና የስራ ፍቃድ ያሏቸው ማለቱ ነው። እነኚህ የህጻናት ቦታዎች የህጻናቱን የእውቀት ደረጃ፣ የእንቅስቃሴ ችሎታ፣ ማህበራዊና ስሜታዊ እድገታቸውን የሚያጠናክር፤ ጥራት ያለው ፕሮግራም በመሰጠት ላይ መሆናቸውን የሚያረጋገጥ አጥጋቢ አገልግሎቶችን በመስጠት ላይ መሆናቸውን ማሳየት አለባቸው( ለምሳሌ የህጻናቱን ፍላጎት የሚያሟላ የፕሮግራም አቀራረብና የሞቀና አዎንታዊ ዝምድና እንዳለ)። ዲስትሪክቱ፡ የፕሮግራሞች ሰኬታማነትን የሚለካበት አያሌ መንገዶች አሉት፤ እነዚህም የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፡ ካፒታል ኳሊቲ Capital Quality፡ የዲስትሪክቱ የጥራት መለኪያና የመሻሻል ሁኔታ(Quality Rating and Improvement System (QRIS) (https://osse.dc.gov/page/capital-quality-qris)፤የቅድመ ትምህርትን ለማጎልበት የሚደረግ የገንዘብ አበርክቶ( Pre-K Enhancement and Expansion Funding Program (PKEEP)፤ ለማህበረሰቡ ተቋሞች ጥራት ያለው ሚና መስጠት (community-based organizations (CBOs) (https://osse.dc.gov/publication/fy-2020-21-pre-k-enhancement-and-expansion-funding-high-quality-designation-application)፤ የክፍል ውስጥ ትምህርት ውጤትና አሰጣጥ ስነስርአት (Classroom Assessment Scoring System (CLASS) ለቅድመ ትምህርት ቤት ህጻናትና በዲስቲክቱ ላሉ የመንግስት ትምህርት ቤቶች (DCPS)፤ የህዝብ የቻርተር ትምህርት ቤቶችና እና CBOs (PKEEP and non-PKEEP) (https://osse.dc.gov/page/program-quality-evaluation-and-assessment-class-pre-k)፤ እንድ አንድ ግልጽነትንና ሪፖርት አደራረግን የሚያሳይ( the School Transparency and Reporting (STAR) የዲሲ የትምህርት ሪፖርት ካርድ (DC School Report Card (https://osse.dc.gov/dcschoolreportcard) ፤ለዲሲ የመንግስት ትምህርት ቤቶችና የቻርተር ትምህርት ቤቶች (https://osse.dc.gov/page/dc-school-report-card-resource-library)። ወደ ህጻናቱ መኖርያ ቤት ጉብኝት ማድረግ ደግሞ በእናቶች፣ ህጻናትና የቤት ጉብኝት ክፍል (Maternal, Infant and Early Childhood Home Visiting (MIECHV) ) እንደ አንድ የታማኝነት ጥሩ ምሳሌ የሚወሰድ ነው (https://dchealth.dc.gov/perinatal)።

**መሪ ጥያቄ፣** ለጉዳት ለተጋለጡና ማግኘት ከሚገባቸው አገልግሎት በታች ለሚያገኙ የሚሰጥ የገንዘብ አበርክቶ ሲባል ምን ማለት ነው?

**ግኝት 1 ለ፤ ዲስትሪክቱ ለጉዳት የተጋለጡ ልጆች ሲል ከሚከተሉት ውስጥ በአንዱ ክፍል ወይም ከዛ በበለጠ ያሉ ልጆች ማለቱ ነው፣**

- የተረጋገጠ ልዩ አገልግሎት የሚያስፈልጋቸው ወይም የዕድገት መዘግየት ያለባቸው ልጆች
- ከአባትና እናት ውጪ በሌሎች አሳዳጊዎች ቤት ውስጥ የሚኖሩና ከልጆች ና ቤተሰቦች አገልግሎት ተቋም (Child and Family Services Agency (CFSA)፣ ጋር የተያያዙ ወጣት ልጆች ካሏቸው ቤተሰቦች ጋር የሚኖሩ ልጆች
- የቤት-አልባነት ተመክሮ ያሳለፉ ልጆች ወይም
- ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦች ልጆች (ማለትም መንግስት የድህነት መመዘኛ ብሎ ካወጣው ክልል በ250 ከሙቶ ውስጥ)ያሉ ልጆች ፣ ከመንግስት የተጨማሪ ምግብ እርዳታ የስናፕ (SNAP) ወይም ለችግረኛ ቤተሰቦች መንግስት በሚሰጠው እርዳታ በ ቲ--ኤ-ኤን-ኤ((TANF) ውስጥ የሚገኙ

ዲስትሪክቱ፤ ማግኘት ከሚገባቸው አገልግሎት በታች የሚያገኙ ልጆች ሲል ደግሞ በጣም ከፍተኛ ድህነት ባለበት ማህበረሰብ ውስጥ የሚኖሩና ከልጅነታቸው ጀምሮ ጥሩ የትምህርት ፕሮግራም የማግኘት ዕድል ፍጹም የሌላቸውን ልጆች ነው።

**መሪ ጥያቄ፣** በዚህ የገንዘብ አበርክቶ ውስጥ፣ የመጀመርያው የህጻናት ልጆች እንክብካቤ ሲባልና የትምህርት ዕድል መኖር ሲባል ምን ማለት ነው?

**ግኝት 1 ሐ ፤** ዲስትሪክቱ የኢ-ሲ-ኢ( ECE) ፕሮግራሞች መኖር ሲል ከ 3 እስከ 5 ዕድሜ ያላቸውን ህጻናት ልጆችን ለማስተናገድ የስራ ፈቃድና ቦታው ያላቸውን ማለቱ ነው። ከ 3 እስከ 5 ዓመት ዕድሜ ላላቸው ህጻናት ደግሞ የስራ ፈቃድ ያለውና በዲሲ የመንግስት ትምህርት ቤቶችና በቻርተር ትምህርት ቤቶች ውስጥ ቦታ መኖሩን የሚያጠቃልል ነው። ህጻናት ልጆችን መኖርያ ቤታቸው ድረስ እየሄዱ መጎብኘትና አገልግሎትና ድጋፍ መስጠትን ደግሞ በሁለት መልኩ ነው የሚያየው- ቤተሰቦችን ለማገልገል ባሉት ቦታዎች ቁጥርና በሙሉ ግዚያቸው ተቀጥረው በሚሰሩ ሰራተኞች ቁጥር።

## ክፍል 2 ግኝቶች

# የገንዘብ አበርክቶውን ለመቀበል ትኩረት የሚሰጠው የህዝብ ክፍል

***መሪ ጥያቄ፣*** በዲስትሪክቱ ውስጥ ማግኘት የሚገባቸውን የማያገኙ ወይም ከሚገባቸው በታች የሚያገኙ ልጆች የትኛዎቹ ናቸው?

### ግኝት 2 ሀ፣ ለጉዳት የተጋለጡና ማግኘት ከሚገባቸው በታች የሚያገኙ ልጆች በብዛት በ ቤቶች(Wards) 7 እና 8 የሚኖሩ ናቸው። [9,10]

በአማካይ ሲታይ፤ በ ቤቶች 7 እና 8 ከሚኖሩት ውስጥ 45 ከመቶው 18 ዓመት ዕድሜ ወይም ከዛ በታች የሆኑ ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦች ሲሆኑ፣ መንግስት ካወጣው የድህነት ደረጃ ከ መቶ 40.90 እና 48.50 በድህነት ክልል ውስጥ የሚገኙ ናቸው። [11] በ ቤቶች 2 እና 3 የሚኖሩት ደግሞ 18 ዓመት ዕድሜ ወይም ከዛ በታች የሆኑ ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦች ሲሆኑ፣ መንግስት ካወጣው የድህነት ደረጃ ከመቶ 4.60 እና 2.90 መካከል የሚገኙና ዝቅተኛውን ደረጃ የያዙ ናቸው።[12]

### በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ህጻናት ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦች መለያ ጠባዮች

በዲስትሪክቱ ውስጥ ፈጣን እድገት የሚያሳዩ ልጆች ናቸው። በአሁኑ ግዜ በዲስትሪክቱ ውስጥ ዕድሜአቸው ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ከ45,000 በላይ ሲሆኑ፤ ከእነዚህም ውስጥ 28,203 ገና የተወለዱና ዕድሜአቸው እስከ 3 ዓመት የሆኑ ናቸው። 16,832ው ደግሞ የ3 ዓመትና የ4 ዓመት ዕድሜ ልጆች ናቸው።[13]

- 5,012 (11 ከመቶ) የ 5 ዓመት ዕድሜ ወይም ከዛ በታች የሆኑ መንግስት ለችግረኛ ቤተሰቦች በሚሰጠው እርዳታ በ(TANF) የታቀፉ ቤተሰቦች ልጆች ናቸው።[14]
- 1,168 (2.60 ከመቶ) 5 ዓመት ወይም ከዛ በታች የሆኑ ልጆች በቅርቡ በቤት አልባነት ተመክሮ ያለፉ ናቸው።[15]
- 1,323 (3 ከመቶ) 5 ዓመት ወይም ከዛ በታች የሆኑ ልጆች የተመዘገበ አንድ ዓይነት ስንክልና ወይም የእድገት መዘግየት ችግር ያላቸው[16] እና
- 177 (0.30 ከመቶ) 5 ዓመት ወይም ከዛ በታች የሆኑ ልጆች ደግሞ ከህጻናት ና ቤተሰቦች አገልግሎት ድርጅት (CFSA) ጋር ግንኙነት ያላቸው ናቸው።[17]

በዲስትሪክቱ ውስጥ ያለው የልጆች ስርጭት ሁሉም ቦታ ውስጥ አንድ ዓይነት አይደለም። በመላው ዲስትሪክት ውስጥ ከሚገኙት ህጻናት ልጆች ግማሾቹ (በ4፣ 5፣ 7 እና 8 ቤቶች( wards) 4፤ 5፤ 7 እና8) ውስጥ የሚኖሩ ናቸው። ቤት 2 (Ward 2) ውስጥ ከሁሉም እጅግ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ልጆች ነው የሚኖሩት።[18]

### ገቢያቸው በጣም ዝቅተኛ የሆነ ፤ ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦች

ከ 2011 ጀምሮ፣ በዲስትሪክቱ የሚኖሩና መንግስት ካወጣው የድህነት ደረጃ በታች ገቢ ያላቸውና የ18 ወይም ከዛ በታች ዕድሜ ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦች ቁጥር በ2011 ከነበረበት 4 ከመቶ በመቀነስ 30 ከመቶ ሲሆን፤ በ 2017[19] ደግሞ 26 ከመቶ ሆኗል። በዲስትሪክቱ የሚኖሩና መንግስት ካወጣው የድህነት ደረጃ ከ250 ከመቶ በታች ገቢ ያላቸውና የ18 ወይም ከዛ በታች ዕድሜ ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦች ቁጥር በ2011 ከነበረበት 53 ከመቶ፣ 5 ከመቶ በመቀነስ፣ በ 2017[20] 48 ከመቶ ሆኗል።

---

9 Kids Count Data Center and Annie E. Casey Foundation, *Children in Poverty by Age Group in District of Columbia*, 2017, p. 21.
10 *Ibid*, p. 21.
11 *Ibid*, p. 56.
12 Kids Count Data Center, *Annie E. Casey Foundation, Children below 250 percent poverty in District of Columbia*, 2016.
13 U.S. Census Bureau, ACS 5-Year Survey, 2017.
14 DC Department of Human Services, Economic Security Administration.
15 Metropolitan Washington Council of Governments.
16 District of Columbia Office of the State Superintendent of Education, 2017.
17 DC Child and Family Services Agency.
18 Kids Count Data Center, *Annie E. Casey Foundation, Children below 250 percent poverty in District of Columbia*, 2016.
19 Kids Count Data Center, *Annie E. Casey Foundation, Children in Poverty by Age Group in the District of Columbia*, 2016.
20 Kids Count Data Center, *Annie E. Casey Foundation, Children below 250 percent poverty in District of Columbia*, 2016.

በ 2017፣ በዲስትሪክቱ ካሉት ቁጥራቸው ከ45,000 ከሚበልጥ ቤተሰቦች ውስጥ ዕድሜአቸው ከ ልደት እስከ 5 ዓመት የሆኑ ልጆች ያሏቸው 5,012 ቤተሰቦች፤ በጣም አነስተኛ ገቢ ያላቸውና ቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ (TANF) በመባል የሚታወቀው መንግስት ለችግረኛ ቤተሰቦች የሚሰጠው እርዳታ ተቀባዮች ናቸው። [21] ይህም የሚያሳየው ከእነዚህ ዕድሜአቸው ከ ልደት እስከ 5 ዓመት የሆኑ ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦች፣ ዕድሜአቸው ከ3 እስከ 5 ዓመት ከሆነ ልጆች ቤተሰቦች ይልቅ፣ ከመቶ ስድሳ ስምንቱ እስከ ሁለት ዓመት ዕድሜ ልጆች ያሉዋቸው ቤተሰቦች ናቸው የቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ (TANF) የመንግስት እርዳታ የሚቀበሉት። ከ 2016 እስከ 2017፣ ቁጥራቸው ወደ 500 የሚሆን ቤተሰቦች፤ የቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ (TANF) የመንግስት እርዳታ ለማግኘት ተመዘገቡ። ከእነዚህ ውስጥም ከ80 ከመቶ የሚበልጡቱ፤ በ ቤቶች 7 እና 8 ( wards 7 እና 8) የሚኖሩ ናቸው። ይህም የሚያሳየው አነስተኛ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦች የታጨቁት በአንድ አካባቢ መሆኑን ነው። [22]

### ቤት-አልባነት ያጋጠማቸው ቤተሰቦች

በልጆች ቁጥር መረጃ ማእከል( Kids Count Data Center) መሰረት፤ በ 2017፤ በቤተሰብ ውስጥ የነበሩ 2,281 ልጆች የቤት-አልባ ተመክሮ ያሳለፉና ቋሚ አድራሻ ያልነበራቸው ናቸው። በ 2017፤ ለ1,358 ቤተሰቦች ቀልጣፋ የቤት ድጋፍ ተደረገላቸው። በ 2018፤ 1,434 ቤተሰቦች ቀልጣፋ የቤት ድጋፍ ተደረገላቸው። የቤት አልባነት ችግር የሚያጋጥማቸው አብዛኛውን ግዜ ትናንሽ ህጻናት ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦች ናቸው። የቤት-አልባነት ችግር ከሚያጋጥማቸው ቤተሰቦች ውስጥ ሁለት ሶስተኛዎቹ ከልደት እስከ ሶስት ዓመት ዕድሜ ልጆች ያላቸው ናቸው። ከእነዚህ የቤት እጦት ችግር ተመክሮ ካጋጠማቸው ውስጥም 60 ከመቶው የሚኖሩት በቤቶች 7 እና 8 (wards 7 እና 8) ነው።[23]

### ስንክልና ያላቸው ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦች

ስንክላና ላላቸው ግለሰቦች የሚሰጥ የትምህርት ህግ 2004 (The Individuals with Disabilities Education Act of 2004 (አይዲያ-IDEA)፤ ስንክልና ላለባቸው ልጆች ከተወለዱበት ዕለት ጀምሮ 21 ዓመት እስኪሆናቸው ድረስ ምን አገልግሎት እንደሚሰጣቸው በዝርዝር አስፍሯል።ይህ ህግ አያሌ ክፍሎች አሉት። ክፍል ለ እድሜአቸው ከ3 እስከ 21 በሆኑት ላይ ያተኩራል። ክፍል 619 ከ 3 እስከ 5 ዓመት ዕድሜ ጨምሮ የተዘጋጀ ሲሆን ክፍል ሐ ደግሞ ከተወለዱበት ዕለት ጀምሮ 2 ዓመት እስኪሆናቸው ድረስ ያለውን የሚመለከት ነው። ህጻናት ከተወለዱበት እለት ጀምሮ ሶስት ዓመት እስኪሞላቸው ድረስ ደግሞ ልዩ የሆነ ትምህርትም ሆነ ከትምህርት ጋር የሚዛመድ አገልግሎት የሚያስፈልጋቸው ከሆነ ለግላቸው ለተዘጋጀ የቤተሰብ አገልግሎት ፕሮግራም (individualized family service plan (IFSP) ወይም ከ ሶስት ዓመት ዕድሜ በላይ ለሆኑ ልጆች ለግል የተዘጋጀ ልዩ የትምህርት ፕሮግራም (individualized education program (IEP) ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። እነኚህን አገልግሎቶች ለማግኘት ብቁ የሆኑ ልጆች፤ ስንክልና/ስንክልናዎች ያሏቸው ወይም የዕድገት መጎተት/መዘግየት ችግር ያለባቸው ተብለው ሊመደቡ ይችላሉ። አንድ ልጅ፡ የእድገት መጎተት ወይም የዕድገት መዘግየት ችግር አለበት ሲባል ዕድገት በሚያሳዩት ትምህርቶች ቢያንስ 25 ከመቶ ወይም ከዛ በላይ መጎተት ሲያሳይ ነው።

ከታህሳስ ወር 2017 እስከ ታሕሳስ ወር 2018 የቀረበው የመንግስት ሪፖርት፤ በዲስትሪክቱ ውስጥ ያሉት 1,906 ልጆች ስንክልና ላለባቸው ግለሰቦች የሚሰጥ አገልግሎት የአይዲያ ( IDEA) ክፍል ሐ (ከልደት እስከ 2ዓመት ዕድሜ)ተቀባዮች እንደነበሩ ያሳያል። 1,759 ቱ ደግሞ የክፍል ለ (ከ3 ዓመት እስከ 5) አገልግሎት አግኝተዋል።[24]

### የማደጎ ልጆች( FOSTER) ያሏቸው ቤተሰቦችን የሚያግዝ ፕሮግራም

በ2017፤ ዕድሜያቸው ከልደት እስከ 5 ዓመት የሆኑ የማደጎ ልጆች ያሏቸው 177 ቤተሰቦች ከ**(ሲ-ኤፍ-ኤስ-ኤ CFSA)** ጋር ሰርተዋል። ይህም ከዛ በፊት ከነበረው በ16 ከመቶ ቀንሷል። ከእነዚህም 70 ከመቶው ዕድሜአቸው ከልደት እስከ 2 ዓመት ዕድሜ ያላቸው ናችው።

ከእነዚህም የሲ-ኤፍ-ኤስ-ኤ (CFSA)ልጆች ከግማሽ የሚበልጡት የሚኖሩት በቤቶች 7 እና 8 (wards 7 እና 8) ሲሆን አርባ ከመቶዎቹ ደግሞ መንግስት ለችግረኛ ቤተሰቦች የሚሰጠው እርዳታየ( TANF) ተቀባዮች ናቸው። 20 ከመቶው በደንብ እውቅናው የተመዘገበ የእድገት መዘግየት ችግር ያለባቸው ናቸው። በመሆኑም CFSA በቤቶች 7 እና 8፤ የአካባቢ የስራ ቡድን በማቋቋም የሚታገዙበትን መንገድ እያመቻቸ ነው።[25]

### የገቢ አለመመጣጠን

---

[21] District of Columbia Office of the State Superintendent of Education, 2017.
[22] DC Department of Human Services Economic Security Administration, 2017.
[23] District of Columbia Government Child and Family Services Agency, *FY2020 Needs Assessment and Resource Development Plan*, 2018.
[24] U.S. Department of Education, *40th Annual Report to Congress on the Implementation of the Individuals with Disabilities Education Act*, 2018.
[25] District of Columbia Government Child and Family Services Agency, *FY2020 Needs Assessment and Resource Development Plan*, 2018.

በዲስትሪክቱ፤ ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦች የሚያገኙት ዓመታዊ ገቢ አንዱ ከሌላው የማይመጣጠን መሆኑ በቀላሉ ሊታይ ይችላል። በዲስትሪክቱ ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦች አማካይ ገቢ በአንዳንዱ ቦታ ከ $24,000 በላይ፤ በሌላው ቦታ ደግሞ $200,000 በላይ ነው።[26] በቤት 8 (Ward 8) ከሁሉም ቁጥራቸው የበዛ፣ ዕድሜያቸው ከልደት እስከ 5 ዓመት የሆነ 8,061 ልጆች ይኖራሉ። ከዛ የሚመጡት በቤቶች 4፣ 5 እና 7[27]የሚቀመጡ ናቸው ። ይሁንና በቤት 8 (Ward 8) የሚኖሩ ቤተሰቦች፤ ከልደት እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦች ከሁሉም አነስተኛ የሆነ የ $24,749 ዓመታዊ ገቢ ያላቸው ናቸው።[28,29] የቤቶች 4፣ 5 እና 7 (Wards 4፣5 እና 7 ) ቤተሰቦች በአማካይ የ $101,869, $70,336 እና $31,130 ዓመታዊ ገቢ ያላቸው ናችው[30] ከዚህ ጋር በማነጻጸር ግን በቤት ሁለት (Ward 2) የሚኖሩ ከልደት እስከ አምስት ዓመት ዕድሜ የሚደርሱ 2,309 ልጆች ያሏቸው በጣም ጥቂቶች ቤተሰቦች፤ ዓመታዊ ገቢያቸው እስከ $182,019.[31] ይደርሳል። በዚሁ በ ቤት ሁለት(Ward 2) የሚኖሩ ከልደት እስከ አስራ ሰባት ዓመት ዕድሜ ልጆች ያላቸው ቤተሰቦች አማካይ ዓመታዊ ገቢ በ2000 ከነበረው $47,000፤ በ 2016 ከ $182,000 በላይ ከፍ ሲል በቤቶች 7 እና 8 (Wards 7 እና 8) የሚኖሩቱ እንዳለ ነው።[32]

**በዲስትሪክቱ ውስጥ ያለው የተለያየ የዘር ልዩነት**

በዲስትሪክቱ ከሚኖረው መላው ህዝብ አንድ አራተኛው፤ ከእንግሊዘኛ ቋንቋ ውጪ ሌላ ቋንቋ የሚናገር ነው። ዲስትሪክቱ ይህንን በመቀበልና እገዛ በማድረግ ብዙ ነገሮች በአያሌ ቋንቋዎች ለምሳሌ የአማርኛ ቋንቋ፡ የቻይና፣ የፈረንሳይ፣ የኮርያ፣ የስፓኒሽኛ፣ የቬየትናም ቋንቋዎችን የሚያጠቃልሉ ሌሎች አያሌ ቋንቋዎች ተተርጉመው እንዲቀርቡና የአስተርጓሚ አገልግሎቶችም እንዲኖራቸው አድርጓል።

በተጨማሪም፣ አያሌ የተለያዩ ቋንቋዎች የመኖር ብቻ ሳይሆን፡ አያሌ የዘርና የባህል ልዩነትም አለ። በዲስትሪክቱ በብዛት የሚገኘው ህዝብ ነጭ፣ ጥቁር አሜሪካውያንና የስጳኛ ተናጋሪዎችን ሲያጠቃልል፤ እነኚህ በብዛት በዲስትሪክቱ ውስጥ የሚገኙት በዲስትሪክቱ በእኩልነት የተሰራጩ አይደሉም።[33] በቤቶች 7 እና 8 (wards 7 እና 8 )፤ አብዛኛዎቹ ወይም ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው አፍሪቃውያን አሜሪካውያን ይኖራሉ። ነጮች በአጠቃላይ በብዛት የሚኖሩት በዲስትሪክቱ ሰሜናዊ ምዕራብ በኩል ሲሆን በ ቤቶች 2 እና 3 (wards 2 እና 3 ) ካሉት ተቀማጮች ውስጥ 65 ከመቶው ነጮች ናቸው። በ ቤቶች 7 እና 8 (wards 7 እና 8) [34] ግን ነጮች ከመቶ 5 ብቻ ናቸው። በአጠቃላይ ሲታይም፤ ግዜ ባለፈ ቁጥር በቤቶች 2 እና 4 (wards 2 እና 4) የሚኖሩ ነጮች ቁጥር እየጨመረ መጥቷል። በቤቶች 4 (Ward 4 ) የሚኖሩ አፍሪቃዊ አሜሪካውያን ቁጥር ግን ከ2011 እስከ 2016 ምንም ሳይጨምር በአብዛኛው እንደነበረው ነው። በቤቶች 2 (Ward 2 ) ደግሞ የሚኖሩ የአፍሪቃውያን አሜሪካውያን ቁጥር እየቀነሰ ሲመጣ ከ2011 እስከ 2016.[35] በቤቶች 7 እና 8 ( wards 7 እና 8) የሚኖረው የአፍሪቃዊ አሜሪካውያን ቁጥር ጨምሯል። በማወዳደር ሂስፓኒኮች ደግሞ በብዛት በዲስትሪክቱ ሰሜናዊ ክፍል በቤቶች 1 እና 4 (Wards 1 እና 4) የሚኖሩ ሲሆኑ ይህ ክፍል 35 ከመቶው ሂስፓኒክ ሲሆን ሌሎች ጎረቤት ቦታዎች ግን 20 ከመቶ ነው ሂስፓኒክ[36]

በዲስትሪክቱ ላሉት ወጣት ልጆች የተመጣጠነ ዕድል ለመስጠት በቤቶች ((wards) 7 እና 8 ከፍተኛ ትኩረት የሚያደርጉ ስራዎችን ተግቶ መስራት ያስፈልጋል።

***መሪ ጥያቄ:*** በዚህ ህዝብ ላይ የቀረበው መረጃ ደካማና ሃያል ጎን ምንድነው ?

**ግኝት 2 ለ፤ በአሁኑ ግዜ ዲስትሪክቱ ወቅታዊ የሆነ ልዩ የልጆች መለያ የለውም።** የተለያዩ ተቋሞች የተለያዩ መረጃዎችን ይሰበስባሉ፣ ያጠራቅማሉ ግን በተሰበሰቡት መረጃዎች ሁሉ ልጆችና አዋቂዎች በልዩ ሁኔታ የየግላቸው መለያ የላቸውም። እነኚህ ልዩ የህጻናት መለያዎች ፤ በተለያዩ ፕሮግራሞች ውስጥ የሚገኙትን መረጃዎች አንዱ ከሌላው ለማዛመድ ያስችላሉ። ልዩ መለያዎች ሲኖር ለልጆች የተሻሻለ አገልግሎት ለመስጠት፣ ቀልጣፋ ውጤት ለማስገኘት፣ የሚሰጠው አገልግሎት እንዳይደጋገም ለማድረግ፣ በበለጠ ትክክል የሆነ ክትትልና መረጃ እንዲኖር ለማድረግ ያግዛል።

---

[26] Kids Count Data Center, *Annie E. Casey Foundation, Median Income of Families with Children by Ward*, 2016.
[27] Kids Count Data Center, *Annie E. Casey Foundation, Population by Age Group by Ward: Under 5*, 2016.
[28] *Ibid*, https://datacenter.kidscount.org/data/tables/6747-population-by-age-group-by-ward#detailed/21/1852-1859/false/870,573,869,36,868,867,133,38,11/3933,214,838,123/13833.
[29] *Ibid*, https://datacenter.kidscount.org/data/tables/6747-population-by-age-group-by-ward#detailed/21/1852-1859/false/870,573,869,36,868,867,133,38,11/3933,214,838,123/13833.
[30] Kids Count Data Center, *Annie E. Casey Foundation, Median Income of Families with Children by Ward*, 2016.
[31] *Ibid*, https://datacenter.kidscount.org/data/map/6749-medianincome-of-families-with-children-by-ward#21/any/true/true/870/any/
[32] Kids Count Data Center*, Annie E. Casey Foundation, Median Income of Families with Children by Ward*, 2016.
[33] Kids Count Data Center, *Annie E. Casey Foundation, Race/Ethnicity of Total Population by Ward in District of Columbia*, 2016.
[34] Kids Count Data Center, *Annie E. Casey Foundation, Race/Ethnicity of Total Population by Ward in District of Columbia*, 2016.
[35] *Ibid*, https://datacenter.kidscount.org/data/tables/8875-race-ethnicity-of-total-population-by-ward#detailed/21/1852-1859/false/870,573,869,36,868,867,133,11/3498,2161,2159,2157,2663,3499,3307,2160|381/17763,17764.
[36] Kids Count Data Center, *Annie E. Casey Foundation, Race/Ethnicity of Total Population by Ward in District of Columbia*, 2016.

የሚቀርቡት ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች እንዲሁም የሚሰጡት ጠቀሜታዎች የተቀባዩን ህዝብ ፍላጎት የሚያንጸባርቁ መሆን አለባቸው። ሰው የት የት እንደሚኖር አነጥሮ ማወቅ፤ ምን ዓይነቶች ፍላጎቶች እንዳሉ ለማወቅ ጠቃሚ ቢሆንም፤ የዲስትሪክቱ ተቋሞችና ሌሎች ድርጅቶች አንድ ውሳኔ ላይ ለመድረስ፤ የቤቶችን ትክክለኛ ቦታዎችንና የአካባቢ ሁኔታዎችንም፤ ሁለቱንም፤ ግምት ውስጥ እንዲያስገቡ ሃሳብ ይቀርብላቸዋል። አያሌ የተደረጉ ጥናቶች፤ ሁኔታዎች በአካባቢ ዓይንም መታየት እንዳለባቸው ይጠቁማሉ።.[37,38,39]

***መሪ ጥያቄ: ይህንን መረጃ ለማሻሻል የሚደረግ አነሳሽነት አለን***?

**ግኝት 2 ሐ፤ ዲስትሪክቱ፤ የመረጃዎችን ጠቀሜታና ግንኙነት ለማሻሻል በስራ ላይ ያሉ ሶስት ዋና አነሳሽነት አለው።** እነኚህ የመረጃ አያያዝን፣ የመረጃዎች መለዋወጥንና ትብብርን ለማሻሻል የሚሰራባቸው ዋነኛ አነሳሽ ጉዳዮች፤ በዲስትሪክቱ ላሉት ከ ልደት እስከ 5 ዓመት ዕድሜ የሆኑ ህጻናት ልጆች ያላቸው ቤተሰቦች የሚሰጠው አገልግሎት በቅርብ የሚገኝና ጥራት ያለው እንዲሆን ያግዛል።

ከሚደረጉት አንሳሽነት አንዱ፤ የህጻናት የተባበረ የመረጃ ስርአት ( Early Childhood Integrated Data System (ECIDS) ነው። ይህንን ስርአት መልክ ለማስያዝ የመጀመርያው እርምጃ፤ በዲስትሪክቱ ያሉት መረጃዎች ሁሉ ጥቅም ላይ እንዲውሉ፤ ከተለያዩት የትምህርት ተቋሞች ያልተደጋገመ የቁጥር መረጃ እንዲሰበሰብ ማድረግ ነው። እነኚህን መረጃዎች ማግኘት ማለት ልጆችና ቤተሰቦቻቸው የሚያገኙትን አገልግሎት በማሻሻል በኩል መደረግ የሚገባው ቁልፍ እርምጃ መውሰድ ማለት ነው። ቢያንስ ያልተደጋገመ መረጃ የማግኘት ቀዳማይ ጥረት የስትሮንግ ስታርት (Strong Start)፣ የዲሲ የመጀመርያ ጣልቃገብነት ፕሮግራም( DC's Early Intervention Program (DC EIP)፣ የሄድ ስታርት( Head Start (HS) ፕሮግራሞችና በቅድመ-ትምህርት ያሉ ህጻናት ልጆችን መረጃ ባሉት የአካባቢ ተቋሞች((LEA) የሚሰበስብ ክፍለሃገር-አቀፍ የትምህርት መረጃ (Statewide Longitudinal Education Data (SLED)መረጃዎችን መሰብሰብ ነው። የልጆችን ቁጥር በሚመለከት ያለውን ያልተደጋገመ መረጃ መሰብሰብ፤ የሽግግር ወቅት ጥረቶችን ያግዛል፤ በ ኤችኤስ( HS) ፕሮግራም ውስጥ ከክፍል ለ ፕሮግራም ወደ ክፍል ሐ የሚሸጋገሩት ልጆችን ለማሸጋገር የሚረዳ የLEA መረጃ ይሰጣል። በተጨማሪም፤ ይህ መረጃ ዲስትሪክቱ፤ ልጆች ሌሎች ፕሮግራሞች ውስጥ መግባትና ተጨማሪ አገልግሎቶች ማግኘት የሚያስፈልጋቸው ከሆነ የትኞቹ እንደሆኑ ለይቶ ለማወቅ ያስችለዋል ብቻ ሳይሆን የሚወጣውን ዕቅድና ትብብርም እንዲሻሻል ያግዛል።[40] በመጨረሻም፤ የ ECIDS ዓላማ፤ ሙሉ በሙሉ ተግባር ላይ መዋል ሲጀምር፤ ህጻናት የሚገኙበትን አጠቃላይ ሁኔታ ሰዕላዊ መግለጫ መስጠት፤ በፕሮግራሞች መሻሻል ላይ ስትራቴጂካዊ የሆነ የገንዘብ ወጪ እንዲደረግ መፍቀድ፤ በሚነደፉት ፕሮግራሞች ያለው ቀዳዳ እንዲጠብ ማድረግ፤ በአጠቃላይም ልጆች ተገቢ የሆነ የጤና ጥበቃ፤ የአእምሮ ደህንነትና የዕድገት ምርመራና አገልግሎት እየተደረገላቸው ጥሩ ውጤት እንዲገኝ ማድረግ ነው። በዚህ ቀዳማይ ጥረት ያልተደጋገመ ሪፖርት የማዘጋጀት ጉዳይ ዲስትሪክቱ፤ በመረጃ አሰባበሰብ ላይ ቁልፍ የሆኑ አሰራሮችን ለማስተዋወቅና ለሚደረጉት ጥረቶች መሰረት ለመጣል ያስችለዋል።

ሁለተኛው ዋነኛ አነሳሽነት ደግሞ የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምብያ የመገናኝያ ስርአት (District of Columbia Access System (DCAS) ሲሆን ይህ ስርአት ዲስትሪክቱ ፤ የሜዲኬድ (Medicaid )፣ የሴቶች፣ የህጻናትና የልጆች እርዳታ ፕሮግራም (Women, Infants and Children (WIC ) ፣ የስናፕ(SNAP)፣ የTANF ፕሮግራሞችንና ሌሎች ፕሮግራሞችን በተገቢው መልካቸው ለማካሄድ መንገዱን ያመቻቹሉታል። ዲሲኤኤስ( DCAS)፤ ዋጋው ቀለል ባለው የጤና ኢንሹራንስ( Affordable Care Act (ACA) በሚያዘው መሰረት፤ አዲስ የጉዳዮች አስተዳደርና አሰራር በማስተዋወቅ፣ ተገልጋዮቹ ቤተሰቦች አድቫንስድ ፕሪሚየም የግብር አከፋፈል ብድር (Advanced Premium Tax Credit)እና የሜዲኬድ ብቁነት ለመመዘን የሚያስችል አገልግሎት (Modified Adjusted Gross Income Medicaid eligibility) ይሰጣሉ። በተጨማሪም አነስተኛ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦች የኤኮኖሚ ነጻነት እንዲያገኙ ያበረታታል። የዲሲኤኤስ (DCAS ) በስራ ላይ መዋል፤ የዲስትሪክቱን የረጅም-ግዜ የጤናና የማህበራዊ አገልግሎት ፕሮጀክቶችን ለማዋሃድ ይጠቅማል። ይህ ከተጠናቀቀ፤ዲሲኤኤስ (DCAS ) የዲስትሪክቱ ተቀማጮች የህክምና ፤ የገንዘብ፣ የምግብ ወይም የውሃና የመብራት ክፍያ እርዳታ ለማግኘት እንዲያመለክቱ ያደርጋል። ቅናሽ እንዲደረግ ወይም የቤት አልባነት አገልግሎት ወይም ሌሎች የጤናና የማህበራዊ አገልግሎት ጠቀሜታዎችን ለማግኘት ተቀማጮች በዘመናዊና በተራቀቀ መልክ ለማመልከት ይችላሉ።

በስራ ላይ ያለ ሶስተኛው ዋናው አነሳሽነት ደግሞ የትምህርት ዝግጁነትን በህዝብ ብዛት የሚለካ የዕድገት መሳርያ (Early Development Instrument (EDI)) ነው።[41] ይህ ኢ-ዲ-አይ (EDI) የተባለው አገባብ ከቅደመ-ትምህርት እስከ 4 ዓመት ዕድሜ

---

37 District of Columbia Government Child and Family Services Agency, *FY2020 Needs Assessment and Resource Development Plan*, 2018.
38 DC Policy Center, *Needs Assessment of Out-of-School Time Programs in the District of Columbia*, October 2017.
39 Georgetown University Center for Child and Human Development, *Maternal, Infant and Early Childhood Home Visiting Phase I Needs Assessment*, September 2016.
40 District of Columbia Office of the State Superintendent of Education, *District of Columbia Preschool Development Grant Birth to Five Application*, 2018.
41 Janus, M., & Offord, D. (2007). *Development and Psychometric Properties of the Early Development Instrument (EDI): A Measure of Children's School Readiness*. Canadian Journal of Behavioural Science, 39(1), 1-22. doi: 10.1037/cjbs2007001.

ያሉትን ህጻናት ይመለከታል። የዲሲኤኤስ (DCAS )ደግሞ ለማህበረሰቡ በሚቀርቡ ጥያቄዎች ላይ የተመረኮዘ ሆኖ አስተማሪዎች፤ አንድ ህጻን ልጅ ዕድሜው የሚፈቅደውንና የሚጠበቅበትን የእድገት ደረጃ ያሳያል ወይስ አያሳይም የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ይረዳቸዋል። ይሄው ኢዲአይ( EDI)ህጻኑ ልጅ ትምህርት ቤት ለመጀመር ዝግጁ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ አምስት ጉዳዮችን መመልከት እንዳለባቸው ይጠቁማል፤ ማህበራዊ ችሎታው፣ ቋንቋና የእውቀት ደረጃው፣ ስሜታዊ እድገቱ፣ አካላዊ ጤንነቱና ደህንነቱ፤ ከሌሎች ጋር የመገናኘት ችሎታውና ጠቅላላ እውቀቱ። ይሄው ኢዲአይ( EDI) በቅድመ- ትምህርት በ 294 የዲሲ የመንግስት ትምህርት ቤቶች፣ ቻርተር ት/ቤቶችና በፒኪፐ( PKEEP) ውስጥ በሲቢኦ( CBO) ክፍሎች ውስጥ ያሉ ወደ 4,000 የሚጠጉ ህጻናት ትምህርት ለመጀመር ዝግጁ መሆናቸውን አረጋግጧል።

## ክፍል 3 ግኝቶች

# አገልግሎት በማግኘት ላይ ያሉና አገልግሎት ለማግኘት ተራ የያዙ የልጆች ቁጥር

**መሪ ጥያቄ፤** ዲስትሪክቱ ባሉት ፕሮግራሞች በመገልገል ላይ ያሉት ልጆች ያልተደጋገመ ቁጥራቸውን በትክክል ለማግኘት የሚያግዘው ምን ዓይነት መረጃ አለው?

**ግኝት 3 ሀ. ዲስትሪክቱ፤ ዕድሜያቸው ከ ልደት እስከ 5 ዓመት የሆኑ ልጆች ያልተደጋገመ መረጃ መኖር እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ያውቃል።** ቀደም ሲሉ የነበሩት የዲስትሪክቱ የፍላጎት ግምገማዎች፤ የልጆችንና የአዋቂዎችን መረጃ ለይቶ ለማወቅ፤ የቃላትና አጠቃቀምና አገላለጻቸው በአንድ ዓይነት መለኪያ የተደረገ እንዲሆን እንዲሁም የተሳትፎ አለመደጋገም እንዲኖር ጥያቄ ሲቀርብባቸው ቆይቷል። ተደጋጋሚ ያልሆነ የልጆች መረጃ ለማግኘት በተደረገው ጥረት፤ የመረጃው ቅርጽና ሂደት ተጠናቋል። በመሆኑም ዲስትሪክቱ፤ ከልደት እስከ አምስት ዓመት ዕድሜ ያላቸው ልጆች ፕሮግራምና የአገልግሎት ምዝገባ መረጃን በተመለከተ የተዋሃደ የመረጃ ስርዓት እንዲኖር እየሰራ ነው። አገላለጾች አንድ ዓይነት እንዲሆኑና ተሳታፊዎች እንዳይደጋገሙ ማድረግ፣ ሕግና መመርያ አውጪዎች እንዲሁም የፕሮግራም አስተዳዳሪዎች፣ የፕሮግራሙ ተሳታፊዎች ደረጃና የእያንዳንዱ ፕሮግራም ውጤታማነትን በበለጠ እንዲረዱና የትኞቹ ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች ናቸው በበለጠ ውጤታማ የሆኑት የሚለውን ጥያቄ በበለጠ  ለመመለስ ይረዳቸዋል።

**መሪ ጥያቄ: በዚህ ቦታ ውስጥ ያለ ከፍተኛው የመረጃ እጥረት ምንን ይመስላል**?

**ግኝት 3 ለ፣  ከ 2019 የበልግ ወራት ጀምሮ፤ ዲስትሪክቱ ፤ ከልደት እስከ 5 ዓመት ዕድሜ ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦች የህጻናት መዋያዎችና የትምህርት ተቋሞች በቀላሉ የሚያገኙባቸው ዕድሎች እየጨመሩ እንዲሄዱ አስደናቂ ጥረቶችን ሲያደርግ ቆይቷል።** ዲስትሪክቱ፤ በ2019 የስራ ፈቃድ ባላቸው 470 የህጻናት መዋያዎች፤ ዕድሜያቸው ከ6 ሳምንት እስከ 13 ዓመት የሚሆኑ ከ25,000 በላይ ልጆችን አስተናግዷል። የህጻናት መዋያ ማግኘት ወይም ደግሞ ለህጻናት መዋያ የሚከፈለውን ገንዘብ መክፈል በዲስትሪክቱ ላሉ ቤተሰቦች ከባድ ሆኖ ቆይቷል። የአሜሪካ የጤና ጥበቃና የማህበራዊ አገልግሎት ሚኒስቴር በሰጠው መረጃ መሰረት፤ እንደደንቡ ከሆነ ለህጻናት መዋያ የሚከፈለው ገንዘብ ከቤተሰቡ ገቢ ከ7 ከመቶ መብለጥ የለበትም። ለ 3 እና 4  ዓመት ዕድሜ ልጆች የሚሰጠው ሁለንተናዊ እንክብካቤ  በዲስትሪክቱ ውስጥ ነጻ ነው።ይሁንና ቻይልድ ኬር አዌሮፍ አሜሪካ ( Child Care Aware of America) በሰጠው መረጃ መሰረት፤ በ 2017 በዲስትሪክቱ፣ በአማካይ ለህጻናት መዋያ በዓመት የተከፈለው ገንዘብ $22,658  ነበር። በብዙ ሁኔታዎችም ከትምህርት በፊትና ከትምህርት በኋላ ላሉት የህጻናት ማቆያ ቦታዎች፣ ለበጋ ማቆያዎች የሚከፈለው ወጪ፡ ለቤተሰቦች ሌላ ተጨማሪ ወጪ ነው። እንደ ኤችኤስ (HS) እና እርሊ ሄድ ስታርት( Early Head Start (EHS) የመሳሰሉት ፕሮግራሞች፤ ዕድሜያቸው ከልደት እስከ 5 ዓመት ለሆኑ ህጻናት ቤተሰቦችና ችግረኞች ለሆኑ ነጻ ትምህርትና ነጻ የእርዳታ አገልግሎት እንዲያገኙ ይሰራል።

የህጻናት ማቆያ ዋጋ ከፍተኛ ቢሆንም፤ ዲስትሪክቱ፤  በአገሪቱ ውስጥ ከፍተኛ ቅናሽ የሚያደርጉና የተከፈለ ወጪን የሚመልሱ ፕሮግራሞች ካሏቸው ተቋሞች ውስጥ አንዱ ነው።[42] ይሄ የከፍተኛ ቅናሽ ፕሮግራም፤ ቤተሰቦች ለትምህርት የሚያስፈልጋቸው ወጪን ሁሉ በመሸፈን ብቁ የሆኑ ቤተሰቦችን የሚያግዝ ፕሮግራም ነው።  ልዩ የሰራ ሁኔታ ያላቸው ቤተሰቦች፤ በተለይም እነኝያ ስራ መስራት የሚችሉ ግን ስራ የሌላቸው ችግረኛና በመንግስት የሚሰጥ የቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ (TANF ) እርዳታ ተቀባይ የሆኑ ቤተሰቦች ወይም በስልጠና ወይም በትምህርት ላይ ያሉና ገቢያቸው በዚህ ምክንያት የቀነሰ ቤተሰቦች፤በዚህ ፕሮግራም፤  በጣም ትንሽ ገንዘብ ከፍለው ወይም ሙሉ በሙሉ ነጻ የልጆች መዋያ ሊያገኙ ይችላሉ። ቅናሽ በሚያደርግ በዚህ ፕሮግራም ውስጥ የገቡ ደግሞ ከዓመታዊ ገቢያቸው 7 ከመቶ በላይ ለህጻናት መዋያ እንዲከፍሉ አይጠየቁም።

ይህ የሚደረገው የህጻናት መዋያ ቅናሽ ግንT በመላው ዲስትሪክት በእኩልነት የሚዳረስ አይደለም። ካሉት 10,052 የህጻናት ቦታዎች ውስጥ በትምህርት ዓመት 2018፣ 4,999 (ማለትም 50 ከመቶ) ቅናሽ በሚያደርጉ ፕሮግራሞች ወይም ነጻ ትምህርት በሚሰጡ ፕሮግራሞች ውስጥ የተጠቃለሉ ናቸው። (e.g., EHS).[43]  አነስተኛ ገቢ ያላቸው ከልደት እስከ 5 ዓመት ዕድሜ ልጆች ያሉዋቸው ቤተሰቦች በአብዛኛው የሚኖሩት በ ቤቶች( wards) 7 እና 8 ሲሆን በእነዚህም በ2018፤ ቅናሽ የሚያገኙት ቦታዎች ቁጥር 3,644 እና 5,387 ነበር። ሁለቱ ሲደመሩ፤ ከሌሎቹ ቦታዎች በሙሉ፤ አብዛኛውን ቁጥር ወይም ከፍ ያለውን ቁጥር ይዘው ይገኛሉ።[44] በ 2018

---

[42] Urban Institute, *Subsidy Policies and the Quality of Child Care Centers Serving Subsidized Children*, 2019.

[43] District of Columbia Office of the State Superintendent of Education, *FY19 Performance Oversight Questions: Capacity, Enrollment, Utilization FY17-FY19,* 2019.

[44] Bainum Family Foundation, *Early Learning Supply and Demand in the District of Columbia: Using Data to Identify Critical Gaps*, 2018.

በቤቶች( ward) 7 ከሚኖሩት ቤተሰቦች ከመቶ 96ቱ ፤ በቤቶች( ward ) 8 ከሚኖሩቱ ደግሞ ከመቶ 76 ቱ የቅናሽ እገዛ ሲያገኙ በቤቶች (ward) 4 የሚኖሩት ግን 62 ከመቶው (የሚቀጥለው ትልቁ ቁጥር) የቅናሽ እገዛ አገኙ።[45]

***መሪ ጥያቄ :*** አገልግሎት የሚያገኙ ልጆችን በተመለከተ የቀረበው የመረጃ ደካማና ሓይል ጎን ምንድናቸው?

**ግኝት 3 ሐ. ዲስትሪክቱ፤ ዕድሜያቸው ከልደት እስከ 5 ዓመት የሆኑና በህጻናት መዋያና በትምህርት ቤቶች የተመዘገቡ ህጻናትን በተመለከተ ሃብታም መረጃ ይሰበስባል፣ያስተዳድራልም።** ዲስትሪክቱ፤ ምንም እንኳን ፈቃድ ባላቸው የህጻናት መዋያ ውስጥ ስለተመዘገቡት ህጻናት በርካታና ሃብታም መረጃ ቢኖረውም፤ ከአጠቃላይ ከተመዘገቡት ውስጥ ጉዳት ሊደርስባቸው የሚችሉና ማግኘት ከሚገባቸው አገልግሎት በታች የሚያገኙ ህጻናት መረጃ እጥረት አለበት። በተለይም ዲስትሪክቱ፤ ቅናሽ ለማግኘት ብቁ ያልሆኑ ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦች እንዴት አድርገው ልጆቻቸውን በህጻናት መዋያ ውስጥ ለማስገባት እንደሚችሉ ሊረዳበት የሚያስችለው መረጃ የለውም።

ይህንን የመረጃ እጥረት በበለጠ ለመረዳትና መፍትሄ ለማስገኘት፤ (በግኝት 1 ሀ እንደተገለጸው)፤ የካፒታል ኳሊቲ ( Capital Quality) የሚያስከተለው ውጤት እንዲያድግ ማድረግ እጅግ አንገብጋቢ ነው። የኢ-ሲ-ኢን ( ECE)ጥራት ለማጎልበት የመግለጫዎች አንድ ዓይነት አገላለጽ፤ መረጃዎችን መሰብሰብ እንዴት እንደሚቻልና እንዴት የተሰበሰበውን መረጃ ማሰራጨት እንደሚቻል ያስተምራል።

## የተራ ጥበቃ ግዜ

የተራ ጥበቃ (Waitlists) በተቋሙና በትምህርት ቤት ደረጃ የሚያዝ እንጂ በዲስትሪክቱ የሚያዝ አይደለም። ቤተሰቦችም፡ በመረጡት አካባቢ የህጻናት መዋያዎች ውስጥ ቦታ እንዳለና እንደሌለ ለማወቅ ከፈለጉ፤ የዲስ የህጻናት መዋያ ( DC Child Care Connections (DC CCC)፣ የዲስቲክቱ የህጻናት መዋያ ምንጮችና ወደሌላ የሚመራ ስርአት( Child Care Resource and Referral (CCR&R) ጋር ተገናኝተው መጠየቅ አለባቸው። ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የተገኘ መረጃ እንደሚገልጸው፤ ቅናሽ የሚያስፈጋቸው አያሌ ቤተሰቦች፡ አስፈላጊውን ውሳኔ ለመወሰን የሚያስችላቸውን መረጃ ለማግኘት አይችሉም። ዲስትሪክቱ፤ ለሁሉም የሚዳረስ፡ በተራ ጥበቃ መቆየት ምን ያህል ጠቃሚ መሆኑን የሚያስረዳም ሆነ የት የት የተራ ጥበቃው እንዳለ የሚያሳውቅ መረጃ የለውም።

[45] District of Columbia Office of the State Superintendent of Education, *FY19 Performance Oversight Questions: Capacity, Enrollment, Utilization FY17-FY19,* 2019.

## ክፍል 4 ግኝቶች

# ጥራትና ቦታ መኖር

***መሪ ጥያቄ፤*** የአጠቃላይ የህጻናት መዋያዎችን ጥራት በተመለከተ የዲስትሪክቱ ወቅታዊ የኢ-ስ-ኢ( ECE) ሃያል ጎኖች ምንድናቸው ?

***ግኝት 4 ሀ. ዲስትሪክቱ፤ ቤተሰቦች ጥራት ያላቸው የህጻናት መዋያዎች ለሚሰጧቸው ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች እውቅና እንዲኖራቸው በእነዚህ በሚከተሉት መንገዶች ያረጋግጣል- የስራ ፈቃድ ክፍል( licensing) በሚከተላቸው መመርያዎችና ስርአቶች መሰረት የተጎላበቱ የልጆች የእድገት ተቋሞች፤ በቅናሽ የሚሰሩ (ECE) መማሪያዎች፤ ካፒታል ኳሊቲ( Capital Quality)፤ ዘ ኳሊቲ ኢምፕሮቭመንት ኔትወርክ ( Quality Improvement Network (QIN)፤ እርሊ ሄድ ስታርት- (ቻልይልድ ኬር ፓርትነርሺፕ (Early Head Start-Child Care Partnership (EHS-CCP)፤ የ MIECHV ፕሮግራም፤ ዘ ኣርሊ ለርኒንግ ኳሊቲ ፋንድ( Early Learning Quality Fund (ELQF) እና በአካባቢ የገንዘብ እርዳታ የሚካሄዱ የቤት ጉብኝት ፕሮግራሞች።*** ቀደም ሲሉ ከተጠቀሱት እርዳታ ሰጪዎችና ፕሮግራሞች በተጨማሪ፤ ከልደት እስከ 5 ዓመት ዕድሜ የሆኑና የእድገት መጎተት ችግር ወይም ስንክልና ያለባቸው ልጆች ቤተሰቦች፤ ከአይዲያ ክፍል ሐ እና ክፍል ለ እርዳታና አገልግሎት እንዲሁም ፕሮግራምና ምንጮችን ለማግኘት ብቁ ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ፤ ከ ስድስት እስከ 11 ሰዓታት የሚቆይ የልጆች እንክብካቤ የሚያደርጉ፤ በቀን ከ ስድስት ሰዓታት ያነሰ ቆይታ የሚሰጡ ወይም ሙሉ ዓመት የሚዘልቅ መዋያ የሚሰጡና የቤተሰቦችን ምርጫ የሚያከበሩ ፤ ፈቃድ ያላቸው 470 የህጻናት መዋያዎች አሉ።[46]

***ግኝት 4 ለ. ቤተሰቦች፤ በዲስትሪክቱ ያሉትን የህጻናት ልጆቻቸውን መዋያዎች ጥራት ለመገምገም፤ በካፐታል ኳሊቲ ( Capital Quality) በተወከሉት በማይ ቻልድ ኬር ዲሲ ዌብሳይት(My Child Care DC) ዌብሳይት ውስጥ በመግባት ሊያውቁ ይችላሉ።*** በግኝት 1 ሀ እንደተገለጸው፤ ካፒታል ኳሊቲ( Capital Quality) ፍቃድ ባላቸው መዋያዎች ውስጥ የሚሰጠው የትምህርት ፕሮግራም ጥራት ምን ላይ እንዳለ ይገመግማል። ይሄው ማይ ቻይልድ ኬር ዲሲ( My Child Care DC) ዌብሳይት፡ በዲስትሪክቱ ውስጥ ፍቃድ ስላላቸው የህጻናት መዋያዎች ለቤተሰቦች አስፈላጊ መረጃዎችን ይሰጣል። በአጠቃላይም፤ የህጻናት ልጆች ዕድገት ተቋሞች ምን ዓይነት አገልግሎቶችን ነው የሚሰጡት፤ በቅናሽ አገልግሎት ለማግኘት የሚሰጡ ኩፖኖችን ይቀበላሉ ወይስ አይቀበሉም፤ በማህበረሰቡ የተቀባይነት ደረጃቸው ምን ያህል ነው፤ የስራ ፍቃድ የሚሰጠው አካል የሰጠው አስተያየት ምንድነው፤ በተጨማሪም በአገልግሎት ተቀባዩ ህዝብ የሚሰማ በሃቅ የተመሰረተ ምን ቅሬታ አለ የሚሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል። በካፒታል ኳሊቲ (Capital Quality) የተሰጡ አስተያየቶችንም ማየት ይቻላል። በ ማይ ቻይልድ ኬር ዲሲ (My Child Care DC ) ዌብሳይት የሰፈረው በርካታ መረጃ ፤ ወላጆች/ቤተሰቦች በአካባቢያቸው ስላሉ የልጆች ዕድገት ተቋሞችና መዋያዎች፤ አጠቃላይ ሰዕል እንዲኖራቸውና ልጆቻቸውን የት እንደሚያስገቡ በእውቀት ላይ የተመረኮዘ ውሳኔ ለመወሰን ይረዳቸዋል።

***መሪ ጥያቄዎች:*** ለእነኝያ ለአደጋ የተጋለጡ ናቸው ለሚባሉትና የሚያገኙት አገልግሎች ማግኘት ከሚገባቸው በታች ነው የሚባሉት ህጻናት ልጆች ጥራት ያለው አገልግሎት እንዲያገኙ ለማድረግ ምን ዓይነት ዕቅድ በመካሄድ ላይ ይገኛል? ይህንን በተግባር ለማወል ደግሞ ምንድነው የሚሰራው?

***ግኝት 4 ሐ. ዲስትሪክቱ፡ በመላው ዲስትሪክት ያሉ፤ ዕድሜያቸው ከልደት እስከ 5 ዓመት የሆኑ ህጻናት፤ ቀጣይና ጥራት ያለው አገለግሎት እንዲያገኙ ከፈተኛ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል።*** ዲስትሪክቱ በቅድመ ትምህርት ለተመዘገበ እያንዳንዱ ልጅ የሚያወጣው ገንዘብ በመላይት አገር የመጀመርያ ከፍተኛውን ደረጃ የያዘ ሲሆን ለቅደመ-ትምህርት አገልግሎት የሚያወጣውም ወጪ እንዲሁ ከመላይቱ አገር የቀዳማይ ደረጃ የያዘ ነው። ለአደጋ የተጋለጡ ናቸው ለሚባሉትና የሚያገኙት አገልግሎት ማግኘት ከሚገባቸው በታች ነው ለሚባሉት ህጻናት ልጆችም የሚያደርገው ባለ ብዙ ዘርፍ እገዛ፤ ገና ከተወለዱበት ዕለት ጀምሮ ቅድመ-ትምህርት እስኪገቡ ድረስ ቀጣይ ነው።

---

[46] District of Columbia Office of the State Superintendent of Education, Division of Early Learning, *The Child Care Licensing Unit Report*, September 2019.

### ሁለንተናዊ የቅድመ-ትምህርት ፕሮግራም

በ 2016-17 የትምህርት ዓመት፤ ዲስትሪክቱ፤ ለ5,968 የ3-ዓመት ዕድሜ ህጻናት ልጆችና(ለ69 ከመቶ የ3-ዓመት ዕድሜ ህጻናት ልጆች) ለ7,186 የ 4-ዓመት ህጻናት ልጆች (ለ89 ከመቶ የ 4ዓመት ዕድሜ ህጻናት) ሁለንተናዊ የቅድመ-ትምህርት አገልግሎት በተለያዩ መንገዶች ሰጥቷል። (ይሄውም በመላው የዲሲ የመንግስት ትምህርት ቤቶች በኩል፣ በፒኪፒ (PKEEP)በተወከሉ በሲ-ቢ-ኦ (CBO) ቻርተር ትምህርት ቤቶች)።[47] በ 2017-18 የትምህርት ዓመት ደግሞ 13,492 ልጆች በሶስቱም የትምህርት ክፍሎች የሁለንተናዊ ቅድመ ትምህርት ዕድል እንዲያገኙ ሲደረግ ከእነዚህ ውስጥ 85 ከመቶ የ 4ዓመት ዕድሜ ህጻናት፣ 73 ከመቶ ደግሞ የ 3 ዓመት ዕድሜ ህጻናት ልጆች ናቸው።[48]

ድስትሪክቱ ለሁለንተናዊ የቅድመ ትምህርት ፕሮግራም ከሚያደረገው ወጪ በተጨማሪ፤ በየመንግስት ትምህርት ቤቱ የሄድ ስታርት( Head Start School-wide Model (HSSWM))ፕሮግራም ጀምሯል። ይህም በማእከላይ መንግስቱና በአካባቢ ወጪ የሚተዳደር ሲሆን፤ ከሁለቱ ምንጮች የሚገኘው ገንዘብ፤ በሄድ ስታርት( Head Start) ፕሮግራም ለመሳተፍ ብቁ ናቸው ወይስ አይደሉም የሚለው የብቁነት መለከያ ሳይደረግ በሁሉም ፕሪኬ-3 (pre-K 3) እና ፕሪ- K 4 (pre-K 4) ባላቸው የ ታይትል አንድ ትምህርት ቤቶች መካከል በእኩልነት እንዲከፋፈልና ሁሉም የጤና፡ የምግብ፡ የአእምሮ ጤንነትና የቤተሰብ ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል።

### በቅናሽ የሚካሄድ የህጻናት የትምህርት( ECE) ፕሮግራም

በግኝት 3 ለ ላይ እንደተገለጸው፤ ከልደት እስከ 5 ዓመት ዕድሜ ላላቸው ህጻናት ልጆች፤ ዲስትሪክቱ የሚያካሂደው ፕሮግራም ቁልፍ ሃያል ጎን፤ በዋጋ ቅናሽ የሚካሄድ መሆኑና ደረጃ በደረጃ የሚደረግ የማወራረድ ክፍያ (tiered reimbursement) ትኩረቱ አቅም ለሌላቸው ቤተሰቦች ፍትሃዊ የሆነ ዕድል ለመስጠት መስራቱ ነው። በ2017 የትምህርት ዓመት፤ ዕድሚያቸው ከልደት እስከ 5 ዓመት የሆኑ 9,400 ህጻናት ልጆች ቅናሽ ተደርጎላቸው ነው አገልግሎት ያገኙት። በገቢ መጠን ሲለካም ( ለምሳሌ ለጉዳት የተጋለጡ ተብለው በግኝት 1 ሀ ከተሰየሙት) በዲስትሪክቱ ውስጥ ካሉት ዕድሜያቸው ከልደት እስከ 5 ዓመት የሆኑ 16,618 ልጆች ነበሩ ቅናሽ ለማግኘት ብቁ የነበሩ።[49]

ዋጋዎችን ለማስተካከል በተደረገ ጥናት፡ ዲስትሪክቱ፤ ቅናሽና ማወራረድን በተመለከተ ከመላው አገር እጅግ ከፍተኛውን ደረጃ ይዞ ይገኛል።[50] የማህበራዊ አገልግሎት ሚኒስቴር ( Department of Human Services (DHS) ማለትም ከተለመደው የስራ ሰዓታት ውጪ (ማለትም ከጥዋቱ 7 ሰዓት እስከ ማታ-6 ሰዓት፣ ከሰኞ እስከ ዓርብ) ለሚሰሩ ቤተሰቦች የህጻናት መዋያ ክፍያ ቅናሽ በማድረግ ልጆቻቸው በእነዚህ መዋያዎች እንዲሳተፉ ያደረጋል። በ2017 የቻይልድ ኬር ጥናት ( Child Care Study Act) ህግ መሰረት ያልተለመደ ሰዓት ወይም ከተለመደው ሰዓት ውጪ ሲባል ከ ጥዋቱ 7 ሰዓት እስከ 6 ሰዓት እጪ ከሰኞ እስከ ዓርብ ማለት ነው። ይህ 24-ሰዓት ሙሉ የሚቆይ ማቆያንም ያጠቃልላል።

### ግኝት 4 መ፤ የጥራት መለከያ ኔትወርክ (QIN) ችሎታን ይገነባል፡ በጉዳዩ የሚሳተፉት ሁሉ ጥራት እንዲኖራቸው ያበረታታል

የ2015 የጥራት መለከያ ማሻሻያ ህግ (The Early Learning Quality Improvement Network Amendment A (QIN Act) ቤተሰቦች ቅናሽ የሚያገኙበትን መንገድ ለመፈለግ ከ ኢ-ኤች-ኤስ (EHS ) ብቁነት ማረጋገጭ ውስጥ በማለፍ አጠቃላይ ቀጣይና ጠንካራ የቴክኒክ እገዛ (TA)ና የባለሙያዎች ስልጠና (professional development (PD)ይሰጣል።

ዲስትሪክቱ፤ ከአካባቢ፣ ከ ማእከላይ መንግስት እንዲሁም ከግል ድርጅቶች የሚገኘውን የገንዘብ አበርክቶ፤ በ QIN በኩል የሚገኘውን የቲኤ( TA) እገዛንም ጨምሮ፤ ጥራት ያለው፣ ቀጣይና ሁለንተናዊ የሆነ አገልግሎትና ስልጠና ለመስጠት ጥቅም ላይ ያውለዋል። ከ2014-2019 ፤ ዲስትሪክቱ ለ16 የህጻናት ልጆች የዕድገት ተቋሞች እንዲሁም ለ19 የቤት ውስጥ የህጻናት ዕድገት ቤቶች የገንዘብ አበርክቶ እርዳታ በመስጠት በአጠቃላይ ከ600 ለሚበልጡ ልጆች አገልግሎት ሰጥቷል። የሄድ ስታርት የስራ መመዘኛዎች (Head Start Program Performance Standards (HSPPS)ንና በጥናት ላይ የተመሰረቱ አሰራሮችን በመጠቀም፤ እነኚህ ማእከሎች፤ አስተዳዳሪዎች፣ አስተማሪዎች፣ በህጻናት ልጆች የእድገት ተቋሞች ውስጥና በቤቶች ያሉ ልጆችና ቤተሰቦቻቸውን ለመርዳት ባለሙያዎችን ይቀጥራሉ። ይህ እርዳታ ለልጆችና ቤተሰቦች ስልጠናና አጠቃላይ አገልግሎት የቤተሰቦች ትኩረትና እገዛ፣ ጤንነትና አመጋገብ፣ እንዲሁም የአእምሮ ጤነነትና ጣልቃ ግብነት እገዛ በመስጠት ላይ ያተኩራል። ተቋሞቹ፤ ቅነሳን የሚቀበሉ ሲሆኑ በቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ( TANF) የሚሳተፉ፣ የማደጎ ልጅ ያላቸው ቤተሰቦችና የቤት-አልባነት ተመክሮ ያሳልፉ፤ የእድገት መጓተት የሚያሳዩ ወይም ስንክልና ያላቸው ልጆችም ጥራት ያለው ትምህርት እንዲያገኙ በቀጣይነት ይሰራሉ።

---

[47] District of Columbia Office of the State Superintendent of Education, *Fiscal Year 2017 Pre-K Report*, 2017.

[48] A.H. Friedman-Krauss, W.S. Barnett, K.A. Garver, K.S. Hodges, G.G. Weisenfeld, & N. DiCrecchio. *The State of Preschool 2018: State Preschool Yearbook*. New Brunswick NJ: National Institute for Early Education Research, 2018.

[49] District of Columbia Office of the State Superintendent of Education, *District of Columbia Preschool Development Grant Birth to Five Application*, 2018.

[50] District of Columbia Office of the State Superintendent of Education, *Modeling the Cost of Child Care in the District of Columbia*, 2018.

አያሌ የዲስትሪክቱ ተቋሞች፤ የዲሲ የጤና (DC Health )፡ የጠባይ ጤንነት ክፍል (Department of Behavioral Health (DBH)፣ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴርየገንዘብ ክፍል (Department of Health Care Finance (DHCF)፣ ዲ-ኤች-ኤስ-ኤስ( DHS) እና ሲ-ኤፍ-ኤስ-ኤ( CFSA)፣ በኪው-አይ-ኤን( QIN) የተመዘገቡ ልጆችና ቤተሰቦች ውጤታማ የሆነ አገልግሎት እንዲያገኙ ይተባበራል።ገና ልጅ ያልወለዱ ግን ነፍሰጹር የሆኑ እናቶችም ከጸነሱበት ቀን አንስቶ እርዳታ ያገኛሉ። በትምህርት ዓመት 19፤ የመንግስትና የአካባቢ የገንዘብ አበርክቶ ስለጨመረ ዲስትሪክቱ ኪው-አይ-ኤን( QIN)ን አምስት የህጻናት ተቋሞች እንዲጨምር አስችሏል።

**ግኝት 4 ሰ፤ በ ግኝቶች 1 ሀ እና 4 ለ እንደተገለጸው፤ በዲስትሪክቱ ውስጥ ከልደት እስከ አምስት ዕድሜ ላላቸው ልጆች ጥራት ያለው እንክብካቤ ለማድረግ ካፒታል ኳሊቲ (Capital Quality )ቁልፍ ነው።** የፕሮግራሙ ዓላማ በዲስትሪክቱ ያሉት ልጆች በሙሉ ተገቢ በሆነና ጥራት ባለው ተመክሮ እንዲያልፉ ማገዝ ነው። ካፒታል ኳሊቲ ፕሮግራምም( Capital Quality program) ፤ ማህበራዊና ስሜታዊ ደህንነት በማሻሻል፣ ኤኮኖሚያዊ ዕድሎች እንዲገኙ በማድረግ፤ ቤተሰቦችና መምህራን ገንዘባዊ እርጋታ እንዲያገኙ በማገዝ፤ የትምህርት ዕድገትን በማሻሻልና ለጉዳት በቀላሉ ለመጋለ የሚችሉና ከሚገባቸው በታች አገልግሎት ሲያገኙ ለቆዩት ልጆች ጥሩ የሆነ የትምህርት ስርአት እንዲፈጠር ያግዛል።

**ግኝት 4 ሸ፤ ሲ-ቢ-ኦ (CBO) ከ ፒ-ኪፐ (PKEEP) እና ከኢ-ኤች-ኤስ/ኤች-ኤስ( EHS/HS) ፕሮግራሞች ጋር በመተባበር ለጉዳት የተጋለጡና ከሚገባቸ እው አገልግሎት በታች ሲያገኙ የቆዩትን ልጆች ያገለግላል።** በግኝት 1 ሀ እንደተገለጸው የፒኪፐ( PKEEP) ውክልና ያገኙ ሲ-ቢ-ኦ ዎች (CBOs) በሁለንተናዊ መዋእለ-ህጻናት በፊት ላሉ ተቋሞች ነጻ ቦታ ይሰጣሉ። የፒኪፐ( PKEEP) አንደኛው የብቁነት ጥያቄ፤ ሲ-ቢ-ኦ ዎች (CBOs) ብቁ ሁነው ለተገኙ ለልደት እስከ አምስት ዓመት ዕድሜ ላላቸው ልጆች የክፍያ ቅናሽ ለመቀበል መስማማት ነው። በትምህርት ዓመት 2018፡ በህዝባዊ ቻርተር ትምህርት ቤት ካሉት 49 ከመቶ ልጆች፤ በዲሲ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ካሉት 44 ከመቶ የቅድመ ትምህርት ልጆች ይበልጥ በፒኪፐ( PKEEP) ውክልና ባገኙ በሲ-ቢ-ኦ ዎች (CBOs) የተገለገሉ 52 ከመቶ የሚሆኑ ልጆች ለአደጋ የተጋለጡ መሆናቸው ተመዝቧል።[51] [52]

ኢ-ኤች-ኤስ/ ኤች-ኤስ (EHS/HS) የማእከላዊው መንግስት ፕሮግራም ሆኖ አነስተኛ ገቢ ላላቸው ቤተሰቦች የትምህርት እርዳታ የሚሰጥ ነው። በዲስትሪክቱ ያሉ አምስት የገንዘብ አበርክቶ አድራጊዎች ለነፍሰጹር ሴቶችና በ ኢ-ኤች-ኤስ( EHS) ብቁነታቸው ለተረጋገጠ ህጻናትና ልጆች አጠቃላይ አገልግሎትና እገዛ ያደርጋሉ።

ግኝት 4 ረ፤ **የዲስትሪክቱ ተቋሞች፤ ዕድሜያቸው ከልደት እስከ አምስት ዓመት የሆኑ ለጉዳት የተጋለጡና ማግኘት ከሚገባቸው አገልግሎት በታች የሚያገኙ ህጻናትን ለማገዝ የተለያዩ ፕሮግራሞች አሏቸው።** እነኚህም ጠባይ፣ ማህበራዊና ስሜታዊ ጤንነት፣ የአእምሮ ጤንነት፣ የዕድገት መዘግየት ወይም ስንክልና ያለባቸው፤ የተቋሞች መሻሻል፤ ጤንነትና ደህንነት፣ አስቀድሞ የመጠንቀቅ እገዛ፡ ወደ ሌላ ባለሙያዎች ማስተላለፍ ወላጆችና ቤተሰቦች የልጆቻቸውን ትምህርት በተመለከተ ተሳትፎአቸው እንዲጨምር ማድረግ የመሳሰሉ ፕሮግራሞች ማቀናበርና ማካሄድ። በዲስትሪክቱ ውስጥ ያሉት ግለሰቦች ማድረግ ስለሚገባቸው ተጨማሪ መረጃ ከተፈለገ ግለሰቦች በተጨማሪው ገጽ ለ (Appendix B. ) ማየት ይቻላል።

***መሪ ጥያቄ*** **:** ምን በተሻለ ነበር?

**ግኝት 4 ሸ. ለንጭ እናቶችና ህጻናት ከሚያጋጥማቸው በላይ፤ ለጥቁሮች፡ ሂስፓኒክ ላልሆኑ እናቶችና ህጻናት ከመወለዳቸው በፊት ጀምሮ ወድያውኑ እንደተወለዱ መጥፎ ውጤት ያጋጥማቸዋል።** በዲስትሪክቱ ውስጥ ከ 2012-2016፤ ከነጭ እናቶች ከተወለዱ ህጻናት ይልቅ፤ ከጥቁሮችና ሂስፓኒክ ካልሆኑ እናቶች የተወለዱ ህጻናት የመሞት ብዛት አምስት እጥፍ ነበር።[53] በተመሳሳይም የህጻናት የመሞት ደረጃ፡ ከነጭ እናቶች ከተወለዱት ህጻናት 2.55 ከመቶ ሲሞቱ፤ ከጥቁሮች፡ ሂስፓኒክ ካልሆኑ እናቶች የተወሉዱ ህጻናት ከመቶ 11.49 ይሞታሉ። የሂስፓኒክ እናቶች ህጻናት ደግሞ ከመቶ 5.33 ይሞታሉ።[54] ፔሪኔታል ሄልትና የህጻናት የሞት ሪፖርት (Perinatal Health and Infant Mortality Report) እንደሚያስረዳው ዲስትሪክቱ፤ ከጽንስ በፊት ያለውን የእናቶችን ጤንነት

---

[51] A student is identified as at-risk for academic failure if the student is identified as any one of the following: (1) whether a student is identified as having received (or is currently receiving) support from a number of assistance programs, including the Temporary Assistance for Needy Families (TANF) or Supplemental Nutrition Assistance Program (SNAP); (2) whether a student is (or ever was) a ward of the state under the Child and Family Services Agency (CFSA); or (3) whether a student was ever identified as experiencing homelessness.

[52] Office of the State Superintendent of Education, *Fiscal Year 2018 Pre-K Report*, 2018.

[53] District of Columbia Department of Health, *Perinatal Health and Infant Mortality Report*, 2018.

[54] *Ibid*, p. 52.

ለማሻሻል አንድ ዓይነት የእንክብካቤ ስርአት መመስረት እንዳለበት፤ ህጻን ከመወለዱና ልክ ሲወለድ የሚያጋጥም እክልን መፍታት፤ የመውለድ ግዜ ሳይደርስ ሊያጋጥም የሚችል መውለድን በተቻለ መጠን ማስወገድ መቻል እንዳለበት ይጠቁማልይህንን የሚቋቋሙ ፕሮግራሞች ቢኖሩም፤ እናቶችን ወይም ወላጆችን እንዲህ ዓይነቶቹ ፕሮግራሞች እንዳሉ በግልጽ የሚያስረዳ ለሁሉም የሚዳረስ የማስራጭያ መንገድ የለም።

ጤንነትን በተመለከተ ያለውን ልዩነት ለመቀነስ፤ የከንቲባው ጽህፈት ቤት፤ ለነፍሰጹር እናቶችና አዲስ እናቶች እንዲሁም ለህጻናት ልጆቻቸው የተዘጋጁትን ፕሮግራሞችና የፕሮግራሞችን ጥራት ለማሻሻል እርምጃዎችን እየወሰደ ነው። እነኚህ ፕሮግራሞችም የ እናቶችና የህጻናት ጤንነትን የሚመለከቱ በትራቭ ባይ ፋይቭ ዲሲ (Thrive by Five DC) የሚካሄዱ ዓመታዊ ስብሰባዎች( Maternal and Infant Health Summit ) ን ያጠቃልላሉ። እነኚህ ስብሰባዎችም የእናቶች ጤንነት እንዲሻሻል ስለሚያግዙ ፕሮግራሞች መረጃ ይሰጣሉ።

ግኝት 4 ቀ፤ ዲስትሪኩቱ፤ በኢጋዥ ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች ሃብታም ቢሆንም፤ ቤተሰቦች ግን ስለነዚህ ያሉት ዕድሎች ያላቸው እውቀት የተወሰነ ነው። ስለነዚህ ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች ያለው መረጃ በብዙ የተለያዩ ቦታዎች የሚገኝ እንጂ አንድ ሁሉንም አቀናብሮ የያዘ መረጃ የለም። የፒ-ዲ-ጂ ( PDG) የቤተሰብ ጥናት እንዳመለከተው፤ የተለያዩ የህጻናት ፕሮግራሞች፤ አገልግሎቶችና ጠቀሜታዎችን በተመለከተ ያለው መረጃ በጣም ሰፊ ነው። ከፍተኞቹ የመረጃ ምንጮች ሁለት ናቸው። አንደኛው ጓደኛ፣ጎረቤት፣ የስራ ጓደኛ፣ ወይም ከህጻኑ ሃኪም ቤት ጽህፈት ቤት((ከሙቶ 24) መረጃ ይገኛል። ሌላው የጠቀሜታ መረጃ ሄልፐ ሚ ግሮ ዲሲ(Help Me Grow DC) ከተባለው ድርጅት ነው ይህም ከሙቶ 35 ይሆናል  ወይም ከቤተሰብ አባል (24 ከሙቶ).[55] ነው። በስብሰባዎች ከተካፈሉት ውስጥ አንዳቸውም ስለሁሉም ነገር- ህጻናት ልጆችን ስለሚጠቅሙ ፕሮግራሞች ሆኑ  አገልግሎቶች አንድ የተጠቃለለና የተሟላ መረጃ የላቸውም። በወቅቱም ቤተስቦች በአንድ የተጠቃለለ ኤል-ኢ-ኤ(LEA)፣ኢ-ሲ-ኢ (ECE ) ተቋሞችንም የሚጨምር፡ የጤና ሁኔታና አገልግሎት፣ እንዲሁም የገንዘብ እርዳታ የትና እንዴት እንደሚገኝ የሚጠቁም መረጃ በየቦታው ተበታትኖ ሳይሆን አንድ ላይ ተጠቃሎ በአንድ መረጃ ውስጥ ቢዘጋጅ ምንኛ ደስተኞች እንደሚሆኑ አስረድተዋል።

### የወላጆች አስተያየት

በ2019 በጸደይና በበጋ ወራት ከቤተሰቦች ጋር የተደረጉ ስብሰባዎች፤ ቤተሰቦች አንድ ውሳኔ ሲወስኑ ከምን ተነስተው መሆኑን አስፈላጊ መረጃ እንድናገኝ ከማድረጋቸውም በላይ ቤተሰቦች በሚሰጡት ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች ምን ያህል ደስተኞች መሆናቸውን ለማወቅ አስችለውናል። ሆኖም ግን ቤተሰቦች ብዙ የትምህርት ምርጫ( ECE) ስለሌላቸው ቅሬታቸውን ገልጸዋል። ገብያቸው አነስተኛ የሆነና በቤቶች( wards) 6፣ 7 እና 8 የሚኖሩ ቤተሰቦች፤ በሌሎች ቤቶች ከሚኖሩት በበለጠ ብዙ የትምህርት( ECE) ምርጫ እንደሌላቸው ቅሬታቸውን ያሰማሉ። ቤተሰቦች ልጆቻቸውን ወደ ቅድመ ትምህርት ለማስገባት፤ በተለይም ጥራት ወደላቸው የቅድመ ትምህርት ቦታዎች) ለማስገባት ረጅም የተራ መስመር፤ የረጂም ግዜ ጥበቃ እንዳለ ያስረዳሉ። ወላጆች " ጥራት ያለው" ሲሉ አንዱ ከሌላው የተለያየ ቢሆንም በ አጠቃላይ ግን የሚከተሉትን ማለታቸው መሆኑን አስረድተዋል፣  ንጽህናው የተጠበቀ፣ በቂ የመንቀሳቀሻ ቦታ ያለው፣አስተማሪዎች ከልጆቹ ጋር ያላቸው ቅርበት፣ የሚሰጣቸ እው የትምህርትና የጨዋታ አይነት ከዛ በተረፈ ደግሞ ልጃቸው "በእኩልነት ለመሳተፍ" ችሏልን የሚሉት ይገኙባቸዋል። አብዛኛዎቹ ቤተሰቦች ልጆቻቸው የሚሄዱባቸው መዋያዎች ጥራት ያላቸው መሆናቸው እጅግ አስፈላጊ ነው ይላሉ። ሌሎች ቤተሰቦች ግን ልጆቻቸውን የት ለማስገባት የመምረጥ ዕድል እንደሌላቸው ይገልጻሉ። ጥራት ይኑረው.አይኑረው፣ ለስራቸው ወይም ለቤታቸው ቅርብ ወደ ሆነው ብቻ ነው ሊያመሩ የሚችሉት።

***መሪ ጥያቄዎች፤*** ወላጆችና የቤተሰብ አባሎች  የልጆቻቸውን ትምህርት በተመለከተ የሚያደርጉትን ተሳትፎና ተካፋይነት ለማጠናከር ዲስትሪክቱ፤ ምን የምያደርገው አለ? ውጤታማ የሚሆነው ደግሞ የትኛው ነው?

**ግኝት 4 በ. ከኪው-አይ-ኤን ( QIN ) እና ከ ቢ ስትሮንግ ቤተሰቦች( Be Strong Families) ጋር በመተባበር፤ የቤናም ፋሚሊ ፋውንዴሽን (Bainum Family Foundationለመመስረት )፣ የበጎ አድራጎት ድርጅት፣ የወላጆች ካፌ በመምስረት ግንባር ቀደምትነቱን ይዟል።** እነዚህ የወላጆች ካፌ ወላጆችን ትኩረት የሚስቡና ወላጆችን የሚያጎለብቱ አገር-አቀፍ ድርጅቶች ናቸው። በዚህም የቤተሰቦች ድምጽ እንዲሰማ፤ወላጆች በልጆቻቸው ትምህርት ያላቸው ተካፋይነት እንዲጠናከር የሚያደርጉ የተለያዩ ባህሎችንና ቋንቋዎችን ግምት ውስጥ የሚያስገቡ ፕሮግራሞችን ያስተዋውቃል።እነኚህም፤

1) የልጆቻቸውን የእድገት ፕሮግራሞች እንዲዲደግፉ የሚያስችላቸውን ዕውቀት እንዲገበዩ
2) ከወላጆች ካፌዎች የሚገኙ መረጃዎችን መሰብሰብና ጥቅም ላይ ማዋል
3) ማህበራዊ ግንኙነቶችን መገንባት እንዲችሉ ማገዝ

ዲስትሪክቱ፤ እነኚህ የወላጆች ካፌ በመባል የሚታወቁትን ቦታዎች በበለጠ እንዲጠናከሩና በተለይም ለአደጋ ሊጋለጡ የሚችሉ ህጻናት ልጆችን በማገዝ በኩል ከፍተኛ ሚና እንዲጫወቱ ያደርጋል።

---

[55] Georgetown University Research Team, DC Family Survey, 2019.

### ግኝት 4 ተ. ከዚህ ከወላጆች ካፌ ሌላ፤ ዲስትሪክቱ በአሁኑ ወቅት፤ የቤተሰቦችን ተካፋይነትን በ ኪው-አይ-ኤን የፖሊሲ ምክር ቤት (QIN Policy Council) ፤በኤስ-ኢ-ሲ-ዲ-ሲ-ሲ (SECDCC) የቤተሰብና በግዜ ጣልቃ መግባት ኮሚቴ ፤ ትራይቭ ባይ ፋይቭ ዲሲ (Thrive by Five DC) አስተባባሪ ምክርቤት እንዲሁም በ ማይ ስኩል ዲሲ የወላጆች አማካሪ ምክር ቤት (My School DC Parent Advisory Council )በኩል ድጋፉን ይሰጣል።

ይህ ኪው-አይ-ኤን የፖሊሲ ምክር ቤት (QIN Policy Council) ከሁለቱ የድርጅቶች የተውጣጡ ሁለት (CCP) የቤተሰብ ተወካዮች፤ ቁጥራቸው አምስት የሚሆን ከማህበረሰቡ የተወከሉና ስራውን የሚመሩና የቤተሰቦች ድምጽ ምን ያህል ለ ፕሮግራሙ ዋና መሆኑን በማስረዳት ይሰራሉ።። የኤስ-ኢ-ሲ-ዲ-ሲ-ሲ ቤተሰብና በግዜ ጣልቃ መግባት ኮሚቴ (SECDCC Family and Early Intervention committee)፤ የዚሁ ድርጅት አነስተኛ ኮሚቴ እንዲሁም (በ ግኝት 11 ሀ እንደተገለጸው) የትራይቭ ባይ ፋይቭ አስተባባሪ ምክርቤት (Thrive by Five Coordinating Council ) በተጨማሪም የቤተሰቦች አመራርና የወላጆች ድምጽ እንዲያስተጋቡ ዕድል ይሰጣል። የማይ ስኩል ዲሲ የወላጆች ምክር ሰጪ ምክር ቤት (My School DC Parent Advisory Council) በዲስትሪክቱ ውስጥ ባሉት ቤቶች(ward ) ውክልና እንዳለውና በዋነኛዎቹ ተራ የእጣ ስርአት ጋር የተዛመዱ ውሳኔ በሚደረግባቸው ጉዳዮች ሁሉ ተካፋይ ቤተሰቦች ድምጽ እንዳላቸው ይገልጻል። ምክር ቤቱ፤ ለአካባቢዎቻቸው እንደ የመረጃ አምባሳድሮች ሆነው የሚያገለግሉትን የማይ ስኩል ዲሲ( My School DC) ስራን ይደግፋል፣ ያጠናክራልም። እንደ አንድ የክፍለሃገሩ ዕቅድ፤ የ ዲስትሪክቱ Every Student Succeeds Act (ESSA) ፤ OSSE የ ወላጆች፤የቤተሰቦችና የማህበረሰብ ተሳትፎ (Family and Community Engagement (PFCE) Framework) በማጎልበት በቤተሰቦችና( ማግኘት የነበረባቸውን አገልግሎት የማያገኙ ልጆች ቤተሰቦችንም ጨምሮ ስኬታማነትና የተሳትፎ በማህበረሰቡ ውስጥ እንዲኖር ሰርቷል። በዚህም፤ ለቤተስቦች ስልጠናና ቴክኒካል እገዛ አድርጓል።

***መሪ ጥያቄ:*** በተለይ ለጉዳት የተጋለጡና ማግኘት የሚገባቸውን አገልግሎት የማያገኙ ህጻናትን በሚመለከት፤ እንክብካቤን ለማሻሻል ትልቁ ነገርና ዕድሉ ምንድነው ይላሉ?

### ግኝት 4 ቀ. በዘርና በቦታ ምክንያት ለህጻናት የሚደረገው እንክብካቤና የሚሰጠው ትምህርት ልዩነት ሳይኖር ለሁሉም በእኩልነት እንዲዳረስ ለማድረግ የበለጠ ጥናት ማካሄድና እርምጃዎችን መወሰድ ያስፈልጋል።

ጥራት ያለውን የትምህርት ፕሮግራም የማግኘት ዕድል በእኩልነት ሁሉም ቦታዎች አልተሰራጨም። መረጃዎች እንደሚያሳዩት፤ ጥራት ያላቸው ቦታዎች እጥረት የሚያጋጥመው ህዝብ በብዛት ባለባቸው ቤቶች በ(wards) 7 እና 8 ነው። ከሌሎች ቤቶች ጋር ካሉት ሲወዳደር በእነዚህ ቤቶች ያሉት የሆነ ነገር ለማግኘት ያላቸው እድል በጣም ዝቅተኛ ነው።[56,57,58]ግልጽ ሆኖ እንደሚታየው በቤቶች(wards) 7 እና 8 የሚኖሩት ጥራት ያለው የህጻናት ትምህርት እድል ወይም ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሰ ልጆች ጥራት ያለው ከትምህርት በፊትና ከትምህርት በኋላ የሚሰጠውን ማቆያ አያገኙም፤እንዲሁም ከ12 ዓመት ዕድሜ በታች ለሆኑ ልጆቻቸው ከተወሰነው ልማዳዊ ሰዓት ውጪ ማቆያ አያገኙም።[59,60] በ2018 የተደረገው የ Urban Institute ጥናት መሰረት፤ በዲስትሪክቱ የ8,250 ልማዳዊ ያሎነ የሰዓታት እጥረት አለ።[61] ይሄው ጥናት በተጨማሪ ይሄው Urban Institute study ይህንን ከልማዳዊ ሰዓታት ውጪ ለልጆቻቸው ማቆያ የሚፈልጉት ቤተሰቦች የገቢ ችግር ያላቸውና ቅናሽ የሚፈልጉ በቤቶች( wards) 7 እና 8 የሚኖሩ ናቸው። በአጠቃላይ አነጋገር፤ ዕድሜያቸው 12 ወይም ከዛ በታች ከሆኑ ልጆች ውስጥ፤ ከመቶ 22ቱ መቆያ ቦታዎች ከተለመደው ሰዓታት ውጪ የሚያስፈልጋቸው ናቸው።በዲስትሪክቱ ካሉት ዕድሜያቸው 5 ወይም ከዛ በታች ከሆኑ ህጻናት 40 ከመቶው ደግሞ እንዲሁ ከተለመደው ሰዓታት ውጪ ማቆያ የሚያስፈልጋቸውና በ ቤቶች (wards) 7 እና 8 [62] የሚኖሩ ናቸው።

እነኚህ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦች በሚኖሩባቸው ቤቶች ያሉ የህጻናት ያገልግሎት መስጭያ ቦታዎች፤ ጥረት ያለው አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ፤ ለአክሰስ ቱ ኳሊቲ የገንዘብ አበርክቶ (Quality Child Care Fund ) የሚደረገውን መዋእለ ንዋይ እንዲጎላበት ማደርግ ነው። ይህም በ ቲቸር ኤጁኬሽን Teacher Education and Compensation Helps (T.E.A.C.H.) በኩል የሚደረግ መማህራን ስኮላርሺፕ እንዲያገኙና እውቀታቸው ከፍ እንዲል ማድረግን እንዲሁም Child Development Associate (CDA) ፕሮግራሞች ፤ Access to Quality Child Care Expansion Grant የመሳሰሉት የገንዘብ አበርክቶ እንዲያገኙ በማድረግ በተቋሞች ላይ መሻሻል ማምጣት ይችላል።

---

[56] District of Columbia Government Child and Family Services Agency, *FY2020 Needs Assessment and Resource Development Plan*, 2018.
[57] District of Columbia Department of Health Community Health Administration, *5 Year Maternal and Child Health Needs Assessment 2016-2020*, 2014.
[58] Sayin Taylor and K. Zickuhr. *Needs Assessment of Out-of-School Time Programs in the District of Columbia. D.C. Policy Center,* October 2017.
[59] Urban Institute, *Nontraditional-Hour Child Care in the District of Columbia*, 2018.
[60] Bainum Family Foundation, *Early Learning Supply and Demand in the District of Columbia: Using Data to Identify Critical Gaps*, 2018.
[61] Urban Institute, *Nontraditional-Hour Child Care in the District of Columbia*, 2018, p.27.
[62] *Ibid,* p. 22.

## ክፍል 5 ግኝቶች

# በፕሮግራሞችና በአገልግሎቶች መካከል ትብብር እንዲኖር ለመደገፍ የመረጃና የጥናት ቀዳዳን ማጥበብ የወላጆች ምርጫን ደግሞ ማጠናከር

***መሪ ጥያቄ:*** የፕሮግራሞችና የአገልግሎቶች ትብብርን በሚመለከት ያሉት የመረጃዎች ወይም የጥናቶች ከፍተኛቹ እጥረቶች ምንድናቸው?

***ግኝት 5 ሀ. እያንዳንዱ የዲስትሪክቱ ተቋም ለጉዳት የታጋለጡትንና ከሚገባቸው በታች አገልግሎት የሚያገኙትን ለይቶ ለማወቅ የየራሱ መንገዶች አሉት።*** በአሁኑ ወቅት ለጉዳት የተጋለጡ (vulnerable) ወይም ከሚገባቸው አገልግሎት በታች የሚያገኙ(underserved) ለሚሉት ሁለት ቃላት፤ የዲስትሪክቱ ተቋሞች ሁሉ የሚጠቀሙበት ዘላቂ፡ የማይቀያየር አገላለጽ የለም።[63] በመሆኑም፤ ጉዳዩ የሚመለከታቸው በዲስትሪክቱ የሚገኙ ከልደት እስከ አምስት ዓመት ዕድሜ ልጆች ያሉዋቸው ቤተሰቦች፤ መንግስት ለተቸገሩ ቤተሰቦች የሚሰጠው እርዳታ የቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ( TANF) ተቀባዮች፤ የማደጎ ልጆች ( foster care) የሚንከባከቡ ቤተሰቦች ወይም ከሲ-ኤፍ-ኤስ-ኤ (CFSA) ጋር ግንኙነት ያላቸው፤ ወይም የቤት አልባነት ችግር ያጋጠማቸው ልጆች ወላጆች ስለእነዚህ ጉዳዮች የተወሰነ ዕውቀት ነው ያላቸው።[64] ከኤስ-ኢ-ሲ-ዲ-ሲ-ሲ( SECDCC) ጋርና ከሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጋር የቅርብ ግንኑነት ማድረግ፤ መረጃውን በመሰብሰብ ረገድ ከፍተኛ ተራ መጫወት ብቻ ስይሆን ወደፊት በሚደርጉ ውሳኔዎችም ከፍተኛ ሚና አለው።

***ግኝት 5 ለ. የዲስትሪክቱ ተቋሞች፡ የየግላቸውን መረጃ ነው የሚሰበስቡት። በመሆኑም በመላው ዲስትሪክት ለሚገኙት ከልደት እስከ አምስት ዓመት ዕድሜ ላላቸው ህጻናት ፕሮግራሞችንና አገልግሎቶችን በእኩልነት ለመስጠት የተወሰነ እድል ነው ያለው***
Each እያንዳንዱ የዲስትሪክቱ ተቋም፤ በፕሮግራሙ ስለመሳተፍና የትኛው ህዝብ በፕሮግራሙ እንደተገለገለ ለማወቅ የመረጃ አሰባሰብና እቀባን በተመለከተ የየራሱ አገባብና ዘዴን ነው የሚጠቀመው።ይህም መረጃዎች የትምማለትም በየተቋሙ ተበታትነው እንዲታቀቡ ያደርጋል። እነኚህ የተበታተኑ መረጃዎች አንድ ላይ እንዲሰባሰቡ ማድረግ የትኛው ክፍል ነው በበለጠ እርዳታ የሚያስፈልገው ለማወቅ ያስችላል ብቻ ሳይሆን ተቋሞችም ውጤታማ ስራ እንዲሰሩና አዲሶች እርዳታ ፈለጊዎችን ለመዳሰስ ያስችላቸ ዋል።

***መሪ ጥያቄ፤*** ይህ የተፈጠረውን ቀዳዳ ለማጥብብ ዲስትሪክቱ ምን የሚወስደው እርምጃ አለ?

***ግኝት 5 ሐ፤***
***የመላው ክፍለሃገር የትምህርት መረጃ ትምህርተ-ስርአት( Statewide Longitudinal Education Data (SLED ስሌድ)፤ ተማሪዎች ከህጻንነታቸው ጀምሮ አድገው ትምህርት እስኪጀምሩና እስኪጨርሱ እንዲሁም ስራ እስኪይዙ ድረስ ያለውን የትምህርታቸውን ሂደት የሚያሳይ መረጃ፤ ከሚመለከታቸው ጋር ሁሉ ለመካፈል የሚያስችል ነው።*** ኦ-ኤስ-ኤስ-ኢ( OSSE)፤ በ ስሌድ የሚሰጠውን ትምህርት ወደአጠቃላይ የኢ-ሲ-አይ-ዲ-ኤስ (ECIDS) ስርዓተ-ትምህርት ለማጠቃለል ዕቅድ አለው።

### የህጻንነት የተቀነባበረ የመረጃ ስርዓት (ECIDS)

የኢ-ሲ-ኢ( ECE) እና የትምህርት መረጃ ሰራዓተ-ትምህርት፤ በኢ-ሲ-አይ-ዲ-ኤስ (ECIDS) በኩል እንዲዋሃዱና ተደጋጋሚ ያልሆነ የመቁጠር መረጃ እንዲፈጠር መፍቀድ በህጻንነት ዘመን ካሉት ፕሮግራሞች ውስጥ፤ ከ ክፍል ሲ ወደ ክፍል ቢ( Part C to B) የሚደረገውን ሽግግር ቀላል እንዲሆን ያደርጋል። በመጨረሻም እንዲህ ዓይነቱ የተሻሻለ ሽግግር፤ ጠቃሚ የሆነ የረጅም ግዜ የውጤት መረጃ እንድናገኝ ስለሚረዳ፤ በተለይ ለጉዳት የተጋለጡ ናቸው ለሚባሉትና ማግኘት ከሚገባቸው አገልግሎት በታች ሲያገኙ ለቆዩ ልጆች፤ ውጤታማ የሆነ ፕሮግራም ለማቅረብ ይረዳናል።
በኢ-ሲ-ኢ( ECE) ፕሮግራሞች በወቅቱ በመገለገል ላይ ያሉ ኦ-ኤስ-ኤስ-ኢ(OSSE) ያልተደጋገመ የልጆች ቁጥር ለይቶ ለማወቅ ልዩ የልጆች መለያ ፤ ወደኋላም ይህ መለያ፤ ተማሪዎች በዲሲ የመንግስት ትምህርት ቤቶችና ቻርተር ትምህርትቤቶች ሲገቡ በስሌድ( SLED) ሰርዓት ውስጥ ዋነኛው የተማሪዎች መለያ መሳርያ ይሆንና ተማሪዎችን በቀላሉ ለመለየት ይቻላል። እነኚህ ጥረቶችም፤ በተለይ

---
[63] Bainum Family Foundation, *The District of Columbia's Preschool Development Grant Birth Through Five: Synthesis of Needs Assessment*, 2019.
[64] *Ibid.*

ለጉዳት የተጋለጡና ከሚገባቸው አገልግሎት በታች ሲያገኙ ለቆዩ፤ ከልደት እስከ አምስት ዓመት ዕድሜ ያላቸው ልጆችን በተመለከተ በመረጃ የተደገፈ ውሳኔዎች እንዲደረጉ ያስችላል።

***መሪ ጥያቄ፤*** የወላጆችን ምርጫዎች ለማሳደግ ባሉት መረጃዎችና ጥናቶች ያለው እጅግ ከባድ እጥረት ምንድነው?

***ግኝት 5 መ፣ በዲስትሪክቱ ውስጥ የወላጆች ምርጫ ትኩረት መስጠት የሚገባው ቁልፍ ነገር ቢሆንም፤ ወላጆች ወይም ቤተሰቦች አንዱን ፕሮግራም ወይም አንዱን አገልግሎት ከሌላው ለምን እንደሚመርጡ የሚያስረዳ ታሪካዊ መረጃ የለም።***
አሁንም ቢሆን የወላጆች የፕሮግራምና የአገልግሎት አመራረጥ ለምን እንደሆነ ለማወቅ ገና ተጨማሪ መረጃ ያስፈልጋል(ለምሳሌ የተመረጠው ቦታ፡ የአስተማሪ ግምገማ፤ የትምህርት ቤት ጉብኝት፤ በበዓላት የሚታለፉ ተሞክሮዎች፡ ከቤት ቤት በመሄድ የሚደረግ ጥናት)። ቤተሰቦች ለምን አንድን የትምህርት ቦታን እንደመረጡ የሚሰጡት መልስ ምናልባት የሚሰጡትን የተለያዩ የትምህርት ዕድሎችን ግምት ውስጥ ሳያስገቡ ወይም እነኚህ ዕድሎች መኖራቸውን ሳያውቁ ሊሆን ስለሚችል፤ የትኛው መለኪት ነው ውጤታም የሆነው ወይም የትኛው የግንኙነት መስኪ ነው መሻሻል ያለበት ብለን ለመገምገም ያበቃናል።

***ግኝት 5 ሰ፤ ቤተሰቦች፤ የልጆቻቸውን እንክብካቤ፣ ጤንነትና ትምህርትን በተመለከተ የሚያደርጉትን ምርጫ ሃብታም ለማድረግ፡ ዲስትሪክቱ ቀጣይነት ባለው መንገድ መረጃ እንዲያገኙ ይጥራል።*** በግኝት 4 ለ እንደተገለጸው፣ ማይ ቻልድ ኬር ዲሲ (My Child Care DC) ዌብሳይት፤ ፍቃድ ያላቸው የህጻናት ማቆያ ትምህርት ቤቶችን በተመለከተ መረጃ ሲስጥ፤ ዲስትሪክቱ ስለዚሁ ጉዳይ አጠቃላይ መረጃ ስለሌለው፡ ቤተሰቦች በአጠቃላይ ምን ያህል ቁጥር ያላቸው የትምህርት ቤቶች እንዳሉ ለማወቅ ያዳግታቸዋል

***መሪ ጥያቄ:*** ይህንን እጥረት ለማስወገድ ዲስትሪክቱ ምን እርምጃዎችን እየወሰደ ነው?

***ግኝት 5 ረ፤ ዲስትሪክቱ፤ ከልደት እስከ አምስት ዓመት ዕድሜ የሆኑ ልጆች ያሉዋቸው ቤተሰቦች፤ የልጆቻቸውን ትምህርት፣ ጤንነትና ሊያገኙዋቸው የሚገቡ አገለግሎቶችን በሚመለከት አስፈላጊውን መረጃ እንዲያገኙ ለማገዝ፤ ከጆርጅታውን ዩኒቨርሲቲ (Georgetown University) ጋር በመተባበር፡ በ 2019 የዲሲ ቤተሰቦች ጥናት አካሄደ።***
በዚህ ጥናትም፡ ቢያንስ አንድ ከልደት እስከ አምስት ዓመት ዕድሜ ልጅ ያሏቸው ቤተሰቦች፤ ፕሮግራሞችን፣ ጠቀሜታዎችን፡ ምንጮችንና የህጻናት መዋያዎችና የትምህርት ተቋሞችን እንዲሁም የጣልቃ ገብነት ፕሮግራምን በተመለከተ ምን ያህል መረጃና እውቀት እንዳላቸው ይገመግማል።[65] ቤተሰቦች በተጨማሪ ስለእነዚህ የተለያዩ ፕሮግራሞች፣ ጠቀሜታዎች፣ አገልግሎቶችና ምንጮች መጀመርያ ከየት እንደሰሙና እነሱን ለማግኘት ደግሞ የሆነ ያጋጠመ ችግር ወይም እንቅፋት ከነበር በዝርዝር ያስረዳል። ይሄው የ2019 ጥናት፤ ከ 2,099 ቤተሰቦች መረጃ የሰበሰበ ሲሆን ይህ የተሰበሰበው መረጃ ለሌሎች ጥናቶች መሰረት ይሆናል። ጥናቱም ከልደት እስከ አምስት ዓመት ዕድሜ ልጆች ካሏቸው ቤተሰቦች አስተያየቶች በየዓመቱ እንዲሰበሰብ ያደርጋል።

በተጨማሪም፤ አርባን ኢኒስቲቱት (Urban Institute) ይህንን የማይ ስኩል ዲሲ ( My School DC) መረጃን ለጉዳት የተጋለጡና ማግኘት ከሚገባቸው አገልግሎት በታች የሚያገኙ ልጆች ቤተሰቦች ትምህርትን በተመለከተ ምርጫዎቻቸውን እንዴት እንደሚያደርጉ ጥናት ለማካሄድ አስችሎታል። ይህ ጥናት፤ በመላው ከተማ ያሉት መዋእለ ህጻናት ምን ያህል ዝግጁ መሆናቸውን፤ ቤተሰቦች የልጆቻቸውን መጀመርያ የህጻናት መዋያ ከዛ በኋላ ደግሞ ትምህርት ቤት ሲመርጡ የውሳኔ አወሳሰዳቸው ሂደትን መዝግቧል። ከዛም በላይ የቅድመ ትምህርት ቦታዎችን ውጤታማነትና ጥራት ለማሻሻል የሚያግዙ ሁኔታዎችን ለይቶ ያቀርባል።

***ግኝት 5 ሰ፤ የዲሲ ቻይልድ ኬር ኮኔክሽንስ (DC Child Care Connections (DC CCC) የዲስትሪክቱ የልጆች እንክብካቤ ምንጮችና ሬፈራል ፕሮግራም( Child Care Resource and Referral (*** ሲ-ሲ-አር&አር ***CCR&R) ) ነው ።*** በወቅቱም ፕሮግራሙ፤ የዲስትሪክቱ ቤተሰቦችና መምሂራን ምን እንደሚያስፈልጋቸው ለማወቅ እየተንቀሳቀሰ ነው። ይሄው የ ሲ-ሲ-አርናአር (CCR&R) ፕሮግራም፤ ለቤተሰቦች፣ለትምህርት ሰጪዎችና ለዲስትሪክቱ ማህበረሰብ የተዋሃሃደና ውጤታማ የሆነ የእገዛና የአገልግሎት ስራአት እንዲኖር ለማድረግ ይሰራል፤ ይህንንም መልስ-ተግባር ባላቸው አገልግሎቶችና በማረጋገጫ በተደገፉ እግዛዎች፣ ፒዲን( PD) ጨምሮ በስራ ላይ ያከናውናል። ለተጨማሪ የዲሲ ሲሲሲ( DC CCC ) መረጃ፤ (https://osse.dc.gov/page/dc-child-care-connections) ይጎብኙ።

[65] Georgetown University Research Team, DC Family Survey, 2019.

## ክፍል 6 ግኝቶች

# የፕሮግራሞች ጥራትና እገዛ የሚገኝበት ሁኔታ

***መሪ ጥያ፤*** What program ልጆችን ተገቢ፡ ጥራት ካለው እንክብካቤና ትምህርት ለማገናኘት ሊደረጉ የሚችሉ ምን ፕሮግራሞች ወይም እገዛዎች አሉ?

***ግኝት 6 ሀ፤ ወላጆችን ተገቢ ከሆነና ጥራት ካለው እንክብካቤና ትምህርት ጋር ለማገናኘት፤ ዲስትሪክቱ አያሌ ጠንካራ ፕሮግራሞችና እገዛዎች አለው።*** እነኚህ ፕሮግራሞችና እገዛዎች፤ የዲሲ የትምህርት ሪፖርት ካርድ( DC School Report Card ( በግኝት ሀ እንደተገለጸው)፣ ፋይንድ ማይ ቻይልድ ኬር ዲሲ (Find My Child Care DC) (በግኝት 4 ለ እና በግኝት 5 ሰ እንደተገለጸው)፣ ማይ ስኩል ዲሲ (My School DC) (በግኝት 5 ረ)፣ ዲሲ ሲሲሲ (DC CCC) (በግኝት 5 ሰ እንደተገለጸው)፤ ሄልፕ ሚ ግሮ ዲሲ (Help Me Grow DC) (https://helpmegrow.dc.gov/) እና ትራይቭ ባይ ፋይቭ ዲሲ( Thrive by Five DC) (https://thrivebyfive.dc.gov/). በተጨማሪም የዲሲ ላንጉጅ አክሰስ ፕሮግራም ( DC Language Access Program) (https://ohr.dc.gov/service/language-access-program-information-portal) ሌላ ባህል ያላቸውና ሌላ ቋንቋ የሚናገሩ ቤተሰቦች በራሳቸው ቋንቋ ምን ዓይነት ፕሮግራሞች እንዳሉና እርዳታ እንዴት እንደሚያገኙ እንዲያውቁ ይረዳል።

***መሪ ጥያቄዎች፤*** ከእነኚህ ፕሮግራሞችና እገዛዎች ጋር ምን ሊሰራ ይችላል?

***ግኝት 6 ለ፤ ዲስትሪክቱ፡ ለጉዳት የተጋለጡ ወይም ማግኘት የሚገባቸውን አገልግሎት የማያገኙ በተለይም የዕድገት መዘግየት ወይም አንድ ዓይነት ስንክልና ያለባቸውን ልጆች ለመርዳት በርካታ ፕሮግራሞች ላይ አተኩሯል።*** *የእነዚህ ፕሮግራሞች ምሳሌዎች ደግሞ* ስትሮንግ ስታርት ዲሲ በግዜ ጣልቃ የመግባት ፕሮግራም (Strong Start DC Early Intervention Program) ያጠቃልላል። (https://osse.dc.gov/service/strong-start-dc-early-intervention-program-dc-eip), Early Stages (https://www.earlystagesdc.org/) እና የዲሲ ኢንተርኤጀንሲ ኮኦርዲኔቲንግ ካውንስል (DC Interagency Coordinating Council (ዲሲ አይ-ሲሲ DC ICC) ንም ያጠቃልላል። (https://osse.dc.gov/service/dc-interagency-coordinating-council)

***መሪ ጥያቄ፤*** ከዚህ የተሻለ ወይም የበለጠ አለን?

***ግኝት 6 ሐ፤ በተደረገው የ ፒ-ዲ-ጂ የመስማት ስብሰባ ላይ፤ ቤተሰቦች ፕሮግራሞቹ የሚሰጡባቸው ቦታዎች ርቀትና እነሱም ጋ ለመድረስ ምቹ የሆነ የህዝብ ማመላለሻ አገልግሎት አለመኖሩ፤ ልዩ የትምህርት ቤት አገልግሎቶችን ለማግኘት እንቅፋት መሆናቸው ተገልጿል።*** ቤተሰቦች፤ የሚሰጡት ፕሮግራሞችና እገዛዎች እጅግ ጠቃሚ መሆናቸውን ቢገልጹም፤ አንዳንድ ቤተሰቦች በማመላለሻ ችግር ምክንያትም ሆነ ወደ ቦታዎቹ ለመድረስ በሚወስደው የግዜ እርዝማኔ ምክንያት፤በተለይም ከአንድ የማመላለሻ አገባብ ወደ ሌላ መቀየር ስለሚያስፈልጋቸው፣ አያሌ ፕሮግራሞችን ለመጠቀም አለመቻላቸውን ገልጸዋል። ቤተሰቦች፤ በሚሰጡት ፕሮግራሞች ለመሳተፍ ፕሮግራሞቹ የሚሰጡት ለቤታቸው ወይም ለስራቸው ቅርበት ባላቸው ቦታዎች ቢሆኑ እንደሚሻል አመልክተዋል።

***ግኝት 6 መ፤ በግኝት 4 ቀ እንደተገለጸው፤ ዲስትሪክቱ አያሌ ፕሮግራሞችንና አገልግሎቶችን የሚሰጥ ቢሆንም፤ እነዚህ ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች መኖራቸውን የማያውቁ ቤተሰቦች አሉ።*** ፕሮግራሞችንና አገልግሎቶችን በሚመለከትም በብዙ ዌብሳይቶች፣ በዲሲ የመንግስት ትምህርት ቤቶች (ዲሲ-ፒ-ኤስ -DCPS) ፕሮግራሞች፡ እንዲሁም በዲስትሪክቱ መጻህፍት ቤቶች፣ የልጆች መዋያና የትምህርት አገልግሎት ከሚሰጡ ለትርፍ የማይሰሩ ተቋሞች (ለምሳሌ ማርታስ ቴብል Martha’s Table) መረጃ ማግኘት ይቻላል። ይሁንና በነዚህ በ ፒ-ዲ-ጂ (PDG) የቤተሰብ መስማት ስብሰባዎች፤ አያሌ ተካፋዮች መረጃ የሚያገኙት ዋነኛው መንገድ፤ “በቃል” በሚሰጥ ማለትም የቤተሰብ አባሎች በሚነግሯቸው፣ ጓደኛ፣ ጎረቤት፣ ወይም የስራ ጓደኛ፣ ወይም በሃኪማቸው ጽህፈት ቤት ወይም ጸሎት በያደርጉባቸው ቦታዎች ካሉ ሰዎች እንደሆነ ይናገራሉ።[66] Theችግሩ በእንደዚህ ዓይነቱ የመረጃ መተላለፍ ትክክለኛነትን ለይቶ ለማወቅና ለመቆጣጠር የሚያስችል የተመደበ የማረጋገጫ መንገድ የለም።

---

[66] Georgetown University Research Team, DC Family Survey, 2019.

ክፍል 7 ግኝቶች

# ከክፍለሃገሩ ራእይ ጋር የሚስማሙ ፕሮጀክቶች የተፈለገውን ወይም የታለመውን ውጤት ማስገኘታቸውን የሚመዝኑ መለክያዎች

***መሪ ጥያቄ፤*** በአሁኑ ወቅት በስራ ላይ ያሉ የእነዚህን የገንዘብ አበርክቶና የዕቅድ ዓላማዎች ውጤታማነትና ዕድገት የሚለኩ ምን ዓይነት መለኪያዎች አሉ?

**ግኝት 7 ሀ ፤ ዲስትሪክቱ፤ ኢ-ዲ-አይን(EDI (https://www.raisedc.org/ourchildren/datacollection) ጨምሮ አያሌ መለኪያዎች አሉት፤ የጎረቤት ሪስክ ኢንዴክስ (Neighborhood Risk Index (NRI)፣ ክላስ (CLASS) ፣ የአካባቢ የመለኪያ ሚዛን (Environment Rating Scales (ERS) እና ፕሬገናንሲ (እርግዝና) ሪስክ አሴስመንት ሞኒተሪንግ ሲይስተም (Pregnancy Risk Assessment Monitoring System (PRAMS) (https://dchealth.dc.gov/DCPRAMS).** ዲስትሪክቱ የ ኤን-አር-ዓይ NRI) እና የኢ-ዲ-አይ (EDI) መረጃዎችን፤ ከፍተኛ አስፈላጊነት ባላቸው ጎረቤቶችና ቤቶች( wards)፤ የሚወስዳቸውን እርምጃዎች ለማስረዳት፤ ትኩረት የተሰጠባቸውን ጉዳዮች እድገት ለማፋጠን ይጠቀምባቸዋል። የክላስ(CLASS) መረጃ ጥቅም በበለጠ በግኝት 1ሀ በበለጠ ተገልጿል። እንደ አንደ የ ካፒታል ኳሊቲ (Capital Quality) ክፍል መጠን (በግኝት 1 ሀ እንደተገለጸው )፤ ሁለቱ የኢ-አር--ኤስ (ERS) መለኪያዎች የፕሮግራም ጥራት ለመለካትና የህጻናት መዋያ ቦታዎችም ሆነ በቤት ውስጥ የሚደረጉ የህጻናት ማቆያ ቦታዎች እንዴት ሊሻሻሉ እንደሚችሉ ለመጠቆም የሚያስችሉ ናቸው። ሌላው አስፈላጊና መመዘንና መታወቅ ያለበት ደግሞ የህጻናት የመሞት ደርጃና ካለቀናቸው የሚወለዱ ህጻናት ሚዛን ነው። ምንም እንኳን በየዓመቱ ስለሚወለዱ ህጻናት መረጃ ቢኖርም፤ካለ ቀናቸው ስለሚወለዱ ህጻናት በቂ መረጃ አምስት ዓመት እስከሚሞላቸው ድረስ የሚሰጣቸው አገልግሎትና የቀረቡት ምንጮች ምን ያህል ውጤታማ እንደሆኑ ለመገምገም አዳጋች ያደርገዋል።

### ኔበርሁድ ሪስክ ኢንዴክስ (ኤን-አር-አይ) Neighborhood Risk Index (NRI)

ኤን-አር-አይ ( NRI) የህጻናት የዕድገት መጓተት በሚመለከት ቀለል ካለው አደጋ ወደ ከፍተኛው ደርጃ ሊያመሩ የሚችሉ አስር የተጠቃለሉ ማሳያዎችን ያጠቃለለ ነው።[67] በህዝብ ቆጠራ ደረጃ የተዘጋጁ መረጃዎች በማውጫው ተዘርዝረዋል። ይህ መረጃም የሚያጠቃልለው፤ ማህበራዊና ትምህርታዊ ማሳያዎች ለምሳሌ በአንድ ወላጅ እንክብካቤ ብቻ የሚያድጉ ህጻናት ከመቶ ስንት ናቸው፤ የተወሰነ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታ ያላቸው ከመቶ ስንት ናቸው፤ ልጆች ያሏቸው ወላጆች ግን ደግሞ በድህነት ደረጃ የሚኖሩ ስንት ናቸው፣ ከመንግስት እርዳታ የሚቀበሉ ስንቶቹ ናቸው የሚሉትን ጥያቄዎች የሚመልሱ ማሳያዎች ናቸው። አደጋኛ ሁኔታ ውስጥ አሉ የሚባሉት (Risk) ሰዎች ደረጃ የሚለካው በጎረቤቱ ውስጥ ምን ያህሎቹ ናቸው አደጋ ውስጥ ያሉት ብሎ ከሚመልስ ማሳያ ነው የሚታወቀው።

ዲስትሪክቱ ሬዝ ዲሲ ጋር (Raise DC )ም እየሰራ ነው። ይህም ሬዝ ዲሲ (Raise DC) ፡ በዲስትሪክቱ ያለውን አነሳሽነት፡ ከዩኒቨርሲቲ ኦፍ ካሊፎርንያ(ሎዝ አንጀሊስ-UCLA) ጋር በማስተባበር ኤን-አር-አይ(NRI)ን ተግባራዊ ለማድረግ የሚሰራ ነው። በጥር ወር 2020፤ዲስትሪክቱ፤ የኢ-ዲ-አይ( EDI) መረጃን ከኤን-አር-አይ ( NRI) መረጃ ጋር በመሸፈን የህጻናት ዕድገት ካለው ለአደጋ የተጋለጠ አካባቢ ጋር እንዴት ተወዳድሮ እንደሚቀርብ በበለጠ ለመረዳት እንዲችል እቅድ አውጥቷል።

### በእርግዝና ወቅት ሊደርሱ የሚችሉ አደጋዎችን የሚገመም ስርአት (PREGNANCY RISK ASSESSMENT MONITORING SYSTEM (PRAMS)

በ2016 ካለ ቀናቸው የተወልዱ ህጻናት በቤት (ward ) 7 እጅግ የተለቀውን ቁጥር የያዘ ሲሆን ከመቶ 13.40፤ በቤት 8 ደግሞ ከመቶ 13.80 ነበር። ይህም በጥቁሮችና ሂስፓኒክ ባልሆኑ እናቶች ዘንድ ሲሆን፤ ከነጭ እናቶች ጋር ሲወዳደር፤ ጥቁርና ሂስፓኒክ ያልሆኑ እና ከመቶ 12.80 እናቶች ካለ ቀናቸው ሲወልዱ፤ ከነጭ እናቶች ደግሞ ከመቶ 7.80 ነበሩ ካለ ቀናቸው የወለዱት። [68] በተጨማሪም፤ በ 2015-16፤ በቤት ( Ward) 8 ገና በህጻነታቸው የሞቱ ህጻናት ቁጥር ከመቶ 14.57 ሲሆን የመላው ዲስትሪክት ደግሞ ከመቶ 7.59

[67] Bruner, C et.al (2007). *Village building and school readiness: Closing opportunity gaps in a diverse society. State Early Childhood Policy Technical Assistance Network: Des Moines, IA. See: Chapter One: Census tracts and child-raising: Place-based implications for child and family policy investments and reforms.* Pp. 5-14.

[68] District of Columbia Department of Health, *Perinatal Health and Infant Mortality Report*, 2018.

ነበር።[69] በ 2017 የዲሲ ሄልት (DC Health) ፕሮግራሞችና ፖሊሲዎች የነፍሰ ጹር እናቶችን ጤነነት በማሻሻል ረገድ እንዲሰሩ የፕራምስን (PRAMS)ፕሮግራም ማስተጋባት ጀመረ።

***መሪ ጥያቄ፤*** የእነዚህ ማሳያዎች ሃያል ጎንና ደካማ ጎን ምንድነው?

**ግኝት 7 ለ ፤ ዲስትሪክቱ በህጻናት ትምህርት ላይ የሚያውለው ወጪ ጠንካራ ቢሆንም፤ ብዙዎቹ የህጻናት መለኪያዎች የሚገኙት ከአጠቃላይ ህዝብ ጋር ተደምረው ነው- በፕሮግራም ደረጃ ወይም በክፍል ደረጃ ተደማምረው ነው። በመሆኑም አብዛኛውን ግዜ፤ በህጻናት ደረጃ ብቻ ሊታዩ የሚገባቸው መረጃዎች የላቸውም።** በአሁኑ ወቅት፤ያለው መረጃ ከሌሎች መረጃዎች ተያይዘው የቀረቡ ። የህጻናት ዕድገት ደረጃዎችን የሚያሳዩ እንጂ ለአደጋ የተጋለጡ ወይም ማግኘት ከሚገባቸው አገልግሎት በታች የሚያገኙ ህጻናትን በተመለከተ ጥልቀት ያለው ግምገማ እንዲደርግ የሚፈቅዱ አይደሉም። እያንዳንዱ ከላይ የተጠቀሱት ስራአቶችና ፕሮግራሞች፤ ከአካባቢ መረጃዎች ጋር በማስተባበር፤ የአካባቢና የመኖርያ ቤቶችን ሁኔታዎች በበለጠ በመረዳትና ለአደጋ የተጋለጡትን ቤተሰቦች ለይቶ ለማወቅ ሊጠቅሙ ይችላሉ። ለምሳሌ የኢ-ዲ-አይ ኳሊቲ ኦፍ ዘ ኮሙኒቲ (EDI Quality of the Community) ግኝቶች፤ ከሌሎች ግኝቶች ጋር ተደማምረው ሊረዱ ይችላሉ።በግኝት 7 ሀ እንደተገለጸው፤ ዲስትሪክቱ፤ ኤን-አር-አይ( NRI)ን ከ ኢ-ዲ-አይ( EDI) መረጃዎች ጋር በማስተባበር በአካባቢው የሚገኙትን ለአደጋ የተጋለጡ አካባቢዎች ከህጻናት እድገት ጋር ያላቸው ዝምድና ምን እንደሆነ ለማወቅ የሚያስችል መንገድ እያጠና ነው።

**ግኝት 7 ሐ. ሌላው መጠናት፣ መታወቅ ያለበትና ጠለቅ ያለ እውቀት የሚያስፈልገው (1) መማህራን/ ትምህርት ሰጪዎች( የወቅቱ ዕድገት)፤ (2) የመማህራን ደሞዝ እና (3) ከጎን የሚሰለፉ ውጤቶች (ለምሳሌ መምህሩ ከተቋሙ ጋር ረጀም ዓመታት ቆየን፤ መምህሩ በዲሲ መንግስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ሆኖ ወይም ወደሌሎች የቻርተር ትምህርት ቤቶች ከፍ ያለ ደሞዝ ለማግኘት ለቆ ሄደን)በተለይም አስተማሪ ለመሆን የሚጠየቀው የችሎታ መጠን በአሁኑ ወቅት እያነሰ በሚመጣበት ወቅት የሚሉት ጥያቄዎች ናቸው።** ኦ-ኤስ-ኤስ ኢ (OSSE) በታህሳስ ወር 2016 (https://osse.dc.gov/node/1258306)፤በህጻናት ትምህርት ውስጥ የሚሳተፉ መማህራን ወይም ሌሎች በስራው ለመግባት ማሟላት ያለባቸውን የትምህርት ደረጃ ወደ ታች ዝቅ አድርጎታል። ይህም ጥሩ መሆኑና አለመሆኑ እንዲሁም የአባሎች ከአንዱ ስራ ወደሌላው መዛወር ቀጣይ ጥናት የሚያስፈልገው ነው። ጥሩ የማስተማር ችሎታ ያላቸውን መማህራን የማግኘት፡ ያሉትን መምህራን የማቀብ ሁኔታን የማወቅ መረጃ ትምህርትን ለማሻሻልም ሆነ መማህራንን የማግኘትና የማቀብ ሁኔታን ለማስተካከል ይረዳል።

**ግኝት 7 ዲ፤ በደንብ የተረጋገጠ ወይም የታወቀ ሃያል ጎን፤ የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምብያ የህጻናት የትምህርት ስርዓት፤ የህጻናት ጤንነት፣ ዕድገት፤ትምህርትና ደህንነት በተመለከተ የሚያደርገው ክትትል ነው።** በ 2018፤ በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምብያና በዲስትሪክቱ ተቋሞች፤ የግልና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች መካከል ከፍተኛ ትብብር ተደርጎ፤ የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምብያ የህጻናት ትምህርት በተለይም የህጻናት ጤንነት፣ እድገት፣ ትምህርትና አጠቃላይ ደህንነት እንዲሻሻል) ተደርጓል። (https://bit.ly/earlychildhoodsystemsapproach። በዚህ ጉዳይ ላይ የተባበሩት ሸሪኮች፣ ኤስ-ኢ-ሲ-ዲ-ሲ-ሲ SECDCC፣ ኩን (QIN) ኢንተርጀንሲ ስቲሪንግ ኮሚቴ(Interagency Steering Committee)፣ የእርሊ ቻይልድሁድ(Early Childhood I novation Network (ECIN) ሸሪኮች ፣ ሬዝ ዲሲ ( Raise DC)ሌሎች የህጻናት ደጋፊ ተቋሞች(ለምሳሌ አገልግሎት ሰጪዎች፣ ቤተሰቦች፣ ኤል=ኢ-ኤ (LEAs )፣ ተጣባቂዎች፣ የዩ-ሲ-ኤል-ኤ (UCLA ) የጤናማ ልጆች ማእከል፣ ቤተሰቦችና ማህበረሰቦች፣ ብሄራዊው የቢልድ (BUILD)አነሳሽነት ይገኙባቸዋል። የዚህ ስርአት መሻሻል የዲስትሪክቱን የፒ-ዲ-ጂ (PDG ) ስትራተጂካዊ የዕቅድ መሰረት እንዲያሻሽል ተደርጓል።

[69] *Ibid*, p. 53.

ክፍል 8 ግኝቶች

# የኢ-ሲ-ኢ( ECE) የስራ ተቋሞችን የሚመለከቱ ጉዳዮች

- **መሪ ጥያቄ፤** የኢ-ሲ-ኢ( ECE) የስራ ተቋሞችን የሚመለከቱ ምን ጉዳዮች ናቸው የተነሱት?

**ግኝት 8 ሀ ፤ በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምብያ የህጻናት ትምህርት ተፈላጊነትና አቅርቦት (Supply and Demand )የሚያሳዩ መረጃዎች እንደሚገልጹት፤ በቤናም ፋሚሊ ፋውንዴሽን( Bainum Family Foundation)በኩል የተደረገውን Identify Critical Gaps) ጥናት በመመልከት በቤቶች( wards) 7 እና 8 የሚጠየቀውን ሁሉ ሊያሟሉ የሚችሉ በቂ የሆኑ ጥራት ያላቸው ተቋሞች የሉም።**[70] እነኚህ ቤቶች (wards)፣ ከፍተኛውን ቁጥር የያዙ፤ ለጉዳት የተጋለጡና ማግኘት ከሚገባቸው አገልግሎት በታች የሚያገኙ ልጆች ያሉባቸው፣ ተቀማጮቹ ጥቁር አሜሪካውያን የሆኑና በጣም ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦች የሚቀመጡባቸው ናቸው። አለመመጣጠን፣ የተደረጉ ጥናቶች፡ ጥራት ያላቸው የመማርያ ተቋሞችነ የእርዳታ አገልግሎቶች ሁሉ (ለምሳሌ ህጻን ከመወለዱ በፊት ለነፍሰጹሮች የሚደረግ እርዳታ፡ የስራ ስልጠና) በዘርና በገቢ መጠን የሚካሄዱ ናቸው።[71]

**መሪ ጥያቄ፣** የህጻናት የትምህርት ተቋሞችን ለመመልከት የሚያስችሉ ምን ወቅታዊ ዕቅዶች አሉ ?

**ግኝት 8 ለ፤ የህጻናት የትምህርት ተቋሞችን ቁጥር ለመጨምር በርካታ ዕቅዶች አሉ።** በኦ-ኤስ-ኤስ-ኢ( OSSE) በኩል አነስተኛ ገቢ ላላቸው የሚደረገው ሎ ኢንካም ኢንቬስትመንት ፋንድ (Low Income Investment Fund (LIIF) የተባለው የገንዘብ አበርክቶ፤ በ2020 ለኩዋሊቲ ቻይልድ ኬር ፋንድ(Quality Child Care Fund )እገዛ በማድረግ 1,000 ህጻናትን የሚያስተናግዱ የህጻናት መዋያዎችን ይጨምራል። ኩን (QIN)ደግሞ (በግኝት 4 መ እንደተገለጸው) ሌላው የገንዘብ አበርክቶ ምንጭ ሆኖ የህጻናት መዋያዎች ተቋሞቻቸውን እንዲያሻሽሉ፤ የሚሰጡትን የትምህርትና እንክብካቤ ጥራት ከፍ እንዲያደርጉ፡ ቤተሰቦችን ይደግፋል ዕድገት እንዲገኝ ይሰራል። የዲስትሪክቱ ልዩ ትኩረት ኩንን አጎልብቶ ሌሎች ተጨማሪ 166 የህጻናት መዋያዎችን መጨመር ነው። በተጨማሪም የኢ-ኤል-ኪው-ኤፍ (ELQF ) ዓላማ ጥራት ያላቸው 625 የህጻናት መዋያዎች 2020 መጨረሻ ላይ በቤቶች(wards)7 እና 8 መጨመር ነው።[72]

**ጥራት ያለው የህጻናት መዋያ ለማግኘት (ACCESS TO QUALITY CHILD CARE EXPANSION (A2Q)**

በህዳር ወር 2019፤ ኤ2ኪው (A2Q) የገንዘብ እርዳታ፡ ከተመደበለት ግዜ አስር ወራት በፊት፤ ለ 39 አገልግሎት ሰጪዎች በ44 በተከፋፈሉ አገባቦች፤በስመንት ቤቶች( wards) 1,000 አዳዲስ የህጻናት መዋያ ቦታዎች እንዲጀመሩ አድርጓል። በተጨማሪም ዲስትሪክቱ 10 ተጨማሪ አበርክቶች ለሌሎች ስምንት በማበርከት ተጨማሪ 150 መዋያዎችን ለመጀመር ተስፋ አድርጓል።

**ዘ እርሊ ለርኒንግ ኳሊቲ ፋንድ (THE EARLY LEARNING QUALITY FUND (ELQF)[73]**

ኢ-ኤል-ኪው-ኤፍ ( ELQF) የልጆች እድገት ተቋሞች የሰላም ዋስትና ያለው፡ ጥራቱ የተጠበቀ የህጻናት መዋያዎች በተለይም እድሚያቸው ከልደት እስከ ሶስት ለሆኑ፡ በ ቤቶች (wards) 7 እና 8 ለሚኖሩ አገልግሎት ሰጪዎቹ የተመደበ ሆኖ፤ ደህንነታቸው የተጠበቀ፣ ጥራት ያላቸው የህጻናት መዋያዎች በማሻሻል፤ ለአደጋ የተጋለጡና ማግኘት ከሚገባቸው አገልግሎት በታች ሲያገኙ የቆዩ ህጻናትን ማገዝ ነው። ኢ-ኤል-ኪው-ኤፍ ( ELQF) አገልግሎት ሰጪዎች ተቋሞቻቸውን እንዲያሻሻሉ፤ ምሕረት ሊደረግበት የሚችል ብድር በመስጠት፤ የቴክኒክና የገንዘብ እርዳታ ያደርጋል። የዚህ የማሻሸያ ፕሮግራም ዓላማ፤ አገልግሎት ሰጪዎች ከፍተኛ ጥራት ያለው ካፒታል ኳሊቲ (Capital Quality ) በሚጠይቀውና የኢ-ኤች-ኤስ ደረጃ ላይ እንዲደርሱ የሚያግዝ ነው።

**መሪ ጥያቄ፤** Whatየህጻናት መዋያዎችና የህጻናት ትምህርት ቦታዎችን ለማሻሻል ምን የሚደረግ ፈጠራዊ ጥረት አለ?

**ግኝት 8 ሐ፤ ከ ቤናም ፋሚሊ ፋውንዴሽን (Bainum Family Foundation ) ጋር መንግስታዊና ግላዊ ሽርክና በመፍጠር፤ ዲስትሪክቱ፤ የቤት ውስጥ የህጻናት መዋያዎችንና የህጻናት ዕድገት ማእከሎችን ለማሻሻል ሁለት መሪ ዶኩመንቶችን አዘጋጅቷል።**እነኚህ ነጻ መምሪያዎች፣ የምስረታ ሃሳቦች (the Design Recommations )፣ የህጻናት የቤት ውስጥ ዕድገት (Child Development Home )ና የተስፋፋ የህጻናት የቤት እድገት (Child Development Home)(http://bainumfdn.org/wp-

---

[70] Bainum Family Foundation, *Early Learning Supply and Demand in the District of Columbia: Using Data to Identify Critical Gaps*, 2018.
[71] Bainum Family Foundation, *Infants and Toddlers in the District of Columbia: A Statistical Look at Needs and Disparities*, 2015.
[72] Bainum Family Foundation, *Early Learning Supply and Demand in the District of Columbia: Using Data to Identify Critical Gaps*, 2018.
[73] Bainum Family Foundation, *Supporting Facility Improvements for D.C. Providers Through the Early Learning Quality Fund*, www.bainumfdn.org.

content/uploads/2018/03/ELQF_Design-Recommendations_Home_Feb-2018.pdf) እና የምስረታ ሃሳቦች፣ የህጻናት የአድገት ማእከሎች (http://bainumfdn.org/wp-content/uploads/2018/03/ELQF_Design-Recommendations_Center_Feb-2018.pdf) የወቅቱ አገልግሎት ሰጪዎችና ወደፊት አገልግሎት ሰጪ ለመሆን ተስፋ ያላቸው ለህጻናት ልጆች ጥሩ የእድገት አካባቢ ለመፍጠር መከተል ስለሚገባቸው መመርያዎች፤ መውሰድ ስለሚገባቸው እርምጃዎች ፤ በአጠቃላይ ይህን በተመለከተ ምን እንደሚያስፈልግ ለመረዳት እንዲችሉ ያግዛቸዋል።

**ግኝት 8 መ፤ የህጻናት ተቋሞችን ለማሻሻል አዳዲስ ዘዴዎች በስራ እየተተረጎሙ ናቸው።** በ ካፒታል ኳሊቲ (Capital Quality )ና በኩን( QIN)ና የሚሳተፉ የህጻናት የእድገት ማእከሎችና ቤቶች ተቋሞቻቸውን እንዲያሻሽሉ ድጋፍ ይሰጣቸዋል። በ ካፒታል ኳሊቲ (Capital Quality ) ስልጠናና ቴክኒካዊ እርዳታ በመሰጠት በኩል ሲተጋገዝ፤ በኩን( QIN) ደግሞ ተቋሞች ጥራታቸው የተጠበቀ እንዲሆን ይተጋገዛል፤ በተቋሞቹ ውስጥ ህጻናት ልጆች ቦታ እንዲያገኙም ይተባበራል። ዲስትሪክቱ በተጨማሪ፤ በዲቪዥን ኦፍ እርሊ ለርኒንግ (Division of Early Learning )የሚሰጡት የስራ ፍቃድ መመመርያዎችን በማሻሻል፤ የትምህርት አገልግሎት የሚሰጡ ተቋሞች ሁሉ ደህንነታቸው የተጠበቀ እንዲሆን ይሰራል። (https://bit.ly/2016licensingframework)።

***መሪ ጥያቄዎች***፤ የህጻናት ፕሮግራሞች ወይም ሌሎች ህጻናትን የሚመለከቱ ተቋሞች እንዲሻሻሉ ለማድረግ ምን ዕድሎች አሉ (ለምሳሌ የሚሰጡ አገልግሎቶችን በማሰባብሰብ)?

**ግኝት 8 ሰ፤ ከዲስትሪክቱ ጋር የሚተባበር ኢ-ሲ-አይ-ኤን (ECIN) የአእምሮ ጤነነትን በተመለከተ ምንጮች የሚገኙባቸውን ቦታዎችንና ወጣት ልጆችና ቤተሰቦቻቸው የተቀነባበረ እርዳታ ሊያገኙ የሚችሉበትን ይጠቁማል።** ኢ-ሲ-አይ-ኤን (ECIN )፤ የትምህርትና የጤና ባለሙያዎች፤ የማሕበረሰብ አደራጆች፤ ተማራማሪዎችና ጠበቃዎችን ያቀፈ ሆኖ ለቤተሰቦችና ለልጆች ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚዘልቅ እርዳታ የሚያደርግ ነው (https://www.ecin.org/)። በተጨማሪም፤ ዲ-ቢ-ኤች( DBH) ሄልቲ ፊውቸርስ (Healthy Futures) የተባለ ድርጅት በማስተዳደር፣ በማረጋገጫ የተደገፈ፣ዕድሜያቸው እስከ 5 ዓመት ለሚሆኑ ህጻናት ልጆች በህጻናቱ መዋያ ውስጥ የአእምሮ ጤነንት ምክር ይሰጣል። (https://dbh.dc.gov/service/children-youth-and-family-services).

***መሪ ጥያቄ***፤ በትምህርት ተቋሞቹ ውስጥ ያለው መረጃ ደካማና ሃያል ጎኖች ምንድናቸው?

**ግኝት 8 ረ፤ ምንም እንኳን ያሉት የትምህርትና የእንክብካቤ ዕድሎች በደንብ የተገመገመ ቢሆንም፤ በ ኢ-ሲ-ኢ (ECE ) ተቋሞች ውስጥ የቦታ ጥበት ወይም ጥራት በተመለከተ ያለው መለኪያ በጣም ዝቅተኛ ነው፤ (የፍቃድ መስጫያ መመርያዎች** በስተቀረ)።ይህም ብቻ ሳይሆን ስንቶች የህጻናት መዋያዎች ናቸው የስራ ፈቃድ ለማግኘት መሟላት የሚገባቸውን ሁሉ ያሟሉ የሚለውም በደንብ አልተገመገመም። ከዚህም በላይ ዲስትሪክቱ፤ በካፒታል ኳሊቲ( Capital Quality) የማይሳተፉ ወይም በ ፒኪፕ (PKEEP) ያልተወከሉ፤ በቤቶቻቸው ውስጥ ህጻናት ልጆችን ተቀብለው በግላቸው የሚንከባከቡ ጥራታቸው ምን ያህል እንደሆነ የተገመገመ ነገር የለም።

***መሪ ጥያቄ*:** ይህንን መረጃ ለማሻሻል የሚወሰድ እርምጃ አለን?

**ግኝት 8 ሰ፤ አዲስ የስራ ፍቃድ የመረጃ ሰርአት፤ የህጻናት ትምህርት የሚሰጥባቸውን ተቋሞች በአካል እየተሄደ የተጠና ጥናት በማሰባሰብ፤ ኦ-ኤስ-ኤስ-ኢ (OSSE) በእነዚህ ተቋሞች ላይ መሻሻል እንዲያደርግ የሚያስችለው ነው።** የአዲስ ልጆችን የእድገት ደረጃ ለመከታተል የስራ ፈቃድ እንዲያገኙ የሚፈቅድ መረጃ ያለበት ስርአት፡ ከገበያተኞች ክፍልና ከቁጥጥር ጉዳይ ክፍል ጋር ግኑኝነት እንዲኖር ከመስራቱም በላይ፤ የህንጻዎቹን ዕድሜና ሁኔታን ግምት ውስጥ በማስገባት አዲስ ልጆችን ለመቀበል አመቺ ናቸውን የሚለውን ጥያቄ መልስ የኦ-ኤስ-ኤስ-ኢ (OSSE) ሰራተኞች በፈቃድ ሰጪዎች ጉብኝትም ሆነ ከዛ በፊት መረጃውን እንዲያገኙ ይፈቅዳ በተጨማሪም፤ በዩኒቨርሲቲ ኦፍ ሺካጎና በአውንስ ኦፍ ፕሪቬንሽን ፋንድ( Ounce of Prevention Fund) በተፈጠረው የገና የህጻንነት ትምህርት አስፈላጊ ነገሮች የመለኪያ ስርአት (Early Education Essentials measurement system )፤ የህጻናት ትምህርት ሃላፊዎች በፕሮግራሞቻቸው ውስጥ የድርጅቶቹን ሁኔታዎችና አጋዥ አካባቢዎች ለመለካትና ለመገምገም ያስችላቸዋል።[74] ይህ መሳርያ፡ ኢላማ ከተደረገው ቲ-ኤ (TA ) ጋር ተሸኝቶ፤ ሃላፊዎችና ሰራተኞች የድርጅቶችን ሁኔታ ለማጠናከርና የልጆችን ትምህርትናን ችሎታን ለማሻሻል ይረዳቸዋል።

---

[74] University of Chicago and the Ounce of Prevention Fund (2018). *Early Education Essentials Illustrations of Strong Organizational Practices in Programs Poised for Improvement*, https://consortium.uchicago.edu/publications/early-education-essentials-illustrations-strong-organizational-practices-programs.

## ክፍል 9 ግኝቶች

# ጥራት ያለው የትምህርት አገልግሎትና እገዛ ለማድረግ በሚደረገው የገንዘብ አበርክቶና እገዛ ላይ ያሉት ጋሬጣዎችና እርዳታዎች ውጤታማ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውሉ የማድረግ ዕድሎች

***መሪ ጥያቄዎች፤*** የህጻናት ትምህርትን በተመለከተ በሚደረጉ የገንዘብ አበርክቶና ጥራት ያለው እገዛ ለማድረግ በሚሰጠው ድጋፍ ላይ በአሁኑ ወቅት ምን ጋሬጣዎች አሉ? ጥራት ያለው የትምህርት አገልግሎት ለመስጠትና እገዛ በማድረግ በኩል፤ በመንግስታዊ አስተዳደር ወይም ገንዘባዊ አሰረጫጨት ላይ እክል የሚፈጥሩ ወይም ጋሬጣ ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮች መለያ ጠባዮች ምን ድናቸው?

***ግኝት 9 ሀ፤ የትምህርት ባለሙያዎች በህጻናት ትምህርት ውስጥ መካፈል ካለባቸው ሊኖራቸው ስለሚገባው የእውቀትና የተሞክሮ ደረጃ ከፍ ያለ መሆን አለበት በሚሉና ባለሙያዎችን ለማቀብ ከተፈለገ መሟላት የሚገባቸውን ነገሮች ለቀቅ ማድረግ አስፈላጊ ነው በሚሉ መካከል ውጥረት አለ። በህጻናት ትምህርት ውስጥ በሶስቱም የትምህርት ክፍሎች ስላለው የትምህርት ባለሙያዎች መረጃ ባይኖርም*** ከሌሎች የአሜሪካ ከተሞች ይበልጥ በዲሲ መንግስታዊ ትምህርት ቤቶች (DCPS ) እና በዲሲ የቻርተር ትምህርት ቤቶች ውስጥ የመማህራን ወደ ስራው የመግባትና ስራውን ለቆ የመሄድ ቁጥር እጅግ ከፍተኛና ከአገሪቱ አማካይ ቁጥርም ከፍተኛው ነው።[75,76] Spe በተለይም ይህ የመማህራን ወይም የባለሙያዎች መውጣትና መግባት፤ ለአደጋ የተጋለጡ ናቸው በሚባሉትና ማግኘት ከሚገባቸው አገልግሎት በታች ሲያገኙ በቆዩት ልጆች ላይ አሉታዊ ውጤት ሲያደርግ ይታያል።[77]

#### በትምህርት ስራ ውስጥ ለሚገኘው የሰራተኛ ሃይል የሚደረግ እገዛ

ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምብያ (District of Columbia) አዲሱ የትምህርት ዓይነት የሚጠይቀውን አስፈላጊ ነገሮችን ለሚሟላት ለሰራተኞቹ፤ አስፈላጊ የስራ ስልጠናና ጥራት ያለው የእድገት ስልጠና በመስጠትና ሰራተኞች አስፈላጊው የማስተማርያ ዘዴዎችን በተመለከተ እውቀት እንዲገበዩ ከፍተኛ መዋእለ ንዋይ ሲያበረክትና የገንዘብ አበርክቶና ስኮላርሺፕ እንዲሁም ወደ ኦ-ኤስ-ኤስ-ኢ (OSSE’s DC Professional Development Information System) በነጻ የመግባት እድል ሲሰጥ ቆይቷል። መዋእለ ንዋዩም፡ ወደ ፒ-ዲ-አይ-ኤስ- (PDIS) (https://osse.dc.gov/page/professional-development-information-system-pdis); በነጻ መግባት እንዲሁም ወደ ኮረም፣ የኦንላይን የስልጠና ፕሮግራም ከሲ-ዲ-ኤ( CDA) የትምህርት ስራ ጋር ነጻ አገልግሎት በመስጠት ላይ ሲያውል ቆይቷል። (https://osse.dc.gov/publication/quorum-online-professional-development-resource)፤በተጨማሪም በትምህርታቸው ገፍተው ባለ ቢኤ ዲግሪ ለመሆን ወይም ተባባሪ ዲግሪ ማግኘት ለሚፈልጉ ሰራተኞቹ ቲች (T.E.A.C.H) ስኮላሺፕ (https://osse.dc.gov/teachscholarship)በመስጠትና  የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ደግሞ ፊርስት ስቴፕ ሲ-ዲ-ኤ ፕሮግራም ( First Step CDA Program)እንዲካፈሉ በማድረግ፤ አገር አቀፍ ተቀባይነት ያለውን ሲ-ዲ-ኤ (CDA) እንዲያጠናቅቁና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውንም ያስጨርሳቸውና የምስክር ወረቀት እንዲያገኙ ያደርጋል። (https://osse.dc.gov/firststep).

#### በህጻናት ትምህርት ስራ የተሰማራውን የሰራተኛ ሃይል የሚያጋጥሙት ጋሬጣዎች

የኢ-ሲ-ኢ( ECE) ባለሙያዎች፤  ለስራው አስፈላጊ ነው ወይም ስራው የሚጠይቀው እንዲህ ዓይነቱን ትምህርት ነው ብሎ የሚሰጣቸውን የተራቀቀ ትምህርት እንዴ ካገባደዱ በኋላ፤ ከፍተኛ ደሞዝ ወደሚከፍሉ ስራዎች መሄድ መፈለጋቸው የተለመደ ነው።[78] በተጨማሪም፤ ከኪንደርጋርተን እስከ 5ኛ ክፍል ድረስ፡ በመካከለኛው (middle )ትምህርት ቤትና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መማህራን በአማካይ ከልጆች ጋር በቀጥታ የሚገናኙት በቀን 6.5 ሰዓታት ሲሆን በህጻናት መዋያ የሚሰሩት የኢ-ሲ-ኢ( ECE) ባለሙያዎች ደግሞ (ማለትም ከልደት እስከ ሶስት ዓመት እድሜ ያላቸውን ልጆች የሚንከባከቡ)ና በሲ-ቢ-ኦ(CBO) ከልደት እስከ አምስት ዓመት ዕድሜ ያላቸውን ልጆች የሚንከባከቡ ፤ሙሉ የስራ ግዜአቸውን ከህጻናቱ ጋር ነው የሚያሳልፉት። ይህ

---

[75] District of Columbia State Board of Education, *Teacher and Principal Turnover in Public Schools in the District of Columbia. DC State Board of Education*, 2018.
[76] Bainum Family Foundation, *The District of Columbia’s Preschool Development Grant Birth Through Five: Synthesis of Needs Assessment*, 2019.
[77] District of Columbia State Board of Education. *Teacher and Principal Turnover in Public Schools in the District of Columbia. DC State Board of Education*, 2018.
[78] Key informant interviews, 2019.

ከደሞዝ ልዩነት ጋር ተደምሮ፤ በህጻናት ትምህርት ላይ በተሳተፉት ባለሙያዎች ላይ ያለውን በቦታው የመቆየት ፍላጎት እንዲያሽቆለቁል ያደርጋል።

ሌላው የህጻናት ትምህርት ውስጥ የሚሳተፉ ባለሙያዎችን ማቀብ ያለመቻል ችግር ደግሞ፤ ብድርን ይቅርታ የማድረግ ፕሮግራም ነው። ከኪንደርጋርተን እስከ 12ኛ ክፍል የሚያስተምሩ መማህራን፤ በዚህ ብድር ይቅርታ በሚያደርግ (Teacher Loan Forgiveness Program (TLFP) ፕሮግራም ውስጥ መሳተፍ ይችላሉ፤ በቅናሽም ይሁን ካለቅናሽ ከማእከላይ መንግስት የተበደሩትን እስከ $17,500 የሚደርስ ብድራቸውን፤ መምህርዋ ወይም መምህሩ ለአምስት ዓመታት፤ በተከታታይ ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው ቤተሰቦች የሆኑ ልጆች በሚማሩባቸው ትምህርት ቤቶች ካስተማሩና በትምህርት አገልግሎት ሰጪ ቦታዎች ከሰሩ እንዲሁም አንዳንድ ሌሎች ጥያቄዎችን ካሟሉ፤ ከመክፈል ነጻ ይሆናሉ።[79]

**ግኝት 9 ለ፤ በወቅቱ በዲስትሪክቱ ገንዘብ የሚተዳደሩ ፕሮግራሞችና ጣልቃ የመግባት ፕሮግራሞች የሚከተሉት ናቸው፤ ሄልቲ ፉቸርስ ፕሮግራም(Healthy Futures)፤ የዲሲ ማህበራዊ፡ ስሜታዊና የህጻናት እድገት ፕሮግራም ( DC Social, Emotional and Early Development (DC SEED) ፤ የአእምሮ ጤንነት የምክር ማጠናከርያ ፕሮግራም። ይሁንና ገና አያሌ የልጆችና የወላጆች ፍላጎቶችን መሟላት የሚያስፈጋቸው ጉዳዮች አሉ።** በግኝት 8 ሰ እንደተገለጸው፤ ሄልቲ ፉቸርስ ( Healthy Futures)፤ የህጻናትን ማህበራዊና ስሜታዊ እድገቶችን የሚመለከት የአእምሮ ጤነንት ምክር ሰጪ ፕሮግራም ነው። በዲ-ቢ-ኤች( DBH) ና በ ዲሲ ሲድ (DC SEED)የሚተዳደር፤ በማስረጃ የተደገፈ፣የህጻናት ልጆችን የሚያግዝ ልዩ ጣልቃ የመግባት ፕሮግራም ነው።እነኚህ ፕሮግራሞች የአእምሮ ጤንነት ችግር ላጋጠማቸው ልጆች አንገብጋቢ ናቸው።

ዲስትሪክቱ፤ እነኚህ የህጻናት የአእምሮ ጤነነት ፕሮግራሞች እንዲጠናከሩ በመስራት ላይ እንዳለ፤ አገልግሎት ሰጪዎች ግን በእኩልነት በሁሉም ቦታዎች ተሰራጭተው የሚያገለግሉ አይደሉም። የ2016 የማህበረሰቡ የጤና ፍላጎቶች ግምገማ (Community Health Needs Assessment) እንዳሳየው የጤናና የአእምሮ ጤነነት ፕሮግራሞች፤በቤቶች 5፣ 6፣ 7 እና 8[80] ላሉ ተቀማጮች በእኩልነት ስለማይዳረሱ በተቀማጮች ላይ በአሉታዊ መንገድ ስምብራት እየተወ ነው፡ ይህም ግልጽ የሆነው በተደረጉ ቃለመጠይቆች ነው። አያሌ ገንዘባዊ እንቅፋቶችም ግልጽ ሆነዋል፡

- የጠባይ ጤንነት ባለሙያዎችና የትምህርት ቤቶች ሃላፊዎች፤ በህጻናት የ አእምሮ ጤንነት ፕሮግራም ውስጥ የሚሰሩ ባለሞያዎች፤ ከትምህርት ቤት ውጪ በሌሎች ቦታዎች ሲሰሩ ከሚከፈሉት በታች በትምህርት ቤት ውስጥ ሲሆኑ መከፈላቸው ያሳስባቸዋል።ይህም የአእምሮ አገልግሎት ማግኘት በሚፈልጉና ወደ አገልግሎቱ ለመመላለስ የህዝብ ማመላለሻዎችን በሚጠቀሙ ና የራሳቸውን የማመላለሻ አገልግሎት በሚጠቀሙ መካከል ልዩነት ይፈጥራል። ስለዚህ በፕሮግራሙ መጠቀም የሚገባቸው ቤተሰቦች ወደቦታው ለመድረስ አያሌ የማመላለሻ ዘዴዎችን መጠቀም ስላለባቸው በፕሮግራሙ ሳይጠቀሙ እንደሚቀሩ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።
- ቁልፍ የሆኑ መረጃ ሰጪዎች፡ በተጨማሪ ያለው የስራ ቅርጽ፤ የተለያዩ አገልግሎት ሰጪዎች -የመንግስትም ይሁኑ ሌሎች ሽሪክ ተቋሞች- አብሮ የመስራት ዕድል እንደማይሰጥ ጠቁመዋል; ይህም የሚከተሉትን ያጠቃልላል፣
  - በቂ ቁጥር ያላቸው የትምህርት (ECE) ባለሙያዎች በአእምሮ ደህንነት ትምህርት መሰልጠናቸውን ማረጋገጥ
  - የወንነጀል ፍርድ ቤቶችን፣ ትምህርታዊ ተቋሞችና የህዝብ ጤና ጥበቃና የአእምሮ ጤነንትን በተመለከተ ያሉትን መረጃዎች አንድ ላይ በማቀነባበር አንድ በቤተብ ላይ ያነጣጠረ፤ አጠቃላይና ችግሮች ከመታየታቸው በፊት የማስወገድ ዓላማ ያለው ስርዓት መፍጠር
  - ከ ስትሮንግ ስታርት (Strong Start )፤ ሄልቲ ሃርት (Healthy Start) ና ከኢ-ኤች-ኤስ (EHS.) ፕሮግራሞችን ማስተባበር
- ቁልፍ የሆኑ መረጃ ሰጪዎች በተጨማሪ የመዘገቡት ሌላ ነገር ከነበር፤ የቤተሰቦችን የሽግግር ወቅት ግምት ውስጥ የሚያስገባ በቂ እገዛ አለመደረጉን ነው (ለምሳሌ ቤተሰቦች በቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ (TANF) ውስጥ ከገቡበት ግዜ ጀምሮ ስራ እስከሚያገኙበት ግዜ ድረስ)። ሰራተኛ ቤተሰቦች በቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ (TANF) ውስጥ ባሉበት ግዜ ከፍተኛ የገቢ ውድቀት እንደሚያጋጥማቸውና በቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ (TANF) መቆየት የሚችሉበት ግዜ ስለተገባደደ ያጡትን እንደገና ለመገንባት እንደማይችሉ ገልጽዋል።

[79] Teacher Loan Forgiveness Program Application, *William D. Ford Federal Direct Loan Direct Loan Program and Federal Family Education Loan FFEL Program*, 2019.
[80] Community Health Needs Assessment, District of Columbia, 2019. *DC Health Maters Collaborative*. June 28, 2019, www.dchealthmaters.org.

## ክፍል 10 ግኝቶች

# የመሸጋገርያ እርዳታና ያሉት ቀዳዳዎች

***መሪ ጥያቄ፤*** *በሁሉም ዓይነት የትምህርትና የእንክብካቤ ቦታ ህጻናት ልጆችን የሚረዱ መሸጋገርያ/ፖሊሲዎችና እርምጃዎች አሉን?*

**ግኝት 10 ሀ፤ ዲስትሪክቱ ፤ መላውን ከተማ የሚያጠቃልል ኤም-ኦ-ኤ( MOA) ፈጥሮ ይህም በኢ-ኤስ-ኤስ ኤ ታይትል I (ESSA Title I )ትብብር አስፈላጊነት ላይ ያተኮረ እንዲሆን አድርጓል።** ህጻናት ልጆች ወደ ቅድመ-ትምህርት ና ኪንደርጋርተን ሲሸጋገሩ ለመርዳት፤ ኢ-ኤስ-ኤስ-ኤ( ESSA) የ ኤል-ኢ-ኤ (LEA)የታትል I( Title I) የገንዘብ አበርክቶ ማግኘትንና ኤም-ኦ-ኤ( MOA) ከኤች-ኤስ( HS)እና ከሌሎች የትምህርት ፕሮግራሞች ጋር በመተባበር ላይ መሆኑን መፈረም አለበት።

ኤል-ኢ-ኤ (LEA) የኢ-ኤስ-ኤስ-ኤ( ESSA) ጥያቄዎችን በሚሟላት ላይ መሆኑን በመደገፍ፤ ኦ-ኤስ-ኤስ-ኢ (OSSE)፤ ከዲሲ ሄድ ስታርት ማህበር( DC Head Start Association -DCHSA) ጋር በመተባበር፤ ከዲሲ ህዝባዊ ቻርተር ትምህርት ቦርድ( DC Public Charter School Board )፣ ከፎካስ ዲሲ( FOCUS DC)፣ ከ DC የወጣት ልጆች ትምህርት ማህበር( Association for the Education of Young Children (DCAEYC)፤ የአሜሪካ የትምህርት ሚኒስቴር የክልል ትምህርት ላቦራቶሪ (US Department of Education's Regional Education Laboratory) እና በጉዳዩ ስሜት ያላቸው የኤል-ኢ-ኤ(LEA)አባሎች በስብሰባ እንዲሳተፉ አድርጓል። ከኤች-ኤስ( HS) ና ከሌሎች የህጻናት መዋያዎች ጋር በመተባበር፤ ህጻናት የሚያደርጉትን የሽግግር መድረክ ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ ተካፋዮች፤ በወር አንድ ግዜ እየተገናኙ ተመክሮችንና ሃሳቦችን ተለዋውጠዋል። የቡድኑ ዓላማ፤ ከተማ አቀፍ የሆነ የኢም-ኦ-ኤ (MOA) ቅርጽ መንደፍና ይህም ኢል-ኢ-ኤ-ኤል(LEA) እንዴት ከኤች-ኤስ (HS)እና ከሌሎች የህጻናት ፕሮግራሞች ጋር እንደሚተባበር፤ ይህም በባለሙያዎች የጋራ እድገትና ቴክኒካዊ ድጋፍ ላይ ያተኮረ ሲሆን፤ አገልግሎቶችንና ግንኙነቶችን፤ የቤተሰብ በጉዳዩ ውስጥ ተካፋይ መሆንን፤ የትምህርት ፕሮግራሞችና መመርያዎች፤ መረጃና መዝገብ መካፈልንና የእንግሊዘኛ ቋንቋን ለመማር የሚፈጉን ማገዝን ያጠቃልላል። ኢል-ኢ-ኤ-ኤል(LEA) በከተማ አቀፉ ኤም-ኦ-ኤ (MOAs) ላይ ለመፈርምም ሆነ በተናጠል ከተለያዩ MOAና ከዲስትሪክቱ ሄድ ስታርት (Head Start )ጋር ለመፈርም ቢፈልግ ተቀባይነት አለው። ኤች-ኤስ-ኤ (HAS) እና ኤል-ኢ-ኤ (LEA)ሁለቱም በአሁኑ ወቅት፤ የማስተማር መመርያዎች እንዲያድጉ በማድረግና ቤተሰቦች በልጆቻቸው ትምህርት ላይ በደንብ ሙሉ በሙሉ ተካፋዮች እንዲሆኑ፡ የመረጃ መካፈልና ሽግግር እንዲኖር ለማድረግ፤ ለትብብር አስፍላጊ ናቸው የሚባሉትን ሁሉ በስራ ላይ እየተረጎሙ ናቸው።

**ግኝት 10 ለ፤ ዲስትሪክቱ፤ ኤች-ኤስ-ኤ (HAS) በህጻናት መዋያ የተመዘገቡ ህጻናት መረጃዎችንና መዝገቦችን፤ በወላጆች ፈቃድ በመሞርከዝ፤ ዋስትና ባለው፤ ስነስርአት በተከተለ አገባብ ወደ ኢል-ኢ-ኤ(LEA) ለማስተላለፍ የሚያስችለውን መንገድ እየቀየሰ ነው።** ኤች-ኤስ-ኤ (HSA) ቀደም ሲሉ በተለያዩ የህጻናት ፕሮግራሞች ሲካፈሉ የቆዩን አሁን ወደ LEA በመሸጋገር ላይ ያሉ ልጆችን መረጃ ከሌሎች ጋር ይካፈላል። ይህም LEAን የአዲስ መጪዎች ያለፈ ተመክሮን ለመገምገም ያስችለዋል፤ የአስተማሪዎች ምድባን፤ ከቤተሰቦች ጋር ሊኖር ስለሚገባው ግኑኝነትና የሚታዩ የጠባይ እክሎች ካሉ ዕቅድ ለማውጣትና የHS ፕሮግራሞች ልጆች በየግላቸው ምን የሚያስፈልጋቸው ነገር እንዳለ ለመገምገም ይረዳል።

ዲስትሪክቱ፤ ለመጀመርያ ግዜ ይህንን አንድ ላይ የተሰባሰበ መረጃን የተካፈለው በትምህርት ዓመት ከ2018-19 ባለው ግዜ ሲሆን፤ ከ LEA፤ ከ HAS እና ከሌሎች የህጻናት መዋያ ፕሮግራሞች ጋር ነው። የቀረበው መረጃ፤ ከ2017-18 ባለው የትምህርት ዓመት ውስጥ፤ ከያንዳንዱ የህጻናት እድገት ወይም ኤች-ኤስ( HS ) ፕሮግራም ምን ያህል ህጻናት እንደተሳተፉ፤ እንዲሁም በ2018-19 ባለው የትምህርት ዓመት በ LEA ምን ያህል ተማሪዎች እንደተሳተፉ ይጠቁማል። ይህ ቁጥርም ሊያ (LEA) የትኞቹ ፕሮግራሞች እንደሆኑ በርካታ ህጻናትን የሚልኩላቸው እንዲገመግሙ በማድረግ፤ የሚያስፈልጉትን ፕሮግራሞች ለመምረጥና ለማስተባበር እንዲሁም መመርያዎችን፤ የልዩ ትምህርት ምደባን፤ የጤና ጥበቃ አገልግሎቶችን፤ ለቤተሰብ የሚደረጉ እገዛዎችንና ሌሎች እገዛዎችን ለማጠናከር ይረዳል።[81,82]

ቁልፍ ለሆኑ መረጃ ሰጪዎች የተደረጉት ቃለመጠይቆች ግልጽ እንዳደርጉት፤ ምቹ በሆኑ ሁኔታዎች፤ ከአሁን ቀደም በህጻናት ፕሮግራሞች ውስጥ የነበሩ ህጻናት ወደ ሊያ (LEA) ሲመጡ፤ የትምህርቱን ሁኔታ ለእያንዳንዱ ህጻን አገልግሎት እንዲሰጥ ለመድረግ፤ የህጻናቱ ያለፈ የትምህርትና የቤተሰብ ታሪክ መረጃ እንደሚያስፈልገው ያመለክታሉ። ይሁንና እነኚህን መረጃዎች በመካፈል ረገድ በአስተማሪዎች መካከል አንድ ዓይነት እቀባ ነበር።ያለፉ ነገሮችን ማየት ምናልባት አስተያየት በመቀየር ላይ ሊሰራ ይችላል የሚሉ አሉ።

---

[81] District of Columbia Office of the State Superintendent of Education, My School DC, *How Does a Family Pick a Public School and Use the DC School Lottery? Train-the-Trainer Session for Early Childhood Providers* FY2019-20, Lottery, 2019.

[82] District of Columbia Office of the State Superintendent of Education, My School DC, *My School DC Application Instructions*, 2019.

በነ አድራጊዎች ግን አስተማሪዎች ያለፉ የልጆችና የቤተሰቦች መዝገቦችንና መረጃዎችን እንዴት መቀበል እንዲሚችሉና እንዴት ሊጠቀሙባቸው እንደሚችሉ የሚያስረዳ አንድ ዓይነት ስልጠና ሊሰጣቸው ይገባል ይላሉ።

**ግኝት 10 ሀ፤ ዲስትሪክቱ፤ የተባበረ የሽግግር አገልግሎቶች የመስጠት ስርዓት ለመገንባት አንድ መላውን ከተማ የሚያቅፍ ሽርክና እንዲኖር እየሰራ ነው።** ልጆች ከህጻናት መዋያዎች ወደ ቅድመ ኪንደርጋርተን ወይም ወደ ኪንደርጋርተን ሲሸጋገሩ፤ የዲስትሪክቱ ተቋሞችና ድርጅቶች ለምሳሌ ከOSSE፤ QIN ፤ DCPS Early Stages ከመሳሰሉት ጋር ሽርክና በመፍጠር ለቤተሰቦች እርዳታ ያደርጋሉ። በ HS ወይም በሌሎች የህጻናት መዋያዎች ያሉ ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦች፤ የማይ ስኩል ዲሲ( My School DC) የጋራ የሎተሪ አጠቃቀምን በመጠቀም በህዝባዊ የቅድመ-ትምህርት ፕሮግራሞች ወይም ከዲሲ የትምህርት ቤቶች ክልል ውጪ ከኪንደርጋርተን እስከ 12ኛ ክፍል ባሏቸው ትምህርት ቤቶች ለማመልከትና ቦታ ለማግኘት ይችላሉ። ሁለቱም LEA እና HS የ MOA የሽግግር ጥያቄዎችን ለሚሟላት፤ OSSE፤ የMy School DC Lotteryን በተመለከተ ለ HS ቤተሰቦችና ሰራተኞች [83,84] ፤ በኦንላይን ባሉ ምንጮች፤ በአካል በሚኬድባቸው የተቀናበሩ ዝግጅቶች፤ በ አዲስ መልክ በተዘጋጀው የሎተሪ ማውጫ መሳርያና አስተማሪውን ማስተማር በሚሉ ፕሮግራሞች፤ የኤችኤስ ቤተሰቦችና ሰራተኞችን ይደግፋል። የሽግግር እገዛዎች፤ በህጻናት መዋያዎች መካከል ቀጣይነት እንዲኖር የሚያግዝ ሆኖ ወደ ህዝባዊ ቅደ- ኪንደርጋርተን የሚደረግ ሽግግር እንዲመቻችና፤ የእድገት መጎተት ችግርና ስንክልና ያለባቸውን ልጆች የሽግግር ወቅት ማቀላጠፍ፤ቤተሰቦችና ልጆችም ለእነዚህ ለውጦች ዝግጁ ሆነው እንዲገኙ የሚያገዛቸውን ማሸጋገሪያ ዕቅድ ማውጣትን ያጠቃልላሉ።

## የወላጆች አስተያየት

በ PDG ቤተሰቦችን የመስማት ስብስባ፤ ተካፋዮች በትምህርት ቤት ሽግግር ወቅት ስለታዩ ሰኬታማ ውጤቶችና መሻሻል ስለሚገባቸው ጉዳዮች ተወያይተዋል። አብዛኛዎቹ ልጆቻቸው የእድገት መጎተት ችግር ወይም ስንክልና የሌላቸው ቤተሰቦች ፤ ልጆቻቸውን ከህጻናት መዋያዎች ወደ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ለማሻገር የተደረገው የሽግግር ወቅት በተዛማጅ በጣም ጥሩ እንደነበር ይገልጻሉ። በአነዚህ የቤተሰብ ስብሰባዎች ላይ የታየው የቤተሰብ እርካታ በ QIN የህጻናት እድገት ተቋሞች ላይ ያተኮረ ነበር።ቤተሰቦች፤ በእነዚህ ተቋሞች ልጆችን ለማዘጋጀት በተደረገው የማስተማርና የትምህርት ደረጃ ላይ ያላቸውን እርካታ የገለጹ ሲሆኑ ተቋሞቹ አስፈላጊውን መሰረት በመጣል ልጆቹ አስፈላጊው የሽግግር ችሎታ እንዲኖራቸው አድርገዋል ብለዋል። በተጨማሪም፤ በስብሰባው የነበሩ ቤተሰቦች፤ የ QIN የቤተሰቦች ተካፋይነት ባለሙያዎች ስህተቶች እንዲታረሙ በግልጽ የሚናገሩ ጠቃሚ ሽሪኮች መሆናቸውን ሲናገሩ በሽግግር ወቅትም ቤተሰቦችን፣አስተማሪዎችን፤ አስተዳዳሪዎችንና ሰራተኞችን የሚያግዙ ናቸው ብለዋል።

የዲስትሪክቱ የሎተሪው ስርዓት፤ ቤተሰቦች ልጆቻቸውን በዲሲ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ወይም በህዝባዊ የቻርተር ትምህርት ቤቶች ውስጥ፤ በህጻናት መዋያ ውስጥ እንዲቀጥሉ ወይም ወደ ቅደመ- ኪንደርጋርተን 3 ወይም ቅድመ -ኪንደርጋርተን 4 እንዲሻገሩ ለመወስን ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። ቤተሰቦች፤ በሚደረገው የሎተሪ ምርጫ ወቅት፤ አብዛኛውን ግዜ፤ በተለይ የቅድመ-ኪንደርጋርተን 3ን የሚመለከት ከሆን፤ የመጀመርያ ምርጫቸውን ለማግኘት ያላቸው እድል ከፍተኛ ነው። በአጠቃላይ፤ መርጭ በእልቶሪ መደረጉ ጥሩ ነው ይላሉ ምክንያቱም ሎተሪውፍትሃዊ ነው፤ አያዳላምም ግን በብዙ ምክንያቶች አካሄዱ በጣም አስቸጋሪ ነው ይላሉ። መጀመርያ፤ ብዙ ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦች፤ በአድሜ አነስ ያሉት ልጆቻቸው በትልቅየው ትምህርት ቤት ውስጥ ለመግባት አለመቻላቸው ያበሳጫቸዋል። በተጨማሪም፤ ይህ የልጆች በየትምህርት ቤቱ መበታተን፤ ልጆቹን በሙሉ ወደ ትምህርት ቤት በመውሰድና በመመለስ የሚወስደው ግዜ በተለይም ስራ ላለውና ህዝባዊ ማማላለሻዎችን ለሚጠቀም ሰው በጣም አስቸጋሪ ነው። ሶስተኛ፤ ቤተሰቦች፤ በሎተሪው ማመልከቻ ወቅት፤ አያሌ የትምህርት ቤቶች ምርጫዎችን እንዲዘረዝሩ ይጠየቃሉ፤ በመጨረሻም በአንደኛነት የመረጡትን ትምህርት ቤት ካላገኙ፤ ተራቸውን እንዲጠብቁ ይጠየቃሉ፤ ሆኖም ግን በዚህ የጥበቃ ዝርዝር ውስጥ ያሉ ሰዎች ትምህርት ቤት የሚደርሳቸው ትምህርት ቤት ካልሞላ በስተቀር ነው፤ አንዳንዴም በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ቦታ የሚገኘው ትምህርት ቤቱ በተከፈተበት ስሞን ብቻ ነው። በዛ ላይ በጥበቃ እድል ውስጥ የገባ ሰው የሚመረጠው ከወጣ በ rolling basis ወይም ሁሉም ሎተሪ የደረሳቸው ጉዳይ ከተጠና በኋላ የሚደርግ ምርጫ ነው። ትምህርት ከተጀመረ በኋላ ይሚደረግ ምደባ ግዜ የማይሰጥ ስልሆነ ወላጆች የስራ ሰዓታቸው መለወጥ ላይ ችግር ይፈጥባቸዋል; እነኚህ የጥበቃ ግዚይት ምደባዎች ቀደም ብለው ቢደረጉ የቤተሰቦች ምርጫ ነው።

በባለሙያዎች የትኩረት ቡድኖችና በቤተሰብ የመሰማት ስብሰባዎች ላይ የተካፈሉት ተሳታፊዎች፤ የእድገት መዘግየት ችግር ያላባቸው ልጆችና ስንክልና ያለባቸው ልጆችን ወደ ሌሎች የትምህርት ተቋሞች የማሸጋገር ሂደትን በተመለከተ የሰጡት አስተያየት የተደባለቀ ነው። ስትሮንግ ስታርት( Strong Start) እና አርሊ ስቴጅስ(Early Stages) የልጆችን መረጃዎች በሚያስተላልፉበት ወቅት ተባብሮ የመስራት ምንም ችግር እንዳልነበራቸው ሲያስረዱ፤ በሁለቱ ፕሮግራሞች ስር ያሉት የጉዳዮች አስተባባሪዎችና አገልግሎት ሰጪዎች፤ የልጆቹን መዛግብትና የድህረ ታሪክ መረጃዎችን በማስተላለፍ በኩል ምንም ችግር እንዳላገጠማቸው ይገልጻሉ። ይሁንና እነኘያ የእድገት መጎተት ችግር ያለባቸውን ልጆች፤ ከ ልደት እስከ 3 ዓመት እድሜ ያላቸው ህጻናት ከሚውሉበት መዋያዎች፤ ከ3 ዓመት በላይ ዕድሜ ህጻናት ወደ አሉበት ትምህርት ቤቶች በማሸጋገር ወቅት ከፍተኛ የአገልግሎት ቅነሳ እንደታየ ታውቋል። ተካፋዮች እንዳሉት፤

---

[83] District of Columbia Office of the State Superintendent of Education, My School DC, *How Does a Family Pick a Public School and Use the DC School Lottery? Train-the-Trainer Session for Early Childhood Providers* FY2019-20, Lottery, 2019.

[84] District of Columbia Office of the State Superintendent of Education, My School DC, *My School DC Application Instructions*, 2019.

አንዳንድ ልጆች፤ LEA ሊያቀርብላቸው ከሚችለው አገልግሎት በላይ አገልግሎት እንደሚያስፈጋቸው ሲጠቁሙ፤ በተለይ አንድ ባለሙያ እንዳለው፤ አንድ ልጅ በትምህርት ቤት አካቢ ስላለ፤ የመማርና የአካል እንቅስቃሴ ችግሩን አጠፋ ማለት አይቻልም።

### ግኝት 10 መ፤ ቀጣይ የሆነና የተባበረ የሽግግር ሁኔታ በመላው የህጻናት ትምህርት በሚሰጥባቸው ቦታዎች ሁሉ የለም

ከአንድ የትምህርት ቦታ ወደ ሌላው ሽግግር በሚደረግበት ወቅት፤ በክፍል ሐ አገልግሎት የሚያገኙና ወደ ክፍል ለ ለሚሸጋገሩ ልጆች በሙሉ ቀጣይ የሆነ፡ ውጤታማ፤ የተቀናጀ ሽግግር እንዲደረግላቸው በአይዲያ( IDEA)ተውክሎላቸዋል ) ።የሽግግር እገዛዎች፤ በ HSA እና LEA እስከ ESSA MOA ድረስ እንዳሉ ሁነው፤ የመረጃ መለዋውጥ አሰራር ግን በመላው ዲስትሪክት እንድ ዓይነት ነው ወይም በአንድ ዓይነት አሰረጫጨት ይሰራጫል ማለት አይደለም።

ልጆችን ከ ክፍል ሐ ወደ ከፍል ለ በተሳካ መልኩ ለማጨጋገር የሚያስችል ዕድል አለ። ያሉትን የፕሮግራም መረጃዎች ሁሉ አቅጣጫ እንዲይዙ የሚያደርግና የተለያዩ ፍላጎቶች ያሏቸው ልጆች መረጃ ለሁሉም እንዲዳረስ የሚያግዝ አዲስ ስርአት መፍጠር ነው።

## ክፍል 11 ግኝቶች

# የስርዓት መዋሃሃድና የውስጥ ተቋሞች ትብብር

***መሪ ጥያቄ፤*** *ወጣት ልጆችንና ቤተሰቦችን የሚያግዙ ውጤታማና ኢጋዥ የሆኑ ምን የውስጥ ተቋሞች አሉ?*

አያሌ የዲሲ መንግስታዊ ተቋሞች ተወካዮችን የሚጨምር፤ 17 (አስራ ሰባት) አባሎች ያለው ትራይቭ ባይ ፋይቭ ዲሲ (Thrive by Five DC) ምክርቤት፤የዲስትሪክቱንና ማህበረሰብ -ጠቀስ የሆነን እድገት የሚለካው በእናቶችና በህጻናት ልጆች የጤንነት ደረጃ ነው።\ በተጨማሪም፤ ምክርቤቱ እድገትን የሚመዝነው ዕድሜያቸው ከልደት እስከ 5 ዓመት ለሆኑ ህጻናት በሚደረገው ጤናማ የጤነነት እድገት ነው።ትራይቭ ባይ ፋይቭ ዲሲ (Thrive by Five DC) አስተባባሪ ምክር ቤት፤ የህጻናት መዋያዎች ውጤታማነት ለመጨመር፤ ትብብር፡ ኦቅድ ማነጠርና ማስተካከል ለማድረግ ፤ ፖሊሲዎችን በማውጣትና ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች በሚመለከት ሃሳብ ያቀርባል።

***መሪ ጥያቄ:*** *እንዴት ነው እንዲያድጉ የተደረጉት? ወደ ሌሎች ቦታዎች እንዲዛመቱ ምን መደረግ አለበት?*

***ግኝት 11 ለ፤ ዲስትሪክቱ፤ በውስጥ ተቋሞች መካከል ያለውን ትብብር በሚመለከት በ ኤም-ኦ-ኤ( MOA)ና በመግባባት ማስታወሻ ሜሞራንደም ኦፍ አንደርስታንዲንግ(Memorandums of Understanding (MOUs) በኩል እድገት አድርጓል።*** በተጨማሪም በአጠቃላይ ከልደት እስከ 5 ዓመት ዕድሜ ያላቸው ህጻናት ልጆች በሚማሩበት የትምህርት አካባቢ ተመሳሳይ እርምጃዎችን ወስዷል።. በዲስትሪክቱ ውስጥ ያሉ መሪዎች፤ እንደ አንድ የፍላጎት ግምገማ ቁልፍ መረጃ ሰጪዎች፤ ቃለመጠይቅ ሲደረግላቸው፤ በውስጥ ተቋሞችና በማህበረሰቡ መካከል ያለውን የትብብር ዕድል ከፍ ስለማድረግ በጣም ደስተኞች እንደሆኑ አስረድተዋል። አንዳንዴ፤ በዲስትሪክቱ ያሉት ተቋሞችና ለትርፍ የማይሰሩ ድርጅቶችን ልክ " ብዙ እውቀት ያላቸው ብቸኞች" እንደሆኑ አድረገው ይመለከቷቸው ነበር። ምክንያቱም "የተቋሞቻቸውን ዓላማና ስራ በሚገባ ሲያሟሉ"፤ ከሌሎች ጋር ቢተባበሩ ምን ያህል ውጤታማ ስራ ሊያከናውኑ እንደሚችሉ አልተገነዘቡም። በውስጥ ድርጅቶች መካከል ትብብር ሲኖር፤ በዲስትሪክቱ ባሉት የልጆች ሁኔታ ላይ ጥሩ ውጤት ስለሚያስከትል ይህንን ለማሻሻል ይጠቅማሉ የተባሉ አንዳንድ ሃስቦች ከታች ተዘርዝረዋል፡፡

- ሜዲኬድ(Medicaid)ን፣ ቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ (TANF)እና ዊክን (WIC) ማጠናከርና ቤተሰቦች እነኚህን ለመጠየቅና ለማሳደስ መሙላት የሚገባቸውን ወረቀቶችንና ማመልከቻዎችን ማሳጠር፤ በተጨማሪም ይህ መረጃ ከ ህጻናት ትምህርት( ECE) መረጃዎች ጋር ቢገናኝ ዋጋው በተቀነሰ የህጻናት መዋያ ውስጥ የሚገባበትን ሂደት ቀለል እንዲል ያደርገዋል።
- ነፍሰጡር እናቶች ከመውለዳቸው በፊትና በኋላ በ WIC እንዲመዘገቡ ማድረግ፣ ወደፊት ምን ያህል ልጆች በዚህ በሚደረገው የህጻናት መዋያ ቅናሽ ሊጠቀሙ እንደሚችሉ አስቀድሞ የመገምገምና እቅድ የማውጣት ዕድል ይሰጣል።
- አንድ ሁለንተናዊ የሆነ የመረጃ አሰባብሰብ መንገድ መፍጠር፤ መረጃዎች ሁሉ በአንድ ዓይነት አያያዝ እንዲያዙ ማድረግ (ለምሳሌ የጤናና የትምህርት ችግሮችን በተመለከተ)
- ወደፊት ሊመጡ የሚችሉ የአደጋ ምልክቶችን በማህበረሰቡ ወጪ መቋቋም
- በተለያዩ ፕሮግራሞች መካከል ያለው ግንኙነት፤ በወንጀላዊ ተግባራት፣ በትምህርት፡ በህዝብ ጤንነትና በአእምሮ ደህንነት መካከል ሊኖር ስለሚችል ግንኙነት የሚሰበሰብ መረጃ፤ ለበጎ አድራጊዎች ያለውን ግንኙነት ሊጠቁምላቸው ይችላል። የዚህ አንድ ጥሩ ምሳሌ በሱስ መሰቃየት ምን ያህል ጣልቃ ገብነት እንደሚያስፈልገው መረዳት ይቻላል።

በተጨማሪም፤ የዲስትሪክቱ ሃላፊዎች፤ ከልደት እስከ 5 ዓመት ዕድሜ ያላቸውን ህጻናት ልጆችንና ቤተሰቦቻቸውን ለማገዝ፤ የጠባይ የጤና አገልግሎቶችና የትምህርት ምንጮችን ለማስተባበር ራእይ አላቸው። ይህም ስኬታማ የቤተሰብ ህይወት ለመምራት የሚያስፈልጉ የልጆች የ እድገት ተቋሞች ወይም በትምህርት ቤቱ ያሉ "የደህንነት ተቋሞችን" የሚደግፍ ሊያጠቃልል ይችላል። ሌላው የሚያሳስባቸው ነገር ቢኖር፤ቤተሰቦች የሚጠቀሚቸው ፕሮግራሞችንና አገልግሎቶችን ለማግኘት ምን ይህል እንደሚቸገሩና በፈተና እንደሚያልፉ ነው። ይህም በመሆኑ፤ መረጃ ሰጪዎች የማህበራዊ ጉዳዮች በሙሉ እርስበርስ መገናኘትና መሻሻል እንዳለባቸው ጠቁመዋል፣

- ***ለጉዳት የተጋለጡ ቤተሰቦችን የሚረዱ የጉዳይ አምባሳድሮች፣*** እነኚህ አምባሳድሮች፤ ቤተሰቦች በሚያስፈጋቸው ነገሮች ና ባሉት አያሌ ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች መካከል ያለውን ግንኙነት ለቤተሰቦች ይገልጻሉ፤ ምን ምን አገልግሎቶች እንዳሉ ያስረዳሉ፣ ልጆችን በፕሮግራሞች ውስጥ እንዲመዘገቡ ቤተሰቦችን ይረዳሉ፣ ፍቃድ በማግኘትም ያለውን ኢጋዥና ተገቢ የሆነ መረጃን ከአገልግሎት ሰጪዎች ጋር ይካፈላሉ።
- ***የወላጆች/ ቤተሰቦች ሸሪኮች፤*** ሸሪኮች በአሁኑ ወቅት ቢኖሩም፤ ቁልፍ የሆኑ መረጃ የሚሰጡ ሰዎች፤ ቤተሰቦች ሸሪኮች የሚሆኑት ከሚመሳሰሏቸው ወይም አንድ ዓይነት ተመሳሳይነት ካላቸው ቤተሰቦች ጋር መሆን አለበት (ለምሳሌ ልጆቻቸው በአንድ ዓይነት የዕድሜ ክልል ያሉ ወላጆች፤ የእድገት መጉተት ችግር ወይም ስንክልና ያለባቸው ልጆች ወላጆች፤ ከአንድ ዓይነት ባህል የመጡ ስደተኛ ቤተሰቦች...ወዘተ) ራሳቸውን ቅርብ ማድረግ አለባቸው፣ በዲስትሪክቱ ስለሚገኙት የተለያዩ ፕሮግራሞችና አገልግሎቶችም እውቀታቸውን ለማሳደግ መሰልጠን አለባቸው።

- **የቤተሰብ ኅብኘዎች፤** በአሁኑ ወቅት፤ ዲሲ-ፒ-ኤስ (DCPS ) ንና የህዝባዊ ቻርተር ትምህርት ቤቶች መማህራንን ጨምሮ አምስት ተቋሞች አሉ ቤተሰቦችን የሚኅበኙ። ይሁንና ይሄው የቤተስብ ጉብኘት በጣም የተለየ ሊሆን ይችላል። በኅብኘ ቡድኖች መካከልም ያለው ትብብር የተወሰነ ነው (ለምሳሌ ሁሉንም ቤተሰቦች በተለይ እነሱን ብቻ የሚመለከቱ ጥያቄዎች ከመጠየቅ ውጪ፤ ሌሎች አያሌ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ በተጨማሪ መጠየቅ)፣ የሚደረጉ ጉብኘቶችን ማዋሃሃድ፤ ጠቃሚ የሆነ መረጃ ለማግኘት፤ እነኝያ ለአደጋ የተጋለጡና ማግኘት ከሚገባቸው አገልግሎት በታች የሚያገኙ ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦች ያገኙት ካልነበረው ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች ጋር ማስተዋወቅ እንዲሁም ቤተሰቦች ሰራተኞችን የሚጠይቋቸው የተደጋገሙ ጥያቄዎችን ይቀንሳል።

**ግኘት 11 ሐ፤ ዲሲ አይ-ሲ-ሲ ( DC ICC) ለክፍል ሐ ፤ የእድገት መዘግየት ችግርና ስንክልና ላለባቸው ልጆች ቀልጣፋ የጣልቃ መግባት አገልግሎት መሰጠት እንዳለበት ለከንቲባው ጽህፈት ቤትና ለኦ-ኤስ-ኤስ-ኢ (OSSE) ምክር ይሰጣል።፡** ይሄው ዲሲ አይ-ሲ-ሲ (DC ICC) (በግኘት 6 ለ ላይ እንደተገለጸው) በከንቲባው የተመረጡ 25 አባላት ያለው ሲሆን (ዕድሜያቸው 12 ዓመት ወይም ከዛ በታች) ስንኩላን ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦችን፣ አገልግሎት ሰጪዎችንና በ አይዲያ( IDEA) የተጠቀሱ ወይም በከንቲባው የተመረጡ ሌሎችን ይጨመራል።

**ግኘት 11 መ፤ ኲን (QIN) በዲስትሪክቱ ውስጥ ባሉ ወጣት ልጆችንና ቤተሰቦችን በሚያገለግሉ ተቋሞች በተውጣጣ በውስጥ ተቋሞች ቀስቃሽ ኮሚቴ የሚደገፍ ነው።** ይህም ኦ-ኤስ-ኤስ-ኢ ዴል( OSSE DEL)፤ ኦ-ኤስ-ኤስ-ኢ የጤና ጥበቃና ደህንነት ክፍል (OSSE Division of Health and Wellness)፣ ዲ-ኤች- ኤስ( DHS)፣ ዲ-ቢ-ኤች (DBH)፣ ዲሲ ሄልት (DC Health)፣ ዲ-ኤች-ሲ-ኤፍ፣ (DHCF )፣ ሲ-አኤፍ-ኤስ-ኤ (CFSA)፣ የ ኲን (QIN) ዋና ተቋም የአመራር አካል ና የዲሲ አክሽን ፎር ችልድረን ( DC Action for Childre) የጥብቅና ድርጅትን ያጠቃልላል። የውስጥ ተቋሞች ቀስቃሽ ኮሚቴ ( interagency steering committee) የዲስትሪክቱ ተቋሞች ያላቸውን ምንጮች በሙሉ የህጻናት ልጆችን ና የቤተሰቦቻቸውን ጤንነትና ደህንነትን ለመጠበቅ እንዲሁም እድገታቸውን ለማጠናከር እንዲያውሉት ያደርጋል። በዚህ በኮሚቴው ስራ፤ ኦ-ኤስ-ኤስ-ኢ ( OSSE)ተካፋይ የሆነው ሲ-ሲ-ፒ(CCP በሚሰጡት ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች ሙሉ በሙሉ ተጠቃሚ እንዲሆንና ቤተሰቦችና አስተማሪዎች የአእምሮ ጤንነት ምክር፤ የምግብና የአመጋገብ ትምህርት እንዲሁም የአፍ ጤንነት ትምህርት ማግኘታቸውን ያረጋግጣል። ኦ-ኤስ-ኤስ-ኢ ( OSSE) ከ ዲ-ኤች-ኤስ ( DHS) ጋርም በመስራት፤የብቁነት ፖሊሲዎች አቅጣጫ እንዲይዙ በማድረግ፤ ቤተሰቦች ቅናሽ በሚደረግባቸው ፕሮግራሞች በሚገባ እንዲመዘገቡና በኲን (QIN)ፕሮግራም በመሳተፍ በሚሰጡት አገልግሎቶች በሚገባ በመጠቀም ላይ መሆናቸውን ያረጋግጣል።

# ማጠቃለያ

ጥራት ያለው የ ህጻናት ትምህርት( ECE) ተመክሮ፤ የልጆች ጤንነትና ትምህርታዊ ግኘት እንዲሻሻል መንገድ ይጠርጋሉ።[85,86,87] ዲስትሪክቱ፤ ከልደት እስከ 5 ዓመት ዕድሜ ያላቸውን በተለይም ለአደጋ የተጋለጡና ማግኘት ከሚገባቸው አገልግሎት በታች የሚያገኙ ልጆች ጥራት ያለውን አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግና አገልግሎቶችንም ማሻሻል ተቀዳሚ ዓላማው ነው። ይህም ለቤተሰቦችና አገልግሎት ሰጪዎች ከተመደበው እጅግ ሰፊ ከሆነው የእገዛ ስርአት፣ ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች፣ ፕሮግራሞችና ምንጮች በቀላሉ ለማየት ይቻላል። ዲስትሪክቱ፤ ምንም እንኳን ቤተሰቦች በጉዳዩ እንዲካፈሉ በማድረግ፤ አገልግሎት ሰጪዎች አስተያየታቸውን ለማበርከት የሚችሉበት ስርአት የፈጠረ፤ የከንቲባው ድጋፍ የታከለበት፤ በዲስትሪክቱ ባሉት ተቋሞች መካከልና በግልና በመንግስት

85 Bainum Family Foundation, *Early Learning Supply and Demand in the District of Columbia: Using Data to Identify Critical Gaps*, 2018.
86 Andres S. Bustamante, Kathy Hirsh-Pasek, Deborah Lowe Vandell, and Roberta Michnick Golinkoff. *Realizing the promise of high-quality early childhood education. Brookings Institution blog, 2017*, www.brookings.edu.
87 ZERO TO THREE, *America's Future Depends on Quality Childcare*, 2019.

ተቋሞችም ትብብር እንዲኖር አድርጎ ጠንካራ ስርዓት የፈጠረ ቢሆንም፤ አገልግሎት በማቅረብ በኩል አሁንም ገና ፍትሃዊ ያልሆነ አገባብና ልዩነት እንዳለና ይህም በወጣት ልጆች ስኬታማ ውጤቶች ላይ ጠባሳ ይተዋል። ዲስትሪክቱ፤ ከልደት እስከ 5 ዓመት የሚሰጠው አገልግሎት መሻሻልና መጨመር እንዳለበት ይረዳል፤ የትምህርት ተቋሞችን ቁጥር መጨመር፤ በተለይም በቤቶች( wards) 7 እና 8 ጥራት ያለው የትምህርት አገልግሎት እንዲኖር መስራት እንዳለበት ያምናል።

የፍላጎቶች ግምገማ፤ የህጻናት ልጆችን የትምህርት ስርዓት ለማጠናከር ለወጣው ስትራቴጂካዊ ዕቅድ መረጃ ይሰጣል፤ ይህም ግኝቶችን፣ ወቅታዊ ፕሮግራሞችን፣ ምንጮችንና አገልግሎቶችን በመጠቀም ዲስትሪክቱ፤ አንድ ዓይነት ራእይ፤ ዓላማ፣ ምሰሶዎን ለመገንባትና፣ ውጥኖችን ለማውጣት ይረዳዋል። ለስትራቴጂካዊ እቅድ ተጨማሪ እገዛ የሚሆን ደግሞ ከበጎ አድራጎት ድርጅቶች ፤ ከቤተሰቦች፤ በዲስትሪክቱ ካሉት ተቋሞችና ከህጻናት ትምህርት ባለሞያዎች ጋር ያለው ትብብር ነው። አንድ ላይ በትብብር መስራት፤ በወቅቱ ያለው ስርዓት ጥራት ያለው እንዲሆንና ዕድሜያቸው ከልደት እስከ 5 ዓመት የሆኑ ህጻናት ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦች ፍላጎቶች እንዲሟሉ ያደረጋል። የሚከተሉት አስተያየቶች ሙሉ በሙሉ እንድንገለገልባቸው የቀረቡ ዝርዝሮች ሳይሆኑ፤ ስትራቴጂካዊ ዕቅድ ለመገንባት የቀረቡ አማራጮች ናቸው።

### ፕሮግራሞችንና አገልግሎቶችን ለማግኘት

- ጥራት ያላቸውን የህጻናት ትምህርት ቦታዎችን ቁጥር ማብዛት፤ በተለይም ለጉዳት የተጋለጡና ማግኘት ከሚገባቸው አገልግሎት በታች የሚያገኙ ልጆች በብዛት በሚቀመጡባቸው ስፍራዎች ቁጥራቸው እንዲበዛ ማድረግ
- ቤተሰቦች አገልግሎቶቹን ለማግኘት በሚሞክሩበት ወቅት ሊያጋጥሟቸው የሚችሉ እክሎችን መገምገም
- በበጎ አድራጊዎችና በቤተሰቦች መካከል ያለውን ግንኙነት እንዲጠናከር ማድረግ፤ በተለይ ለአደጋ የተጋለጡና ማግኘት ከሚገባቸው አገልግሎት በታች የሚያገኙ ልጆች ቤተሰቦች ስላሉት ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች ያላቸው እውቅና ከፍ እንዲል ማድረግ
- ለአደጋ የተጋለጡና ማግኘት ከሚገባቸው አገልግሎት በታች የሚያገኙ ልጆች ቤተሰቦች ልክ ልጆቻቸው ትምህርት እንደሚጀምሩ ወላጆች ጋር ሳይነጠሉ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ
- በቤተሰቡ ፍላጎት መሰረት ወደ ቤት የሚደረጉ የጉብኝቶች ቁጥር እንዲበዛ ማድረግ

### የስርዓት መቀናበርና የስራ ትብብር

- በትምህርት አገልግሎት ሰጪዎች መካከል ያለውን የሶስት የትምህርት ዘርፎችን ግኑኝነት ማጠናከር(ለምሳሌ ዲሲ የመንግስት ትምህርት ቤቶች (DCPS )፣ ሲቢኦ( CBO) እና የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች)
- በህጻናት መዋያዎች፣ በቅድመ-ትምህርት መዋያዎች፣እና በ ኤች-ኤስ (HS) አገልግሎቶች ውስጥ ያለውን የአስተማሪዎች ስራ ለቆ መሄድን መረጃ ለይቶ ማወቅ

### የመረጃ አጠቃቀም

- በስርዓቱ ውስጥ ያለውን “ ለጉዳት የተጋለጡና ማግኘት ከሚገባቸው አገልግሎት በታች የሚያገኙ ልጆች”ሲባል ምን ማለት እንደሆነ በደንብ ግልጽ ማድረግ
- ከተለያዩ ቦታዎችና ምንጮች የተገኙ መረጃዎችን የማገናኘት እውቀት ለማዳበር ችሎታን ማዳበር፤ በዚህም ከልደት እስከ 5 ዓመት ዕድሜ ያላቸው ህጻናት የሚገለገሉባቸውን መረጃዎች ሁሉ ተደጋጋሚ ያልሆነ ቁጥር ለማግኘት መጠቀም፤ ይህም የትኞቹ ልጆች ናቸው አገልግሎት የማያገኙት፤ የትኞቹ ልጆች ናቸው የተለያዩ የአገልግሎቶች ስብስብ የሚያገኙት ለይቶ ለማወቅ ያስችላል።

# ተጨማሪ

## ተጨማሪ ሀ፤ በፍላጎት ግምገማ ላይ መረጃ የሰጡ ምንጮች

1. **በወቅቱ ያሉትን የፍላጎት ሪፖርቶችን መገምገም፤** በ 2016 እና 2019 መካከል የተደረጉ 20 የሚሆኑ የማእከላዊው መንግስትና የክፍለሃገሩ የፍላጎት ግምገማዎች እንደገና ታይተው ወይም ክለሳ ተደርጎባቸው፤ ዲስትሪክቱ ቁልፍ የሆኑ ተግባሮችን እንዴት በማከናወን ላይ እንዳለና ውጤታቸውን እንዲሁም በዲስትሪክቱ የፕሮግራምና የአገልግሎት አቅርቦት ላይ ያሉት ግኝቶች፣ ያገጠሙ ጋሬጣዎችና ጥራት መጠበቅን የመሳሰሉ ጉዳዮችን ለይቶ ለማወቅ ተችሏል። ከፍላጎት ግምገማዎች ሪፖርቶች በተጨማሪ፤ በዲስትሪክቱ ቁልፍ ስትራቴጂዎች ውስጥ በወቅቱ የሚካሄዱትን እንቅስቃሴዎችንና ውጤታማነትን ሙሉ በሙሉ በጥልቀት ለመረዳት፤ የክፍለሃገሩ አምስት ሌሎች ግምገማዎች እንደገና ታይተዋል።

2. **የአስተዳደር መረጃ፤** የወቅቱን ተካፋይነት፣ አመዳደብ፣ የአጠቃቀም ደረጃን…ወዘተ ለመገምገም ቅድመ-ኪንደርጋርተን፣ የህጻናት መዋያ፣ ኤች-ኤስ (HS)፣ ኢ-ኤች-ኤስ (EHS)፣ ቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ (TANF)፣ ሜዲኬድ( Medicai) እና ዊክ (WIC) የሚያጠቃልሉ የአስተዳደር መረጃዎች ተሰብስበዋል።

**ቤተሰቦች የሚሰሙባቸው ስብሰባዎች:** እነኚህ ቤተሰቦች የሚሰሙባቸው ስብሰባዎች የተቀነባበሩት፤ህጻናት ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦች ምን እንደሚፈልጉና ምን እንደሚያስፈልጋቸው በበለጠ ለመረዳትና ለመገምገም፤ ፕሮግራሞችንና አገልግሎቶቹን ሲጠቀሙ ያሳለፉትን ተመክሮ ለማወቅ እንዲሁም ልጆቻቸው ከህጻናት መዋያ ወደ ትምህርት ቤቶች ሲሸጋገሩ የሚሰማቸውና ነገሮችን ለማሻሻል ስላሉት ዕድሎች መነጋገር ነው። በእነዚህ ወደ 32 ቡድኖች በተከፋፈሉ ሰብሰባዎች ውስጥ በአንዱ ከአምስት ዓመት ዕድሜ በታች ልጆች ያሏቸው አንድ መቶ አስራ አምስት ቤተሰቦች በመሳተፍ ስለ ፕሮግራሙና ስለሚሰጠው አገልግሎት(ለምሳሌ ስለህጻናት መዋያዎች፣ ቤት ውስጥ ስለሚደረጉ ጉብኝቶች፣ ከትምህርት ቤት በፊት ስለሚገባበት ትምህርት (Head Start) ስለ ሴቶች፣ ህጻናትና ልጆች ተቋም (WIC), እንዲሁም ስለ ፕሪሌ (pre-K) ተመክሮና አስተያየት ተለዋውጠዋል። ተካፋዮቹ፤ አነስተኛ ገቢ ያላቸው፣ የቤት-አልባነት ተመክሮ ያሳለፉ፣ በገቢ የሚወሰን እርዳታ የመቀበል ተመክሮ ያላቸው፣ የእድገት መጓተት ችግር ወይም ስንክልና ያለባቸው ልጆች ቤተሰቦች፡ በማደጎ ልጆች መኖርያ( foster care) ልጆች ያላቸውና በቤት ጉብኝት ስራ የተካፈሉ ቤተሰቦች ይገኙባቸዋል።

3. **የባለሙያዎች የትኩረት ቡድን ስብሰባዎች፤** የህጻናት ልጆች ባለሙያዎች፤ ህጻን ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦች፤ በፍላጎቶቻቸውና በሚያገጥሟቸው ችግሮች ላይ ያላቸውን አስተያየት፤ በትኩረት ቡድኑ ሰብሰባዎች እንዲሰጡ ተደርገዋል። ከብዙ ቦታዎች የተውጣጡ 90 ባለሙያዎች የተሳተፉባቸው ሃያ ሶስት የትኩረት ቡድኖች ስብሰባዎች ተካሂደዋል። ተሳታፊዎች፤ ከማእከሎች፣ ከቤተሰብ የህጻናት መዋያዎች፣ ኦፊሲያላዊ ካልሆኑ አገልግሎት ሰጪዎች፣ ከመንግስትና ከቻርተር ትምህርት ቤቶች፤ከሲ-ቢ-ኦ (CBO)፣ ከኤል-ኢ-ኤ( LEA)፣ ከተለያዩ የህጻናት ትምህርት ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች( ለምሳሌ፤ ጤና ጥበቃ፣ የጠባይ ጤንነት፣ ከበጎ አድራጎት ድርጅቶች) የተወከሉ ይገኙባቸዋል። ተወካዮቹ፤ ስምንት ዳይሬክተሮች/ የሲ-ቢ-ኦ አስተዳዳሪዎች፣ የቤተሰብ የህጻናት አገልግሎት ሰጪዎች፣ ሰባት መማህራን፣ ሶስት የትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎችና ከኤል-ኢ-ኤ የተወከሉ የህጻናት ትምህርት ሃላፊዎች፣ ስምንት በመኖርያ ቤታቸው ውስጥ ልጆች የሚንከባከቡ፣ 19 የስትሮንግ ስታርት (Strong Star) ና የአገልግሎት አስተባባሪዎች፣ ስምንት የኩን (QIN) አሰልጣኞች ፣ 11 የቤተሰብ ትኩረት ባለሙያዎች፤ሁለት የሄልፐ ሚ ግሮ( Help Me Grow) ሰራተኞች፤አንድ የዊክ (WIC) ሰራተኛ፤ስድስት የቤት ጉብኝት የሚያደርጉ ሰራተኞች፣ ሁለት የካፒታል ኳሊቲ (Capital Quality) አቀላጣፊዎች፣ ሰባት የአእምሮ ጤንነት አማካሪዎች፣ አንድ የቤተ መጻህፍት ባለሙያ፤አንድ የገና የህጻናት መዋያ ሰራተኛና ስድስት የዴል( DEL) ተወካዮች ይገኙባቸዋል።

4. **የቁልፍ መረጃ ሰጪዎች ቃለመጠይቆች፤** የዲስትሪክቱ ተቋሞች፤ ለጉዳት የተጋለጡና ማግኘት ከሚገባቸው አገልግሎት በታች የሚያገኙ ዕድሜያቸው ከልደት እስከ አምስት ዓመት የሆኑ ህጻናትንና ቤተሰቦቻቸውን በበለጠ ለመርዳትና ለማገልገል እንዲቻል፤ ቀደምትነት የሚሰጣቸው ጉዳዮች፣ ዓላማዎችና የረጅም ግዜ ራእዮች ምን እንደሆኑ በበለጠ ለመረዳት፤ ለዲስትሪክቱ ሃያ አንድ ቁልፍ በጎ አድራጊዎች ቃለመጠይቅ ተደርጎላቸው ነበር። ፕሮግራሞችንና አገልግሎቶችን ቅርጽ ለማሳያዝ፤ ያሉ ዕድሎችና ጋሬጣዎች ምን እንደሆኑና በተቋሞች መካከል አጠቃላይ የስራ ትብብር እንዴት ሊኖር እንደሚችል፤ ተጠያቂዎች አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

5. **የዲሲ የቤተሰብ ጥናት፤** በዲስትሪክቱ ውስጥ ከሚገኙ የተለያዩ ቤቶች( wards) የተውጣጡ፤ የተለያየ የገቢ መጠንና የተለያየ የትምህርት ደረጃ ያላቸው ቤተሰቦች (ቁ=2,099 )፤ ዕድሜያቸው ከልደት እስከ አምስት ዓመት የሆኑ ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦች ፤በዲስትሪክቱ ስለሚሰጡት አገልግሎቶችና ፕሮግራሞች እንዲሁም ጠቀሜታዎች ምን ያህል እውቀት እንዳላቸው በኦንላይምን ይሁን በወረቀት በተደረገ ጥናት መረጃ ተለዋውጠዋል። በተጨማሪም፤ የልጆቻቸውን የእድገት ተቋም ሲመርጡ ምን ግምት ውስጥ እንደሚያስገቡና ቅድምያ የሚሰጡት ለየትኛው ጉዳይ መሆኑን አብራርተዋል።

6. **ለሙከራ የተደረጉ የጠቋሚ ፕሮጀክቶች ጥናት:** ለሙከራ የተደረጉ ጠቋሚና ማሳያ ፕሮጀክቶች ዕድሜያቸው ከልደት እስከ አምስት ዓመት የሆኑ ልጆች ባሉባቸው ቦታዎች ተደርገዋል። ይህም ቁል የሆኑ በጎ አድራጊዎች ውጤት ለማየት አስችሏቸዋል።

7. **የቅርብ የክፍለሃገርና የመላው አገር የህጻናት ትምህርት ሪፖርት ኢ- ሲ- ኢ( ECE) ሪፖርት፤** በክፍለሃገርና በአገሪቱ ውስጥ የህጻናት ትምህርትን በተመለከተ የተሰበሰቡ የቅርብ ግዜ መረጃዎች፤በፍላጎት ግምገማ ላይ ተጨማሪ መረጃ እንደሚሆኑ ተጠቁሟል።

## ተጨማሪ ለ ፤ ለጉዳት ለተጋለጡና ማግኘት ከሚገባቸው አገልግሎት በታች ለሚያገኙ ልጆች፤ ጥራት ያለው እንክብካቤ ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ፤ ዲስትሪክቱ የሚወስዳቸው እርምጃዎች

### በጠባይ፣ በማህበራዊ፣ በስሜታዊና በአእምሮ ጤና ጥበቃ ችግር ላይ ያተኮሩ ፕሮግራሞች

**ዲሲ ሲድ ፕሮጀክት (DC SEED Project** ) መድሃኒቶችን ያለአግባብ መጠቀምን የሚመለከትና የአእምሮ ጤና ጥበቃ አገልግሎት አስተዳደርን (Substance Abuse and Mental Health Services Administration (SAMHSA))የሚቃኝ ፕሮጀክት ሲሆን ሁለት የማህበረሰቡ ፕሮግራሞችን በማስተዋወቅ፤ ለልጆች በማስረጃ የተደገፈ የጣልቃ ገብነት እርዳታ የሚያደርግና ከፍተኛ ጥራት ያለው በቤተሰብ ባለሙያ ያለበት ነው።

**ቅድሚያ ለቤተሰብ - ዘ ፋሚሊስ ፊርስት (The Families First )**፤ ይህ ፕሮጀክት በ ዲ-ቢ-ኤች (DBH)ና በሲ-ኤፍ-ኤስ-ኤ( CFSA) የተፈጠረ፤ በማረጋገጫ የተሸኘ፣ ለልጆችና ለቤተሰቦቻቸው የሚሰጥ የአእምሮ ጤንነት ጥበቃ ፕሮጀክት ነው። እነኚህ ለቤተሰቦች የሚቀርቡ ፕሮግራሞች፤ ለቤተሰቦቹ የሚቀርቡት በዚሁ በፋሚሊስ ፊርስት (The Families First ) ሲሆን በማስረጃ የተደገፉና የቤተሰቦችን ህይወት ማጠናከር እንደሚችሉ የተመሰከረላቸው፤ የቤተሰቦችን አሰራር የሚያጠናክሩና ቤተሰቦች የተወሳሰቡና የረጅም ግዜ  ችግሮች ውስጥ እንዳይገቡ የሚያግዙ ናቸው። የዚህ የፋሚሊስ ፊርስት ፕሮግራም ፕሮጀክቶች፤ በተለያዩ የዕድሜ ክልል ላሉ ልጆች በማረጋገጫ የተረጋገጡ የአእምሮ ህክምና የሚሰጥና በቤተሰቡ ህይወት ውስጥ ለውጥ የሚያመጣ ሲሆን፤ የልጅ-ወላጅ  የአ እምሮ ህክምና ለቤት ውስጥ ለሚደረግ ረብሻ (Child-Parent Psychotherapy for Family Violence (CPP-FV) ፤ ዕድሜያቸው ከ 0-6 ለሆኑት፤ Parent-Child Interaction ደግሞ ከ2-6 ዓመት ለሆኑ ልጆች ቀርቧል።

**ጤናማ የወደፊት ዕድል-ሄልቲ ፉቸርስ (Healthy Futures)** ሄልቲ ፉቸርስ፤  ህጻናት ገና በልጅነታቸው ለሚያስፈልጋቸው የአእምሮ ጤንነት ምክር የሚሰጥና የህጻናትን ማህበራዊና ሰሜታዊ እድገት የሚደግፍ፤ የህጻናት መዋያ ቦታዎች ውስጥ ገና በግዜ የሚታዩ የጠባይ ችግሮችን የሚገጥም ነው። ሄልቲ ፉቸርስ (Healthy Futures)፤ ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዮች፤ የመምህራን፣ የእንክብካቤ አድራጊዎች፣ የአስተዳዳሪዎች ችሎታን እንዲሁም የስርአቱን አካሄድ መገንባት፣ በተጨማሪም በማረጋገጫ የተደገፈ፣ ችግር ከመባባሱ በፊት፤ ቀደም ብሎ ጣልቃ በመግባት፤ ችግሩ የሚፈታባቸው ፕሮግራሞች እንዲኖሩ ማድረግ፣ ማህበራዊ ሁኔታዎችና ራስን በራስ የመቆጣጠር ችሎታ እንዲያድግ በማድረግ የልጆች አጠቃላይ የአእምሮ ደህንነት አዎንታዊ ውጤት እንዲያሳይ ማድረግ ናቸው።

**እንዳድግ እርዱኝ-ሔልፕ ሚ ግሮ (Help Me Grow)**፤ የጥሪ ማእከል፤ ማህበራዊና ስሜታዊ ችግር ያላባቸውን ልጆች ድጋፍ ለመስጠት የተቋቋመ ነው።  ሄልፕ ሚ ግሮ ዲሲ( Help Me Grow DC) ማህበራዊና ስሜታዊ ችግሮች ያላቸውን ልጆችና ቤተሰቦች በሙሉ የሚያግዝ ፕሮግራም ነው። ሄልፕ ሚ ግሮ ዲሲ( Help Me Grow DC)  የእድገትና የጠባይ አገልግሎቶች መካከል ግንኙነት የሚፈጥርና በአራት ቁልፍ መንገዶች ቤተቦችንና ልጆችን የሚረዳ ድርጅት ነው (1)በስልክ ተደውሎ የሚገኝ የተባበረ አገልግሎትና እንክብካቤ a centralized telephone access point for services and care coordination; (2) የፕሮግራም አጠቃቀምን የሚያስረዳና በቤተሰቦችን በአገልግሎት-ሰጪዎች መካከል ግንኙነት እንዲኖር በስልክ ከብዙ ሰዎች ጋር ትውውቅና የመገናኛ መስመር እንዲኖር የሚያግዝ  የቤተሰቦችና የማህበረኮም  ባለሞያ (3) ችግሮችን በግዜ ማወቅ የሚችልና በግዜ የጣልቃ መግባት መፍትሄ የሚሰጥ የልጆች ጤና ሓኪም እና (4) ያለውን እጥረትና እንቅፋት መለየትን ጨምሮ የመረጃ መሰብሰብና የመረጃ መገምገም

**ኮግኒቶ (Kognito)**፤ በ ዲ-ቢ-ኤች( DBH) የሚሰጥ ፕሮግራም ነው። በቅድመ- ትምህርት( Pre-K) የሚያስተምሩ መማህራን ደግሞ ትምህርቱን እንዲያገባደዱ ግዴታ ነው።
የ 2012 የመሻሻያ ደንብ - የሳውት ካፒቶል ስትሪት ሜሞርያል አሜንድመንት አክት (The South Capitol Street Memorial Amendment Act) የወጣው በዲስትሪክቱ በጥይት የተገደሉትን የአራት ወጣቶችን ሞት በተመለከተ የተሰጠ ምላሽ ነው። ይህም ደንብ ወይም ህግ በዲሲ ውስጥ ያሉትን የልጆችን የአእምሮና የጠባይ ጤና ጥበቃን ለማሻሻል የወጣ ነው። ከዚህ የተገኘው ውጤትም፤ በዲስትሪክቱ በሁሉም ክፍሎች የሚያስተምሩ አስተማሪዎች፤ ይህንን በኦንላይን የሚሰጠውን ፒ-ዲ (PD) መሳርያ በመጠቀም ማን አደገኛ ቦታ ላይ እንዳለ ለመገምገምና ለመለየት ያግዛቸዋል፤  ቤተሰቦችና ልጆችም ከሚሰጠው የጠባይ ማረምያ እርዳታ ጋር ግንኙነት እንዲፈጥሩ በማድረግ በኩል ይረዳቸዋል። ኮግኒቶ (Kognito)፤ አስቸጋሪ በሆኑ አርእስቶች ዙርያ ውይይት እንዲደረግ የሚያበረታታ፤ በኦንላይን በሚሰጠው ትምህርት አንዳንድ ከሃቀኛ ታሪክ የተወሰዱ የማስመሰያ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት፤ የእአምሮ ችግሮችን በተመለከተ ንቃትን፣ እውቀትንና ችሎታን ከፍ የሚያደርጉ እገዛዎችን ያደርጋል። በኮግኒቶ( Kognito) የሚቀርቡት ፕሮግራሞች፤ አስተማሪዎች አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲያጋጠሙ እንዴት መፍታት እንደሚችሉና ከተማሪዎችና ከቤተሰቦች ጋርም መኖር ስለሚገባው ውይይት በዝርዝር እንዲያውቁ ያግዛል። ቀደም ሲል ኮግኒቶ (Kognito) የሚሰጠው አገልግሎት በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ላሉት አስተማሪዎች ብቻ ነበር። በአሁኑ ወቅት ግን፤ በህጻናት እንክብካቤ አገልግሎት ለተሰማሩ ባለሙያዎችም አገልግሎቱን መስጠት ጀምሯል።  እውነተኛ ታሪክን ቀርጾ በሰእላዊ መግለጫ የማቅረብ የቅጂ ወይም የማስመሰል ፕሮግራም፤ የትምህርት ባለሙያዎች ልምምድ እንዲያደርጉና በቤት ውስጥ በሚያጋጠመው ችግር  አንዳች መጥፎ ጠባይ የሚያሳይ ልጅ ችግር

ለመፍታት እንዲችሉና ከቤተሰብ ጋር ማድረግ ስለሚገባቸው ውይይት ልምምድ እንዲያደርጉ ያደርጋል። በዲስትሪክቱ የሚሰሩ አስተማሪዎችም ሆኑ የህጻናት ትምህርት ባለሙያዎች የራሳቸውን አካውንት በመፍጠር በኦንላይን ባለው ትምህርት ሊገለገሉ ይችላሉ።

**የወላጆችና የህጻናት እድገት ፕሮግራም- የፒስ ፕሮግራም** (PIECE Program)
(PIECE Program) ከ ሰባት ዓመት ዕድሜ በታች የሆኑ ህጻናት ልጆች የማህበራዊ ችግር፤ ስሜታዊ ወይም የጠባይ ችግር እንዳላባቸው ሲያሳዩና ይህ ችግርም ቤት ውስጥም ሆነ በትምህርት ቤት ወይም በማህበረሰቡ ውስጥ አፍራሽ ተግባራት ሲፈጽሙ ፤ ጣልቃ በመግባት በህጻናት ልጆች ስነአእምሮአዊ ስራ ቡድን (Child Psychiatric Practice Group) በኩል እርዳታ ያደርጋሉ። ይህ ፕሮግራምም የዲ-ቢ-ኤች ( DBH)ቅርንጫፍ ነው።

**ቀዳማይ ፕሮጀክት (Primary Project)** የሚባለው ልጆች ገና ቅድመ-ኪንደርጋርተን ውስጥ እያሉ በትምህርት ቤት ውስጥ 3ኛ ክፍል እስኪገቡ ድረስ ሁኔታቸውን የሚመረምርና አጋዥ አስተማሪዎች ስልጠና የሚያገኙበት፣ ልጆች አንዳንድ የጠባይ ችግር ሲታይባቸው ጣልቃ የመግባት እርዳታ ሊያገኙ የሚችሉበትና በማረጋገጫ የተደገፈ ምርመራ የሚያገኙበት ዕድል የሚሰጥ ነው።

## የእድገት ወደኋላ መጎተት ወይም ስንክልና ላይ የሚያተኩር ፕሮግራም

**የጠባይ ጤንነት አነሳሽነት**፤ ዲስትሪክቱ፤ ገና በውቅቱ፤ የእድገት መዘግየት ወይም የጠባይ ችግር ያለባቸውን ልጆች ለይቶ የማወቅ ክፍለሃገር-አቀፍ የሆነ፣ አጠቃላይና የተውሃሃደ የማወቅያ ስርአት አለው። የጠባይ ጤንነት ስርአት ሃይለኛ ጎን፤ አጠቃላይ ስራአተ-ቅርጽና በርካታ የመግብያ እድሎች ያሉት የገንዘብ አበርክቶ ምንጮችና አነሳሽነት ያለው መሆኑ ነው። የወጣቶችን የጠባይ ጤንነት ለማውቅና በዛውም አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ ቁልፍ አነሳሽነቶች አሉ።

**አርሊ ስቴጅ (Early Stages)** ፤ ይህ ፕሮግራም ዕድሜያቸው ከ 8 ወራት እስከ 5 ዓመት ከ 10 ወራት የሆነ ህጻናት የሚገለገሉበት ሁለት የምርመራ ማእከኖችን በመፍጠር ስንክልና ወይም የሆነ ዓይነት የዕድገት መዘግየት ችግር ያለባቸውን ልጆች ለመለየት የሚያገለግልና የሚሰጡ አገልግሎቶች ለእነሱ አስፈላጊ በሆነ መንገድ ለማስተካከል የሚያስችል ነው። እርሊ ስቴጅ (Early Stages)የተባለው ፕሮግራም የዲሲ የመንግስት ትምህርት ቤቶች አካል ሲሆን፤ በዲሲ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚማር ማንኛውንም ልጅ፤ በቤት ውስጥ የሚማሩ ልጆችንና ገና ትምህርት ቤት ያልገቡትን ህጻናት ልጆችን የሚያገለግል ፕሮግራም ነው። ፕሮግራሙ በተጨማሪ በዲስትሪክቱ፤ ከዲስትሪክቱ ውጪም ላሉ  በግል ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ወይም በልጆች የእድገት ተቋሞች ውስጥ የሚሳተፉ ልጆችንም ያገለግላል። እነኚህ አገልግሎቶች በሙሉ በነጻ፣ ካለ ምንም ክፍያ የሚሰጡ ናቸው።

**ጠንካራ አጀማመር Strong Start, በ** OSSE የሚካሄደው የዲስትሪክቱ  የቀልጣፋ ጣልቃ-ገብነት ፕሮግራም፡  መላውን ዲስትሪክት የሚያገለግል፣ የተቀናጀና የተባበረ፣ ባለ ብዙ-ዘርፍ እገዛ የሚያድርግና ስንክልና ወይም የዕድገት መዘግየት ችግር የሚያጋጥማቸውን ህጻናት ልጆችና ቤተሰቦቻቸውን የሚያግዝና የሚያስፈልጋቸውን አገልግሎት እንዲያገኙ የሚያደርግ ነው። መንግስታዊው IDEA፣ ክፍል ሐ ከዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ህዝባዊ ሕግ 1-2-119 (District of Columbia Public Law 1-2-119) ጋር በመተባበር፣ ስንክልና ያለባቸው ልጆችና ቤተሰቦች ልዩነት ሊያመጣ የሚችል የተባበሩ አገልግሎቶችን ከመጀመርያው ጀምሮ እንዲያገኙ ይሰራል።እነኚህ አገልግሎቶች ከሁኔታዎች ጋር የሚቀያየር ወይም እንደየሁኔታው የሚሄዱ፣ የተገለጋዩን ባህልና ልምድ ግምት ውስጥ የሚያስገቡ፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ ስንክልና ወይም የዕድገት መዘግየት ያለባቸው ልጆችና ቤተሰቦች ፍላጎት የሚያሟሉ ናቸው።

## ተቋሞችን የሚያሻሽሉ ፕሮግራሞች

**ጥራት ያለው የልጆች እንክብካቤ ለማግኘት የሚደረግ የገንዘብ አበርክቶ ለማግኘት (Access to Quality Child Care Expansion Grant (A2Q).** የዚህ ኤኪው(A2Q)  የገንዘብ አበርክቶ ዓላማ፤ ኢ-ሲ-ኢ (ECE ) ለህጻናት ልጆች የሚሰጠውን አገልግሎት ማጠናከር ነው። ይህም አዳዲስ የህጻናት መዋያዎችን መገንባትን ያጠቃልላል። ኤል-አይ-አይ-ኤፍ(LIIF) ከ ኦ-ኤስ-ኤስ-ኢ (OSSE) እርዳታ ጋር ህንጻዎችን ለማሻሻል፣ ለመጠገን፣ የገንዘብ ይዘትም እንዲሻሻል በመስራት በዲስትሪክቱ የህጻናት መዋያዎች እንዲበዙ ያደረጋል። ,

**የህጻናት የትምህርት ጥራት የገንዘብ አበርክቶ( Early Learning Quality Fund (ELQF)**፤  ይህ ፕሮግራም በቤናም ፋሚሊ ፋውንዴሽን (Bainum Family Foundation) እና በሪኢንቬስትመንት ፋንድ ( Reinvestment Fund) ገንዘባዊ አበርክቶ የሚተዳደር ሆኖ ዓላማው ጥራት ያላቸው የህጻናት መዋያዎች እንዲበዙ ለማድረግ ሆኖ ፍቃድ ያላቸው የህጻናት መዋያ ባለቤቶች ተቋማቸውን እንዲሻሽሉ የገንዘብ እርዳታ የሚያደርግ ነው። ፕሮግራሙም በቤቶች 7 እና 8  (wards 7 እና 8) ውስጥ የሚገኙ የስራ ፍቃድ ያላቸውን የህጻናት መዋያዎችን የሚያግዝ ነው። በዚህ እርዳታም፤ ፕሮግራሙ 625 ጥራት ያላቸውን የህጻናት መዋያዎችን በ2020 ማገባደጃ ላይ ለመጨመር ዕቅድ አለው።

## የጤናና የደህንነት ጥበቃ ፕሮግራሞች

**ጤናማ ህጻናት (ሄልቲ ቶትስ-Healthy Tots)** በጤና ጥበቃና ደህንነት ክፍል በ OSSE የሚተዳደር ፕሮግራም ሲሆን ህጻናት የሚማሩባቸው ተቋሞች እንዲሻሻሉ የገንዘብና የምንጮች እገዛ የሚያደርግ ነው። በዚህም፤ ጥራት ያለው የደህንነት አገልግሎት ህጻናት ልጆች እንዲያገኙና ተመጣጣኝ ምግብ እንዲያገኙ የሚያግዝ ነው። ይህ ሄልቲ ቶትስ (Healthy Tots) የተባለው ተቋም፤ የምግብ ትምህርት እንዲሰጥ፤ የሰውነት እንቅስቃሴ እንዲደረግ፤ የአትክልት ስራ፤ የአስተማሪዎች ስልጠናንና ትምህርትና ደህንነትን እንዲሁም የቤተሰቦች በሁሉም መስኮች መሳተፍን ይደግፋል።

## የማስወገጃ እገዛ ፕሮግራም

**የጠንካራ ቤተሰቦች ፕሮግራም (Strong Families Program)** ፤ የአገር ውስጥ ደህንነት ሚኒስቴር (DHS) እና የቤተሰብ አገልግሎት አስተዳደር (Family Services Administration)፣ የጠንካራ ቤተሰቦች ፕሮግራምን( Strong Families Program (SFP)ክፍል ያስተባብራሉ። ይህ አስቀድሞ ችግር እንዲወገድ የሚያደርግ የማስወገጃ ፕሮግራም፤ በዲስትሪክቱ ውስጥ ያሉት በከፍተኛ ችግር/ቀውስ ውስጥ በማለፍ ላይና በመጨረሻም ወደቤተሰብ ወይም ልጆች መበታተን የሚያመሩ፤ አንድ ብቻ ሳይሆን የተወሳሰቡ ችግሮች ያሏቸው ቤተሰቦችን የሚያግዝ ነው። ይህ ፕሮግራም በሚስጢር የሚያዝ ብቻ ሳይሆን በግለሰቡ ላይ ያተኮረ ዕቅድ ያለበትና ውሳኔ የሚሰጠውም በጉዳዩ በሰለጠኑ፣ አዎንታዊና ሰኬታማ ውጤቶችን በማስገኘት በኩል በተካኑ ሰራተኞች ነው።

## ወደ ሌሎች  የሚመሩ ምንጮች

**የዲሲ ልጆች እንክብካቤ ግንኙነት፤** ዲሲ ሲ-ሲ-ሲ (DC CCC) የዲስትሪክቱ ሲ-ሲ-አር & አር ( CCR&R) ነው።  ይህ የሲ-ሲ-አር & አር ( CCR&R) ደንብ፤ ቤተሰቦች፡ የህጻናት ትምህርት ኢ-ሲ-ኢ( ECE) አገልግሎት ሰጪዎችና የዲስትሪክቱ ማህበረሰብ የተወሃሃደና ውጤታማ የሆኑ በማረጋገጫዎች የተደገፉ እገዛዎችና አገልግሎቶች የሚያገኙበትን መንገድ የሚፈጥር ነው። እነኚህ አገልግሎቶችና እገዛዎች፡ በሚከተሉት ብቻ ሳይወሰኑ፤ የሚቀጠሉትን ያጠቃልላሉ፤

- ቤተሰቦች፤ ከህጻናት ትምህርት ከ ECE ጋርና ትምህርታዊና ገንዘባዊ ዕድሎች ሊገኙ ከሚችሉባቸው ምንጮች ጋር እንዲገናኙ ማድረግ
- የህጻናት ትምህርት አስተማሪዎች በሙያቸው የሚሰለጥኑበትን ዕድልና ትምህርታቸውን ለመቀጠል ከሚያስችላቸው ምንጮች ጋር እንዲገናኙ ማድረግና በሙያቸው አባልነት የሚያገኙባቸው ምንጮች ጋር ማገናኘት
- በህጻናት ትምህርት ቤት ውስጥ ያሉ አተዳዳሪዎች ቴክኒካዊ እገዛ፡ ምክርና መመርያዎች የሚያገኙበትን መንገድ መክፈት
- በመረጃዎች ሃብታም የሆነ፤ ቤተሰቦችና መማህራን  በአካል ተግኝተውም ሆነ በኦንላይን መጽሃፍትና የተለያዩ ጽሁፎች መዋስ ከሚችሉበት ቤተ መጻህፍት ጋር የሚገናኙበትን መንገድ መፍጠር
- በዲስትሪክቱ መንግስታዊ ድርጅቶችና ሌሎች የግል ተቋሞች ጋር የትብብር ግንኙነት የሚመሰረትበትና የሚጠናከርበትን መንገድ መፍጠር